ነውርነት - በሕጋዊነት

ገጽ 11

ከወደቅንበት ተነስተን አባራችንን እናራግፍ

ገጽ 10

ቅድመ ምርመራ - ስጡት ጤና

ገጽ 18

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

83ኛ ዓመት ቁጥር 033 ጥቅምት 3 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# የወንጪ

## ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት በዚህ ወር መጨረሻ ይመረቃል

ገጽ 4





## “በኢትዮጵያ የተመድ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መርማሪ ኮሚሽን የጊዜ ቆይታ መቋረጡ ትልቅ የዲፕሎማሲ ድል ነው”

- አምባሳደር ዘነበ ከበደ
በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓና አሜሪካ ጀነራል ዳይሬክተር

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የተመድ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መርማሪ ኮሚሽን የጊዜ ቆይታ መቋረጡ ለኢትዮጵያ ትልቅ የዲፕሎማሲ ድል መሆኑን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓና አሜሪካ ጀነራል ዳይሬክተር አምባሳደር ዘነበ ከበደ አስታወቁ፡፡

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓና አሜሪካ

“በኢትዮጵያ የተመድ ... ወደ ገጽ 9 ዞሯል

## “የኮሚሽኑ ትኩረት የችግሩ ምንጭ በመለየት ሁነኛ መፍትሔ የመፈለግ አቅጣጫን ተከትሉ መሥራት ነው”

- አቶ ጥበቡ ታደሰ
የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ቃል አቀባይ

አስቴር ኤልያስ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በዋናነት የሚያተኩረው በምክክር ሒደት የችግሩን ምንጭ በመለየት ከዚያ አዙሪት ለመውጣት ሁነኛ መፍትሔ የመፈለግ አቅጣጫን ተከትሎ መሥራቱ ላይ ነው ሲሉ የኮሚሽኑ የሚዲያ ኮሙኒኬሽንና አጋርነት ዘርፍ አስተባባሪ እና የኮሚሽኑ ቃል አቀባይ አቶ ጥበቡ ታደሰ አስታወቁ።

አቶ ጥበቡ ለኢፕድ እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በ2016 በጀት ዓመት አጋማሽ ላይ ምክክሩን ለመጀመር ተዘጋጅቷል። ኮሚሽኑ በዋናነት የሚያተኩረው የችግሩን ምንጭ በምክክር ሒደት በማግኘት ከዚያ አዙሪት ለመውጣት ሁነኛ መፍትሔ የመፈለግ አቅጣጫን ተከትሎ መሥራቱ ላይ ነው።

በአብዛኛው ዋና ትኩረታችን እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ አለመግባባቶች ላይ ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ እነዚህ አለመግባባቶች በአጭር ጊዜ የተወለዱ ሳይሆኑ ለዘመናት የነበሩና ሲከማቹ ቆይተው ዛሬ የደረሱበት ደረጃ ላይ የደረሱ ናቸው ብለዋል።

አቶ ጥበቡ እንዳሉት፤ አለመግባባቶች ለመፈጠ ራቸው ፖለቲካው አካባቢ ያሉ ቀውሶች የራሳቸው


ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

ሚና አላቸው። ነገር ግን ምናልባት ዋነኛ ምክንያት ናቸው ብሎ መውሰዱ ተገቢ ላይሆን ይችላል። ላለመግባባት አሁን ያለውም ሆነ ቀደም ሲል የነበረው የሀገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት የራሱ የሆነ አስተዋፅዖ አበርክቷል።

ከዚህ ጎን ለጎን ታሪኮቻችንን በተለያየ መንገድ የምንረዳበት

“የኮሚሽኑ ትኩረት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## በአዲስ አበባ ከ802 ሺህ በላይ ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት ያገኛሉ

በዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ በትምህርት ምገባ መርሐ ግብር ከ802 ሺህ በላይ ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ ተጠቃሚ መሆናቸውን የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎችና በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደርን ጨምሮ የተለያዩ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ትናንት የደጃዝማች ወንድይራድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምገባ መርሐ ግብርን ጎብኝተዋል፡፡

በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ በከተማዋ በመከናወን ላይ በሚገኘው የትምህርት ቤት ምገባ መርሐ ግብር ከ802 ሺህ በላይ ተማሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በአዲስ አበባ ከ802 ... ወደ ገጽ 9 ዞሯል






## ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ጥንቃቄ ሲደረግ ይገባል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ሰብሎችን በወቅቱ መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ የሚኖረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በደረሱ ሰብሎች ስብሰባ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያሳድር በየመሐሉ የሚኖረውን ደረቅ ቀን በመጠቀም የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ በማንሳት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

በመግለጫው የሚኖረው እርጥበት በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራልም ተብሏል።

ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱ ለደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ቀደም ብሎ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር የጠቀሰው መግለጫው፤ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ መሻሻል እና የውሃ አቅርቦት ከማረጋገጥ አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል ብሏል።

በሌላ በኩል ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተነግሯል።

በሚቀጥሉት ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው በደቡብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ ብሏል መረጃው። በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንደሚኖር አኃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ ብሏል ።

በተጨማሪም በፀሐይ ኃይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል ሲል አስታውቋል።

በቀጣይ ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ሁሉም የአርሲ፣ የባሌና የጉጂ ዞኖች፣ ምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ የቦረና ዞን፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም፣ መካከለኛው፣ የሰሜንና የምዕራብ ጎንደር፣ የባሕር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል።


የቤንሻንጉል ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ሁሉም የሱማሌ ክልል ዞኖችም መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸውም አስታውቋል።

በተጨማሪም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ጎንደር፣ የሰሜን ወሎ እና ምሥራቅ ጎጃም፣ የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ሐረሪ እና ድሬዳዋ በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል ሲል የብሔራዊ ሚትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታውቋል።

# "የሠራነው ጠንካራ ሥራ ተማሪዎቻችን በ12ኛ ክፍል ፈተና ስኬታማ እንዲሆኑ አስችሏል"

- ትምህርት ቤቶች

**በዳግማዊት ግርማ**



አዲስ አበባ፡- ተማሪዎችና መምህሮቻቸው የሠሩት ጠንካራ ሥራ በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤታማ እንዲሆኑ እንዳስቻላቸው በፈተናው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ትምህርት ቤቶች ገለጹ። ትምህርት ቤቶቹ ባለሀብቶች አይናቸውን ወደ ዘርፉ በማዞር ድጋፍ እንዲያደርጉም ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

የትምህርት ቤቶቹ ኃላፊዎች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ከፈተናው መሰጠት በፊት ያደረጉት የቅድመ ዝግጅት ሥራ ተማሪዎቻቸው ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ውጤት ስኬታማ እንዲሆኑ አስችሏል።

ያስፈተናቸውን 53 ተማሪዎች ሙሉ ለሙሉ ማሳለፍ የቻለው የደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ በለጠ ኃይሌ እንደተናገሩት፤ ባልተሟሉ መሠረተ ልማቶችም ውስጥ ሆኖ የአዳሪ ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በሙሉ ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ችለዋል።

እንደ አቶ በለጠ ንግግር፤ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን ለትምህርት ልዩ ትኩረት ሰጥተው በርትተው በመሥራታቸው የተመዘገበው ከፍተኛ ውጤት ተመዝግቧል።

በትምህርት ቤቱ ትልቁ ውጤት 646 መሆኑን የተናገሩት ርዕሰ መምህሩ ዝቅተኛው 439 መሆኑን በመግለጽ 16 ተማሪዎች ከስድስት መቶ በላይ ማምጣታቸውን ገልጸዋል፤ አራት ተማሪዎች ብቻ አራት መቶ ቤት ማምጣታቸውንም ጠቅሰዋል።

በተማሪዎችና መምህራን መካከል ያለው ግንኙነት አወንታዊ መሆኑን የገለጹት አቶ በለጠ፤ በትምህርት ቤቱ የሚያስተምሩ መምህራን በሙሉ ተመርጠው የገቡና በጠቅላላ ከሁለተኛ ዲግሪ በላይ ያላቸው ስለመሆናቸውም አስረድተዋል።

ትምህርት ቤቱ ደረጃውን ያላሟላ መሆኑን የተናገሩት አቶ በለጠ፤ ችግሮች ቢኖሩም ትምህርት ቤታቸው ችግሮችን ተቋቁሞ ባልተሟላ መሠረተ ልማት ውስጥ ጠንክሮ መሥራት ከተቻለ ጥሩ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ምስክር መሆን ስለመቻሉ ጠቅሰዋል።

ርዕሰ መምህሩ ባለሀብቶች ዓይናቸውን ወደ ዘርፉ በማዞር ድጋፍ እንዲያደርጉም ጥሪያቸውን በማቅረብ ማኅበረሰቡም ትምህርትን በመደገፍና በመረባረብ ለተሻለ ውጤት መትጋት ይገባዋል ብለዋል።

በስልጤ ዞን የሚገኘውና ያስፈተናቸውን ተማሪዎች በሙሉ ማሳለፍ የቻለው ሀይራንዚ አዳሪ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ አብዱልመጂድ ኑረዲን በበኩላቸው፤ የተሠራው ጠንካራ ሥራ ስላመጣላቸው ጥሩ ውጤት ጠቅሰዋል።

ትምህርት ቤቱ 86 ወንድና 26 ሴት ተማሪዎችን በድምሩ 112 ተማሪዎችን ማስፈተኑን የተናሩት ርዕሰ መምህሩ፤ ያስፈተናዎችን ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ማሳለፍ መቻሉን ገልጸዋል። ትልቁ ውጤትም 624 ሆኖ መመዝገቡን በመግለጽ አነስተኛው ደግሞ 351 መሆኑን ገልጸዋል።

ትምህርት ቤቱ በ2014 ተማሪዎችን ሲያስፈትን ሦስት ያህል ተማሪዎች ማለፍ ያለመቻላቸው ቁጭት ፈጥሮባቸው መከረሙን የገለጹት አቶ አብዱልመጂድ፤ ይህ ክስተት ለዘንድሮ እንዲጠነክሩ ማስቻሉን ገልጸዋል።

ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡት አስር ትምህርት ቤቶች አንዱ መሆን የቻለውና ከአንድ ተማሪ ውጭ ሁሉንም ያሳለፈው የአዳማ አዳ አዳሪ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ አበበ ዘውዴም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ትምህርት ቤታቸው ለተከታታይ ስድስት ዓመታት ተማሪዎቹን ሙሉ በሙሉ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማሳለፍ መቻሉን ያወሱት ርዕሰ መምህሩ፤ ዘንድሮ በፈተናው ወቅት የአባቷን መታመም የሰማች አንድ ልጅ ብቻ ውጤቷ ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

ተማሪዎች ላይ ሰፊ የሆነ ቅድመ ዝግጅት መደረጉን የገለጹት አቶ አበበ፤ ሰፊ የጥናት ሰዓት በመስጠት ተማሪዎች ከፈተናው በፊት ሦስት የሞዴል ፈተናዎችን ስለመውሰዳቸውም ተናግረዋል።

ተማሪዎች ከትምህርታቸው በተጨማሪ አንድ ላይ እንዲያጠኑ እንዲተጋገዙ በማድረግ የመረዳዳት ባሕል እንዲያዳብሩ ይደረጋል ብለዋል።

ተማሪዎች የሚያጋጥማቸውን ሥነልቦናዊ ችግሮች ለመቋቋም እንዲያስችላቸው ሥራዎች መሠራታቸውን የገለጹት አቶ አበበ፤ ከወላጅ የመለየት ስሜት እንዳይሰማቸው አንድ መምህር በወላጅነት እንደሚሰጣቸውም ገልጸዋል።

# ማኅበራቱ ከስድስት ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ተጠቃሚ እያደረጉ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ 375 የሲቪክ ማኅበራት ከስድስት ሚሊዮን በላይ ሕዝብን ተጠቃሚ እያደረጉ መሆኑን ክልሉ አስታወቀ።

የላይፍ ወተር ኢንተርናሽናል ግሎባል ሊደርሽፕ ዓመታዊ ውይይት በተካሄደበት ወቅት የኦሮሚያ ክልል የፋይናንስና ኢኮኖሚ ትብብር የግብረ ሠናይ ድርጅቶች ቡድን መሪ አቶ ደሬሳ ደገፋ እንደተናገሩት፤ በኦሮሚያ ክልል 375 የሚጠጉ የሲቪል ማኅበራት ከ700 በላይ ፕሮጀክቶችን በመያዝ በሕጋዊ መንገድ ተመዝግበው እየሠሩ ይገኛል።

ሲቪክ ማኅበራቱ በ29 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር አጠቃላይ በጀት ከስድስት ሚሊዮን በላይ ሕዝብን በተለያዩ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ እያደረጉ መሆኑን አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ደሬሳ ገለጻ፤ ሲቪክ ማኅበራቱ በጤና፣ በትምህርት፣ በንጹሕ ውሃ መጠጥ አቅርቦትና በተለያዩ የልማት ዘርፎች ተሰማርተዋል።

ሲቪክ ማኅበራቱ የውሃ ወለድ በሽታዎችን በመቀነስ ተገቢውን የንጽሕና አጠባበቅ ሥራዎችን በማስፋፋትና በተለያዩ መስኮች ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ያደረጉ ሥራዎችን ማከናወናቸውን አስረድተዋል።

ለአብነት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን አስተዳደር ዶዶላ፣ ነንሴቦ እና ኮኮሳ ወረዳዎች ላይፍ ወተር ኢንተርናሽናል ግብረ ሠናይ ድርጅት ዘላቂ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ፕሮጀክቶችን በመተግበር ጤናን ለማሻሻል፣ የውሃ ወለድ በሽታዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ሥራ እያከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።



አቶ ደሬሳ ደገፋ



አቶ በላይ ደሬሳ

በፌደራል ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት የግብረ ሠናይ ድርጅቶች ድጋፍና አገልግሎት ኃላፊ አቶ በላይ ደሬሳ በበኩላቸው፤ የሕዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሚና ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

መንግሥት በሁሉም ዘርፍ የሚገኙ የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ለመደገፍ ዝግጁ መሆኑን የተናገሩት አቶ በላይ፤ ከውጭ ሲቪክ ማኅበራት በተጨማሪ ሀገር በቀል ለሆኑ የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች አቅም ማጎልበት ላይ እንዲሠሩ እንፈልጋለን ብለዋል፡፡

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ሚና ለማሳደግ ተቋማችን እያደረገልን ያለውን ድጋፍ ከመቼውም በበለጠ አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

የላይፍ ወተር ኢንተርናሽናል ግሎባል ሊደርሽፕ ዓመታዊ ውይይት ከመስከረም 28 እስከ ጥቅምት አምስት ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚቆይ ታውቋል። በመድረኩ የተቋሙ የሦስት ዓመት ስትራቴጂካዊ ዕቅድ የሚቀርብ ሲሆን ኢትዮጵያን ጨምሮ የፕሮግራሙን ተጠቃሚ ሀገራት የ2024 ዓመታዊ በጀት እንደሚያፀድቅ ይጠበቃል።



## በከተማው የጤና መድሕን ተጠቃሚዎችን ቁጥር በ10 በመቶ ለመጨመር እየተሠራ ነው

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድሕን ተጠቃሚ ቁጥር በ10 በመቶ ለመጨመር እየተሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድሕን የነባር አባላት እድሳት እና የአዲስ አባላት ምዝገባ ከጥቅምት 1 እስከ ኅዳር 30 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚደረግ በትናትናው እለት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ በዚሁ ወቅት እንደገለፁት፤ በከተማው ያለውን የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድሕን ተጠቃሚ ቁጥር በ10 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡

በዚህም በ2015 ዓ.ም 2 ሚሊዮን 2 ሺህ 130 የሚሆኑ የከተማው ነዋሪዎች የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድ ሕን ተጠቃሚ የነበሩ ሲሆን፤ በ2016 ዓ.ም ቁጥሩን 10 በመቶ በመጨመር 2 ሚሊዮን 200 ሺህ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ለዚህም የከተማ አስተዳደሩ በ2015 ዓ.ም ለማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድሕን የሚውል ከ400 ሚሊዮን ብር በላይ ድጎማ ያደረገ መሆኑን አስታውቀው፤ በዚህ ዓመት እስከ 600 ሚሊዮን ብር ድጎማ ሊደረግ እንደሚችል ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

በዚህም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሙሉ በሙሉ ድጎማ እና በከፊል ድጎማ በማድረግ በጤና መድሕን አባልነት ተመዝግበው የጤና አገልግሎቱን እንዲያገኙ እየተደረገ ነው ብለዋል ፡፡

በዘንድሮ የነባር አባላት ሙሉ ለሙሉ እድሳት እንዲያደርጉ ይሠራል ያሉት ኃላፊው፤ ለምዝገባ በሚመጡበት ወቅትም የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ እና የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድሕን የአባልነት ካርድ መያዝ እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡

በመሆኑም በ2016 የነባር የአባልነት ክፍያ አንድ ሺህ ብር እንዲሁም እድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆናቸው ልጆች 7 መቶ 50 ብር መክፈል የሚጠበቅባቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አዲስ አባላት የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ፣ የአባልነት መመዝገቢያ ሁለት መቶ ብር፣ የአባልነት ክፍያ አንድ ሺህ ብር እንዲሁም እድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ልጆች ካሉ ለእያንዳንዳቸው 7 መቶ 50 ብር በመያዝ መመዝገብ የሚችሉ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

እራስን እና ቤተሰብን ካልታሰበ ወጪ ብሎም ጤናን በወቅቱ ለመከታተልና ለመጠበቅ መመዝገብ እንደሚገባ የገለጹት ዶክተር ዮሀንስ፤ ምዝገባውን በተጠቀሰው ቀን በሚኖሩበት ወረዳ በሚገኝ ጤና ጣቢያ በመሄድ ማካሄድ እንደሚችሉ አስታውቀዋል፡፡

# የሰንደቅ ዓላማ ቀን ለ16ኛ ጊዜ በተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- የዘንድሮ የሰንደቅ ዓላማ ቀን "የሰንደቅ ዓላማችን ከፍታ ለሕብረ-ብሔራዊ አንድነታችንና ለሉዓላዊነታችን ዋስትና ነው" በሚል መሪ ቃል በመጪው ሰኞ ለ16ኛ ጊዜ እንደሚከበር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስታወቀ፡፡

ምክር ቤቱ ጥቅምት 05 ቀን 2016 ዓ.ም. በሀገራችን ለአስራ ስድስተኛ ጊዜ ሀገራዊ ወቅታዊ ሁኔታን በዋጀ መልኩ፤ ከሰንደቅ ዓላማ መርሆች ጋር ተገናዝቦ እና ሀገራዊ ሪፎርሙን በሚያስቀጥሉ ውይይቶች ታጅቦ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መሪነት በመላ ሀገሪቷ ይከበራል ብሏል፡፡

ምክር ቤቱ ጥንት እናት እና አባቶቻችን የሀገራችንን ዳር ድንበር ደፍሮ የሀገር ነፃነትና ሉዓላዊነትን ለመውሰድ በየዘመናቱ የመጣን የውጭ ወራሪ ኃይል መክተው በከፈሉት የሕይወት መስዋዕትነት ነፃነታችን ተጠብቆ እና ሰንደቅ ዓላማችን ተገቢውን ክብር ይዞ ከትውልድ ትውልድ ተላልፎ እነሆ ከአሁኑ ትውልድ ደርሷል ብሏል፡፡

የበዓሉ መከበር ለሕብረ-ብሔራዊ አንድነታችን እና ለሉዓላዊነታችን መጠናከር መነቃቃትን ለመፍጠር ትልቅ ትርጉም የሚኖረው ሲሆን፤ ለሀገር ክብር እና ጥቅም ሁላችንም የበኩላችንን ለመወጣት በሰንደቅ ዓላማ ፊት ዳግም ቃላችንን የምናድስበት ዕለት ይሆናል ብሏል ምክር ቤቱ፡፡

በዓሉ፤ በፌዴራል የመንግሥት ተቋማት፣ በክልሎች እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች፣ በመከላከያ ሠራዊት ካምፖች እንዲሁም በኤምባሲዎች እና የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች በተመሳሳይ ሰዓት ከረፋዱ 4 ሰዓት ተኩል ላይ በደማቅ ሁኔታ እንደሚከበር ምክር ቤቱ አስታውቋል፡፡

የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀን በዓል በየዓመቱ ጥቅምት ወር በገባ የመጀመሪው ሰኞ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንደሚከበር በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 863/2006 አንቀጽ 2 ተደንግጎ ይገኛል ሲል የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስታውቋል፡፡

# የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ የማቋቋም ሥራ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ይጠይቃል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ የማቋቋም ሥራ በመንግሥት ብቻ የሚሳካ ባለመሆኑ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንደሚጠይቅ የብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን ገለጸ፡፡

ብሔራዊ የተሐድሶ ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡

ስምምነቱን የብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ተወካይ ዋና ዳይሬክተር ሐና ወልደገብርኤል ናቸው፡፡

በወቅቱ የብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ እንደተናገሩት፤ በዓለም ዙሪያም ሆነ በኢትዮጵያ ደረጃ ቀደም ሲል የነበሩ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ የማቋቋም ሥራ በመንግሥት ብቻ የሚሳካ ባለመሆኑ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ የማቋቋም ሥራ የኅብረተሰቡን፣ የሲቪክ ማኅበራትን፣ የተለያዩ ረጂ ተቋማትና የሌሎች አካላትንም ንቁ ተሳትፎ እነደሚጠይቅ አመላክተዋል።

ኮሚሽኑ የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ የማቋቋም ሥራን እንዲያከናውን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክርና የተለያዩ ሥራዎችን ሲያከናውኑ መቆየታቸውን ተናግረዋል።

ቀደም ባሉ ጊዜያት ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ጋር የኮሚሽኑን ሥራ ለማሳካት የሚረዳ ገንቢ ውይይት መደረጉንም አስታውሰዋል።

የቀድሞ ተዋጊዎች ምርታማ ሕይወት እንዲኖራቸው፣ እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ሰላማዊ ወደሆነ የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲያስገቡና በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ የማቋቋም ሥራ ወሳኝነት እንዳለው ገልጸዋል።



**አምባሳደር ተሾመ ቶጋ እና ሐና ወልደ ገብርኤል**

በዚህ ረገድ ከኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የተደረገው ስምምነት ትልቅ ጅማሬ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በስምምነቱ መሠረት የቀድሞ ተዋቂዎችን ለማቋቋም በጋራ የሚከናወኑ ሥራዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

በቀጣይ በስምምነቱ መሠረት እቅዶች ተዘጋጅተው ወደሥራ እንደሚገባ ተናግረው፤ ስምምነቱ ተግባራዊ ሆኖ የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያመጣ በቁርጠኝነት መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ተወካይ ዋና ዳይሬክተር ሐና ወልደገብርኤል በበኩላቸው፤ የተለያዩ ሀገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ከግጭት ወደዘላቂ ሰላም የሚደረገው ሽግግር የበርካታ አካላትን ትብብር ይጠይቃል።

በኢትዮጵያም ዘላቂ የሰላም ግንባታ ለማከናወን በሚደረገው ጥረት የቀድሞ ተዋጊዎች ወደ ቀድሞ ሕይወታቸው የመመለስ ሥራው ውጤታማ እንዲሆን በጋራ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

የቀድሞ ተዋጊዎች ወደ ቀድሞ ሕይወት የመመለስ ሂደቱ ስኬታማ እንዲሆን ምክር ቤቱ የሚጠበቅበትን ሚና እንደሚወጣ አስታውቀዋል፡፡

ስምምነቱ የቀድሞ ተዋጊዎች ከማኅበረሰቡ ጋር በዘላቂነት እንዲቀላቀሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን፣ የአቅም ግንባታ፣ የመረጃ ልውውጥ፣ የምርምርና ዕውቀት ስርፀት፣ የሀብት ማሰባሰብና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመሥራት እንደሚያስችል አመላክተዋል።

የሲቪል ማኅበረሰብ ዘርፉ የኮሚሽኑን ሥራ በመደገፍ የሚያከናውነውን አስተዋፅዖ ለማጠናከር የተለያዩ መድረኮች እንደሚዘጋጁ ተገልጿል።

ዜና

# የወንጪ
## ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት በዚህ ወር መጨረሻ ይመረቃል

ሳምራዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ከሦስት ዓመታት በፊት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት 'ገበታ ለሀገር' በሚል ስያሜ ከተጀመሩ ሜጋ ፕሮጀክቶች መካከል በኦሮሚያ ክልል፤ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ እና ምዕራብ ሸዋ ዞኖች ውስጥ የተጀመረው የወንጪ-ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት ተጠናቅቆ በዚህ ወር መጨረሻ ይመረቃል ተብሎ እንደሚጠበቅ የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ገለጹ፡፡

አስተባባሪው አቶ ዳባ ጂንፌሳ ሰሞኑን ከበሪሳ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለመጠይቅ እንደተናገሩት፣ የፕሮጀክቱ መጀመሪያ ምዕራፍ ላለፉት ሁለት ዓመት ከአምስት ወራት ሲሠራ የቆየ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በመጨረሻው ደረጃ ላይ እንደሚገኝና በያዝነው ወር መጨረሻ ተመርቆ አገልግሎት እንደሚጀምር ተናግረዋል።

የወንጪ-ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ሜጋ ፕሮጀክት የመጀመሪያ ምዕራፍ በሁለት ዓመት ከስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በአራት ቢሊዮን ብር ይጠናቀቃል ተብሎ የታቀደ ሲሆን በተባለው ጊዜና በጀት በመጠናቀቅ ላይ እንደሚገኝም አስተባባሪው ገልፀዋል፡፡

ሥራው ሕዝብ ከተባበረ መሥራት የማይችለው ነገር እንደሌለና በቁርጠኝነትና በትኩረት ከተሠራ ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜ መጨረስ እንደሚቻል መልካም ተሞክሮ የተወሰደበት መሆኑንም ተናግረዋል፡፡



**አቶ ዳባ ጂንፌሳ**

እንደ አቶ ዳባ ገለፃ፣ ፕሮጀክቱ በ2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ወጭ የተገነባ ከወንጪ ሐይቅ እስከ ደንዲ ሐይቅ የሚረዝም 42 ኪ.ሜ ደረጃውን የጠበቀ፤ ሰፊና የማራቶን ትራክን ያካተተ መንገድ፣ በ1ነጥብ5 ቢሊዮን ብር በላይ የተገነቡ የተለያዩ ሱቆች፣ ባሕላዊና ዘመናዊ ሬስቶራንቶች፣ ባንክ፣ ከ500-700 ሰዎች የሚይዝ አንፊ ቲያትር፣ የወንጪ ማርና የተለያዩ ምርቶች መሸጫ ቦታ፣ ፎቶ መነሻ ስፍራዎችና እጅግ ማራኪ መግቢያ በር ያካተቱ አራት ደረጃቸውን የጠበቁ የመዝናኛ ስፍራዎችን የያዘ ነው፡፡

እንዲሁም በሀገራችን ባልተለመደ መልኩ ከመስታወት የተሠራ ዋሻ ላይ ቆሞ መጎብኘት የሚያስችል ቦታን፣ 69 ሜትር የሚረዝም ተንቀሳቃሽ የብረት ድልድይ፣ በአንድ ጊዜ ከ200 በላይ ተሽከርካሪዎችን ማስተናገድ የሚያስችል መኪና ማቆሚያ፣ ሎጆችና የተለያዩ የመዝናኛ መጓጓዣ አማራጮችን የያዘ መሆኑን አብራርተዋል።

የወንጪ-ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት የአካባቢውን መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥና ተፈጥሮዓዊ ይዘት ሳይለውጥ በመሠራቱ ከሌሎች ገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ልዩ እንደሚያደርገው አስተባባሪው ተናግረው፣ የሀሳቡ ባለቤት የሆኑት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ባስቀመጡት አቅጣጫ መሠረት ሙሉ ወጪው በሕዝብ መሸፈኑን ገልፀዋል።

ፕሮጀክቱን ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ የፕሮጀክቱ ተቆጣጣሪ የመከላከያ ሚኒስትሩ ዶክተር አብረሃም በላይ እና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ በቅርበትና በትኩረት ሲከታተሉና ሲደግፉ መቆየታቸውን አቶ ዳባ ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱን በበላይነት በኮንትራት ተረክቦ የሚሠራው አካልም ዝናባማ ለሆነው ለአካባቢው የአየር ንብረት። በአካባቢው ለነበረው የሰላም ሁኔታና በግንባታ እቃዎች ዋጋ መናር ሳይበገር ሌት ተቀን እየሠራ እውን ማድረጉን አንስተዋል። በዚህም ማንኛውንም ሥራ ለማከናወን ምክንያት መደርደር ተቀባይነት እንደሌለው ልምድ የተወሰደበት ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡

በፕሮጀክቱ ግንባታ ከሁለት ሺህ በላይ ዜጎች የሥራ እድል የተፈጠረላቸው ሲሆን፡ ለተባለለት አገልግሎት ሲበቃም 700 የሚሆኑ የአካባቢው ተወላጆች የሥራ ዕድል እንደሚያገኙና ይህም በየጊዜው እየጨመረ እንደሚሄድ አስተባባሪው ተናግረዋል።

የፕሮጀክቱ መጠናቀቅም ለአካባቢው ብቻ ሳይሆን ለክልሉ ብሎም ለሀገር ትልቅ ፋይዳ ያለውና ለቱሪዘም ዘርፉ ትልቅ መነቃቃት እንደሚፈጥር ጠቁመዋል።

ይህን ሙሉ በሙሉ በሕዝብ ተሳትፎ የተገነባውን ፕሮጀክት ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ሊጠብቀውና ሊንከባከበው እንደሚገባ ጠቁመው፣ የመጎብኘት ባሕልን በማዳበርም ቱሪዝምን ማበረታታት እንደሚገባ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

እንደ አስተባባሪው ገለፃ በዚህ ወር መጨረሻ ይከናወናል ተብሎ ለሚጠበቀው የምረቃ መርሐ ግብር ኮሚቴ ተዋቅሮ እንቅስቃሴ የተጀመረ ሲሆን ሁነቱም ከምርቃት በፊትና በኋላ ለአንድ ወር የሚቆይ እንደሚሆን አንስተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)ያስጀመሯቸው የገበታ ለሃገር ፕሮጀክቶች የወንጪ-ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም፣ ኮይሻና ጎርጎራ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

## "የኮሚሽኑ ትኩረት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሁኔታ አለ፤ መግባባት ላይ ያልደረስንባቸው ትርክቶችም አሉ። ሆነ ተብለውም ለተለየ ዓላማ የሚሰራጩ ጉዳዮችም አሉ፤ እነዚህና መሰል ነገሮች ተደማምረው አሁን ለተፈጠረው ችግር አስተዋፅዖ አበርክተዋል ብለን እናምናለን ሲሉ ቃል አቀባዩ ገልጸዋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ የፖለቲካ ቀውስ የፈጠራቸው አለመግባባቶችም ሆኑ አሉታዊ የሆኑ ትርክቶች እንደ ሀገር ከምክክር ኮሚሽኑ ጋርም ተያይዞ ተመካክረን ልንሻገራቸው ከምንችላቸው ሐቆች መካከል ናቸው። ስለዚህ በመጀመሪያ የፖለቲካ ሁኔታችን መሻሻልና መለወጥ አለበት። ሁለተኛው ደግሞ ታሪኮቻችን ላይ ለመግባባት ጥረት መደረግ አለበት። እንዲሁም በተዛባ ሁኔታ የሚፈጠሩ ትርክቶች የሆነ ቦታ ላይ ተገትተው መልክ መያዝ መቻል አለባቸው። እነዚህ በተዛባ መልኩ የተፈጠሩ ትርክቶች ትናንት ነበሩ፤ ዛሬም አሉ፤ መፍትሔ ካልተገኘላቸው ደግሞ ነገም ይቀጥላሉ ማለት ነው፡ ስለዚህ ሥራዎች የሚሠሩት ከእንደዚህ አይነት እሽክርክሪት ውስጥ ለመውጣት ነው።

ከዚህ አኳያ ምናልባት በምክክር ኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ እንደዓላማ ከተቀመጡ ነገሮች አንዱ እነዚህን ሁኔታዎች መቀየር ነው። አንዱ በምክክር ሒደቱ እንደርስበታለን ተብሎ የተቀመጠው ዓላማ መተማመን የሰፈነበት እና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት የመፍጠር ጉዳይ ነው በማለት ተናግረዋል። በተጨማሪም ሲንከባለሉ የመጡ ውስጣዊ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚያስችል የፖለቲካ ሥርዓት ማዳበር አንዱ ከምክክሩ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው ብለዋል።

እርሳቸው እንደተናገሩት፤ የኮሚሽኑ እንቅስቃሴ አሁናዊ ምልክቶችን ተከትሎ መሥራት ሳይሆን መሠረታዊ ችግሮችን በመለየት ፈውስ ማምጣት ነው። ታክሞ በማገገምና በመፈወስ መካከል ልዩነት አለ። ስለዚህ ለሁነኛ መፍትሔ መሥራት የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህም እንደሀገር ካጋጠመ ችግር ለመውጣት የሚያስችል ነው።

ችግሮቹ በምክክሩ ሒደት አጀንዳ ሆነው ይመጣሉ ብለን እንጠብቃለን። አጀንዳ ሆነው ከመጡ ምክክር ይደረግባቸዋል። ስለዚህ በምክክር ሒደቱ ደግሞ እነዚህ ጉዳዮች ወደመግባባት ይመጣሉ ተብለው ይጠበቃሉ። የእኛ ተስፋ ጉዳዮቹ ላይ ምክክር በማድረግ ከእነዚህ አዙሪት ውስጥ የምንወጣበትን ነገር ሕዝቡ መክሮ እዛ ደረጃ ላይ ይደርሳል የሚል ነው ብለዋል።

## ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የመንገዶች የአገልግሎት ደረጃ ጥናትና የባለድርሻ አካላት ሚና

የመንገድ መሠረተ ልማት ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት ወሳኝ ሚና የሚጫወት እንደመሆኑ መጠን የሚገነቡት መንገዶች ጥራታቸውን የጠበቁና ረጅም የአገልግሎት እድሜ ሊኖራቸው ይገባል:: የሚገነቡ መንገዶች አገልግሎት በሚገነቡበት ዓላማ መሠረት የሚለያዩ ሲሆን ስያሜያቸውም በዚሁ መሠረት ይለያያል:: በዚህ ሳምንት እትማችን በኢትዮጵያ የተካሄዱ የመንገዶች የአገልግሎት ደረጃ ጥናት፣ የተገኙ ውጤቶችንና በውጤቱ መሠረት የተቀመጡ የመንገድ ስያሜዎችን እንመለከታለን::

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር እ.ኤ.አ 1997 የፌዴራል መንገዶችን የአገልግሎት ደረጃ /Functional Classification/ የሚያወጣ ጥናት የውጪ አማካሪ ድርጅት በመቅጠር ማካሄዱ ይታወቃል:: ጥናቱ በወቅቱ የነበረውን 19 ሺህ 720 የፌዴራል መንገዶች በአምስት ደረጃዎች በመለየት አስቀምጧል:: እነዚህም አውራ(Trunk)፣ አገናኝ (Link)፣ ዋና መዳረሻ(Main access)፣ ሰብሳቢ(Collector) እና መጋቢ(Feeder) በመባል የተለዩ ናቸው::

በዚህ መሠረት ጥናቱ 3ሺህ 861 ኪሎ ሜትር መንገዶችን አውራ(Trunk)፣ 5ሺህ 421 ኪሎ ሜትር መንገዶችን አገናኝ (Link)፣ 4ሺህ 681 ኪሎ ሜትር መንገዶችን ዋና መዳረሻ(Main access)፣ 2ሺህ 536 ኪሎ ሜትር መንገዶችን ሰብሳቢ(Collector) እና 3ሺህ 221 ኪሎ ሜትር መንገዶችን መጋቢ(Feeder) እንደሆኑ አስቀምጧል::

ጥናቱ አውራ መንገዶች፣ አገናኝ መንገዶች እና ዋና መዳረሻ መንገዶች ተብለው ደረጃ የወጣላቸውን መንገዶች የፌዴራል መንግሥት ማለትም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እንዲያስተዳድራቸው ምክረ ሀሳብ አቅርቧል:: በተጨማሪም ጥናቱ ሰብሳቢ(Collector) እና መጋቢ(Feeder) በመባል ደረጃ የወጣላቸው 5ሺህ 757 ኪሎ ሜትር አስፋልትና ጠጠር መንገዶች የክልል መንግሥታት እንዲያስተዳድሯቸው ሀሳብ አቅርቧል:: እስከ 2019/2020 እ.ኤ.አ ድረስም በጥናቱ ላይ በተቀመጠው ምክረ ሀሳብ መሠረት ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል::

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር(ኢመአ) እ.አ.አ በ1997 የተጠናውንና እስከ 2019/2020 ተግባራዊ ሲደረግ የቆየውን የመንገዶችን የአገልግሎት ደረጃ አወሳሰን በዓለም አቀፍ የማማከርና የቁጥጥር አገልግሎት በድጋሚ እንዲጠና አድርጓል:: አማካሪው ድርጅት ሁሉንም የፌዴራል መንገዶች በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ሥር እንዲተዳደሩና የፍጥነት መንገድ፣ አውራ መንገድ፣ ዋና መዳረሻ መንገድ፣ መንገዶች ሰብሳቢ፣ መጋቢ እና የገጠር መንገዶች ተብለው እንዲጠሩ ሀሳብ አቅርቧል:: ዋና መዳረሻ መንገድ፣ መንገዶች ሰብሳቢ እና መጋቢ መንገዶች በሚል የተሰየሙ የገጠር መንገዶች በገጠር መንገዶች ኤጀንሲ ሥር እንዲተዳደሩ ሰጥቷቸዋል::

የፍጥነት መንገድ እና አውራ መንገድ በመባል የሚጠሩት መንገዶች አዲስ አበባን ከጎረቤት ሀገራት እና ወደቦች ጋር የሚያገናኙ እና አዲስ አበባን ከክልል ዋና ከተሞች እንዲሁም ከሌሎች ከፍተኛና መካከለኛ ከተሞች ጋር የሚያገናኙ መንገዶች ናቸው:: አገናኝ መንገድ የምንላቸው ደግሞ የዞን አስተዳደር ከተሞችን ከክልሎች እና ከመካከለኛ የከተማ ማዕከላት የሚያገናኙ ሲሆኑ ረዥም እና ዙሪያ ጥምጥም ጉዞን የሚያስቀሩና ከተሞችን በአቋራጭ የሚያገናኙ መንገዶች ናቸው::

ዋና መዳረሻ መንገዶች ለልማት ሊውል የሚችል ሰፊ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ከሚገኝባቸውና ከአቅራቢያቸው በሚገኙ ወንዞች በመስኖ ሊለሙ ከሚችሉ አካባቢዎች፣ የምግብ ሰብል(Cash Crops) በከፍተኛ ሁኔታ ትርፍ ከሚመረትባቸው አካባቢዎች፣ እምቅ የማዕድን ሃብት ከሚገኙባቸው ቦታዎች እንዲሁም ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ከሚገኝባቸው የገጠር አካባቢዎች ጋር የሚያገናኙ መንገዶች ናቸው:: ሰብሳቢና መጋቢ በመባል የተለዩት መንገዶች ደግሞ በዋናነት የወረዳ ማዕከላትን ከዞን ማዕከላት ጋር የሚያገናኙ፣ አጎራባች ወረዳዎችን እርስበርስ የሚያገናኙና የወረዳ ማዕከልን በወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች መለስተኛ ከተሞች(ቀበሌዎች) ጋር የሚያገናኙ መንገዶች ናቸው::

የመንገዶች የአገልግሎት ደረጃ አወሳሰን እንደሚያመላክተው የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር(ኢመአ) ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን እንደፍጥነት መንገዶች፣ አውራ መንገዶችና አገናኝ መንገዶች ብቻ ሳይሆን አነስተኛ ደረጃ ያላቸውንም እንደዋና መዳረሻ መንገዶች፣ ሰብሳቢ እና መጋቢ መንገዶችንም በባለቤትነት ያስተዳድራል:: በደረጃ አወሳሰኑ መሠረት የገጠር መንገዶችም እንደ ዋና መዳረሻ መንገዶች፣ ሰብሳቢ እና መጋቢ መንገዶች ያሉትን በባለቤትነት በስሩ ያስተዳድራል::

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር(ኢመአ) ሆነ የገጠር መንገድ ኤጀንሲዎች ዋና መዳረሻ መንገዶች እና ሰብሳቢና መጋቢ መንገዶችን በባለቤትነት ማስተዳደራቸው በሁለቱ ተቋም መካከል የኃላፊነት መደራረብ እንዳለ የሚያሳይ ነው:: ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር(ኢመአ) እንደ ዋና መዳረሻ መንገዶች እና ሰብሳቢና መጋቢ መንገዶችንም በመገንባትና በማስተዳደር ሥራ ላይ ተሰማርቶ ስለነበር ነው::

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር(ኢመአ) ዋነኛ ሥራ እምቅ የኢኮኖሚ ልማት ሀብት ያለባቸውን ቦታዎች፣ ከፍተኛ ትርፍ የምግብ ሰብል አምራች አካባቢዎች እና የወረዳ ዋና ከተሞችን ከዞን ዋና ከተሞችና ከሌሎች ቦታዎች ጋር የሚያገናኙ መንገዶችን ማልማትና ማስተዳደር ነው:: ይህንን የኃላፊነት መደራረብ ለመቅረፍ እንዲቻል ጥናቱ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር(ኢመአ) ራሱን ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን እንደ ፍጥነት መንገዶች፣ አውራ መንገዶች እና አገናኝ መንገዶችን ማስተዳደር ላይ እንዲወስን እና አነስተኛ ደረጃ ያላቸውን እንደ ዋና መዳረሻ መንገዶች፣ ሰብሳቢ እና መጋቢ መንገዶችን ለገጠር መንገዶች ኤጀንሲዎች እንዲያስተላልፍ ሀሳብ አቅርቧል::

የገጠር መንገዶች ኤጀንሲዎች ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን የገጠር መንገዶች መገንባት ብቻ ሳይሆን ነባሮቹን ከፍተኛና አነስተኛ ደረጃ ያላቸውን የጠጠር መንገዶች ወደ አስፋልት ደረጃ የማሳደግ ሥልጣን ሊሰጣቸው ይገባል:: ስለሆነም የገጠር መንገዶች ኤጀንሲዎች ይህንን የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ይችሉ ዘንድ ተቋማዊ አቅም ግንባታ ያስፈልጋቸዋል:: ለዚህም የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር(ኢመአ) እገዛ ያስፈልጋቸዋል::

የአማካሪው ድርጅት ባቀረበው ሀሳብ መሠረት በ2019 እና በ2020 ከአውሮፓ ኅብረት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የገጠር መንገዶች ኤጀንሲዎችን አቅም ግንባታ ለማጠናከር በአዲስ መልክ እንዲዋቀሩ ሀሳብ ቀርቦ ነበር:: አዲሱ ድርጅታዊ መዋቅር በኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት፣ በመንገድ ሀብት ማኔጅመንት እና በሌሎች ጉዳዮች የተለዩትን ክፍተቶች መቅረፍ የሚያስችል ነው:: አማካሪ ድርጅቱ ለገጠር መንገዶች ኤጀንሲዎች፤ በርካታ መሐንዲሶችና የሌሎች ባለሙያዎችን ቅጥር ማከናወን እንዲችሉ ተደርገው እንዲደራጁ ሀሳብ አቅርቧል:: በዚህም መሠረት ለገጠር መንገዶች ኤጀንሲዎች በቀረበው አደረጃጀት መሠረት ባለሙያዎችን በመቅጠር ሂደት ላይ ይገኛሉ:: ይህም አቅማቸውን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል::

አድራሻ Facebook: - Ethiopian Roads Administration Telegram:-ERA ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት

የውስጥ ገጾች



## ‹‹በዚህች አገር መሣሪያ የመያዝ ሙሉ ኃላፊነት ያለው መንግሥት ነው››

አቶ ግርማ ሰይፉ
የኢዜማ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል

ገጽ 6



በታዳጊዎቹ ላይ ግብረሰዶም ወንጀል የፈፀመው ግለሰብ አስተማሪ ቅጣት

ገጽ 19



ካንሰርን - በአሸናፊነት

ገጽ 20

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አፍሪቃዊቷ መልኅቅ

# ኪነ-ሂስን ባሕል ማድረግ ፤ ለኪነ-ጥበብ እድገት

ሂስ፤ በልኬት መስፈርት አማካኝነት፣ አንድን ሥነ ጥበባዊ ሥራ የሚተነትን፣ የሚያስተዋውቅ፣ አድናቆትን የሚያለማምድ የሐተታ ዓይነት ነው ። ኪነ-ጥበባዊ ልምምድን ወደ ዕውቀት የሚያሸጋግር ምሑራዊ ተግባር እንደሆነም ይገለጻል ። ኪነ - ጥበብ እና ሂስ የማይነጣጠል ሕልውና ያላቸው ተግባራት በመሆናቸው፤ የሂስ ባሕል መዳበር ሲጎለብት፣ ለኪነ-ጥበቡ ማደግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው የዘርፉ ሙያተኞች ይናገራሉ ፡፡

የአዲስ አበባ ባሕል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮም ከ2013 ዓ.ም. ጀምሮ በሥነ ጽሑፋዊ፣ በሙዚቃዊ፣ በዕይታዊ ጥበባት፣ እና በክወናዊ ጥበባት ላይ ያተኮሩ የሂስ መድረኮችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት በዘርፉ ላይ የሚያተኩሩ ኪነ-ጥበባዊ ሂሶችን ሲያደርግ የነበረው የአዲስ አበባ ባሕል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ፤ በዘንድሮ ዓመትም ተግባሩን አጠናክሮ በመቀጠል ስድስት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ የሂስ መድረኮችን ለማዘጋጀት እቅድ ይዞ የሚያዘጋጅ ይሆናል ። በዕቅዱ መሠረትም ከኢትዮጵያ የሳይንስ አካዳሚ ጋር በመሆን የ2016 ዓ.ም የመጀመሪያውን የኪነ-ሂስ መድረኩን "ኪነ-ጥበብን ለማሳደግ ኪነ-ሂስን ባሕል እናድርግ" በሚል መሪ ሀሳብ በብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ማዕከል የሳይንስ አካዳሚ ቢሮ የኪነ-ሂስ መድረክ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም አካሂዷል ።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ባሕል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የኪነ-ጥበብ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ሠርፀ ፍሬስብሐት እንደገለጹት፤ ሂስ ምስጋና፣ ነቀፋ፣ ወይም ትችት ሳይሆን በአንድ ደራሲና ተደራሲ ሥራ መካከል የሚሰጥ ብያኔ፣ ትንተናና ትርጉም የማዋለድ ጥበብ ነው። ብዙ ምርምሮችና ጥናቶች ሂሳዊ ፍተሻ ይደረግባቸዋል። ኪነ-ጥበቡ ላይ የሂስ ልማድ በመደበኛነት ወደ ተግባር ብዙም ሲገባ እንደማይታይና እየተሠራበት ባለመሆኑ ሙያዊ የሂስ ዳሰሳ ማድረግ ኪነ-ጥበቡን በከፍተኛ ሁኔታ ያሳድጋል ።







በዘርፉ የሚደረገው ሂስ በኪነ-ጥበብና ሥነ-ጥበብ ሥራዎች ላይ ኅብረተሰቡ የመነጋገር ባሕሉን የሚያዳብርበት መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል ። ስለሆነም የኪነ-ሂስ ባሕልን ይበልጥ በማጎልበት ለኪነ ጥበብ እድገት መሥራት እንደሚገባ የጠቆሙት ሠርፀ ፍሬስብሐት፣ በኢትዮጵያ ያለው የኪነ-ሂስ ባህል ዝቅተኛ በመሆኑ ቢሮው በርካታ የሂስ መድረኮችን በማዘጋጀት ሂስ እንዲስፋፋ ጥረት እያደረገ መሆኑን አብራርተዋል።

በመድረኩ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ባሻገር በሁለተኛ ወይም በሦስተኛ ቋንቋ ተምረው ከሥነ-ልሳን፣ ከሥነ-ጽሑፋዊና ታሪካዊ አጠናን አኳያ በአማርኛ ቋንቋ ላይ የተራቀቁ ደራሲያን ለድርሰቶቻቸው ምክንያቶችና አበርክቶዎቻቸው ላይ የሚያተኩር ጥናታዊ ጽሑፍ ደራሲ፣ ተርጓሚ፤ ሃያሲና አርታኢ አቶ ቴዎድሮስ አጥላው አቅርበዋል ።

አቶ ቴዎድሮስ፣ በዓለም ዓቀፍም ሆነ በሀገር አቀፍ በሌላ የተሻለ የኑሮ አማራጭ ምክንያት፣ ተደራሽነትን እና ተቀባይነትን ለማሳደግ፣ ወይም በግላዊ ፍላጎት ብዙ ደራሲያን ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውጪ አያሌ መጽሐፍት መድረስ የቻሉ ጸሐፍት መኖራቸውን አንስተዋል፡፡ በዚህ ረገድ በሀገራችን እንደ በዓሉ ግርማ፣ ስብሐት ገ/እግዚአብሔር፣ ጸጋዬ ገ/መድኅን፣ አማረ ማሞ፣ በእምነት ገ/አምላክ ያሉ ደራሲዎች አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሳይሆን ለአማርኛ ድርሰት ዕድገትና ዘመናዊነት ጉልህ አበርክቶ እንደነበራቸው አብራርተዋል ፡፡

አቶ ቴዎድሮስ፣ በተለይ ስብሐት ገ/እግዚአብሔር ምናባዊ ነፃነትን ከፍ በማድረግ ተፈጥሯዊነትንና እውነትን በመጻፍ ያልተለመዱ የገጸ ባሕርይ አሳሳልን በማሳየት ለተከታይ ደራሲዎቻቸው ፈር እንደቀደዱ አቶ ቴዎድሮስ ጠቅሰዋል፡፡ በባለሙያዎቹ ዕይታ የአማርኛ ቋንቋ አድራጊ ፈጣሪ እንደሆነ የሚመሰከርለት ፀጋዬ ገ/መድኅን የፀጋዬ ቤት የሚል የግጥም አደራደር ስልትን መድረስ እንደቻለ አክለው ገልጸዋል፡፡ ድርሰቶቹ ዘመን የማይሽራቸው መጽሐፍትን ጨምሮ ለሀገረ መንግሥት ግንባታ ትልቁን ሚና እንደተጫወቱና በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ በኩል በ1959 ዓ.ም የዲፕሎማ፣ የገንዘብና የወርቅ ኒሻን ተሸላሚ እንዳደረገው አንስተዋል፡፡

የኪነ-ሂስ መድረክን ለማበረታታት በሕትመት አቅርቦት ላይ መሥራት እንዳለበት አያይዘው ያነሱት ደራሲ፣ ተርጓሚ ፤ሃያሲና አርታኢ አቶ ቴዎድሮስ፣ "የሕትመት ዋጋ የተመጣጠነ ከሆነ የሥነ-ጽሑፍ ሰዎች ለመፃፍ፣ ኅብረተሰቡ ደግሞ በቀላሉ ገዝቶ ለማንበብ ይችላል፤ ይህም የውይይትና የኪነ-ሂስ መድረክ ለመፍጠር ያግዛል። ለዚህም ከሕትመት ጋር የተያያዘውን ጉዳይ ለመፍታት ሀገሪቷ ራሱን የቻለ የመጽሐፍ ፖሊሲ ሊኖራት ይገባል" ሲሉም ሃሳባቸውን አቅርበዋል ።


የአዲስ አበባ ባሕል ኪነጥበብ ቱሪዝም ቢሮ የኪነ-ጥበብ ጉዞን ለማሳደግ በተለያዩ የኪነ-ጥበብ ሙያዎች ላይ የሚያተኩር ኪነ-ጥበባዊ ሂስ በተያዘው በጀት ዓመት በሰፊው ያካሂዳል፡፡ በዚህም መሠረት በቀጣይ ከሥነ-ጽሑፍ በተጨማሪ በሙዚቃ፣ በሥነ-ሥዕልና ቅርፃ ቅርፅ፣ በፊልምና በሌሎችም ዘርፎች በተመረጡ ርዕሶች የኪነ-ሂስ መድረክ እንደሚያዘጋጅ ከቢሮው የተገኘ መረጃ ያመለክታል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹በዚህች ሀገር መሣሪያ የመያዝ ሙሉ ኃላፊነት ያለው መንግሥት ነው››

አቶ ግርማ ሰይፉ
የኢዜማ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል



አስቴር ኤልያስ

**የዛሬው የዘመን እንግዳችን አቶ ግርማ ሰይፉ ይባላሉ፤ ነጻነትን አጥብቀው ይሻሉ። የፖለቲካውን ዓለም ሲቀላቀሉም ዋና ትኩረታቸው ለአገራቸው የሚሰጡት አንዳች ነገር ካለ በሚል ነው። እንደ ተፎካካሪ የፓርቲ አባልነታቸው ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተፎካክረው የአዲስ አበባ ምክር ቤት አባል መሆን ችለዋል። ትልቁ ግባቸውም ኢትዮጵያን ወደተሻለው መንገድ ማስጠጋት ነው።**

**በተፎካካሪ ፓርቲ ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታ ላይ አገልግለዋል፣ የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርም ሆነውም ሰርተዋል። በፓርላማ ብቸኛው የተፎካካሪ ፓርቲ ተወካይ ሆነው ድምጽ ሲያሰሙ እንደነበር ይታወሳል። በፖለቲካ ላይ የሚያጠነጥን መጽሐፍም ለንባብ ያበቁ ናቸው።**

**እንግዳችን በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ) ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ናቸው፣ የአዲስ አበባ ምክር ቤት የከተማዋን ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኃላፊነት እንዲመሩ ሾሟቸዋል።**

**አዲስ ዘመን ስለ ሀገራዊ የምክክር መድረኩ፤ ኮሚሽኑ እያከናወነ ስላለው ስራና ወቅታዊ በሆኑ የአገሪቱ ሁኔታ ዙሪያ ከአቶ ግርማ ጋር ቆይታ አድርጎ እንደሚከተለው አቅርቦታል።**

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር ዋጋ እያስከፈሉን ያሉ መሰረታዊ ችግሮቻችንና ምንጮቻቸው ምንድን ናቸው ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ግርማ፡-** የችግሮቻችን አንዱና ዋነኛው ምንጭ የሚነሳው ከሐሳብ መቀንጨር ነው የሚል እምነት አለኝ። በአገራችን ችግር እንዳለ ሁሉም ሰው የሚስማማበት ጉዳይ ነው። ችግር መኖሩን አውቆ ለችግሩ መውጫ የሚሆን መንገድ መፈለግ ላይ ሰነፎች ነን። የዚህ አይነት ስንፍና የሚመጣው ከሀሳብ መቀንጨር ነው ብዬ እንዳምን አድርጎኛል።

ለዚህም ነው በአሁኑ ወቅት ትውልድ ላይ መስራት አለብን ብለን ትምህርት ቤቶች ላይ እየተንቀሳቀስን የምንገኘው። ለዚህ ደግሞ ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ጀምሮ እንዲሁም በጨቅላ ሕጻናት ላይ መስራት ይጠበቅብናል። ይህችን አገር ለትውልድ አሻግራለሁ ብሎ የሚያስብና ትንሽም ቢሆን ከመቀንጨር የወጣ ሰው ይህን ማጤን አለበት።

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጥያቄ አሁን ካለንበትን ችግር እንዴት እንውጣ ብቻ ሳይሆን፤ ወደፊት ይህች አገር ከችግር ወጥታ አስተማማኝ መሰረት ያላት አገር እንድትሆን ምን መስራት አለብን የሚለውም ሊሆን ይገባል።

ለምሳሌ ዛሬ ድንገት ከባድ ዝናብ ቢጥል ከዝናቡ ለመጠለል መጠለያ፤ እንዲሁም ወንዝ ሞልቶ ከሆነ ደግሞ ወንዙን ለመሻገር የሚያስችል ግንዲላ/ማሻገሪያ/ እንጣል ይባላል። ይህ ማለት ጊዜያዊ መፍትሔ ነው። አሁን ለኛ የሚያስፈልገን እንዲህ አይነቱ ጊዜያዊ መፍትሔ ሳይሆን ዘላቂ የሆነ መፍትሄ ነው።

ችግራችን አቀንጭራ ነው ያልኩሽ ለዚህ ነው። ምክንያቱ የማሰብና የማስተዋል፤ ለችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ መፍጠር ያለመቻል ነው። አሁን ላይ ስለልጆችም ሆነ ስለትምህርት ስናወራ የአገራችን ከችግር መውጫ መንገድን እያሰብን ነው። ችግሩ ግን እዛስ እንደርሳለን ወይ? የሚለው ነው።

መሳሪያ አንስቶ መፎከር ለችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ መሆን አይችልም። በአንድ ወቅት ፕሮፌሰር ሽብሩ ተድላ ቃለ ምልልስ በተደረጉ ጊዜ አንድ ነገር ሲናገሩ ሰምቻለሁ፤ ይኸውም "አንድ አርሶ አደር አጣማጅ በሬ ሳይኖረው ጠብመንጃ ግን ይገዛል፤ ለምንድን ነው እንዲህ የምታደርገው? ሲባል ረሃብን እታገሰዋለሁ፤ ጥቃትን ግን እንደምን አድርጌ" የሚል ምላሽ መስጠቱን ጠቅሰዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን በዚህ አይነት ስነ ልቦና ውስጥ ሆነን የምንኖር ነን። ነገር ግን ረሃብንም ቢሆን መታገስ አይቻልም፤ በረሀብ ውስጥም መኖር የሚቻለው እስከተወሰነ ጊዜ ነው። ሰው ይነካኛል በሚል ስጋት ብቻ ሳይኖረን ጠብመንጃ ገዝተን የምንራብበትን አጉል ባህል መተው አለብን።

የሚያጠቃንና የሚገፋን ሰው ካለ ‹‹ለምን?›› ብለን መጠየቅ አለብን። ይህን ስናደርግ አንድ ‹‹ለምን?›› ብቻ መሆን የለበትም። አንድ ‹‹ለምን?›› ብቻ አይጠቅምም። የመጀመሪያው ‹‹ለምን?›› የሚነግረን ያለውን ስሜት ብቻ ነው።

ለምሳሌ አንድን ሰው ለምን ትኮሳተራለህ? ብዬ ብጠይቀው ‹‹ራሴን አሞኝ ነው›› የሚል ምላሽ ሊሰጠኝ ይችላል። ግን ራስ ምታት በራሱ በሽታ አይደለም። ራስን ለማመሙ ምክንያቱ ሌላ ሕመም ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ራስህን ያመመህ ለምንድን ነው? ስል ሌላ ‹‹ለምን?›› ማስከተል አለብኝ። በዚህ አግባብ ‹‹ለምን?›› የሚለውን ደጋግመን መጠየቅ ግድ ይለናል። በዚህ መልኩ የምንሔድ ከሆነ ወደ ትክክለኛው የችግሩ ምክንያት /መንስኤ/ ልንደርስ እንችላለን።

አንድ ሰው በደል አድርሶ ከሆነ ‹‹ዘራፍ!›› ብሎ ከመነሳት በፊት ‹‹ስለምን በደል አደረስክ? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። በዚህ አግባብ ከ‹‹ዘራፍ!›› ‹‹ለምን?›› መቅደም መቻል አለበት። ይህን የምናደርግ ከሆነ የውይይት ሰዎች እንሆናለን። ስንወያይ ደግሞ ‹‹ለምን?›› ብለን የምንጠይቀው ከአራትና ከአምስት ጊዜ በላይ ስለሚሆን ጉዳዮች እየጠሩና ወደ መፍትሄያቸው እየቀረቡ ይመጣሉ።

በአገራችን በተለያዩ ማኅበረሰቦች ዘንድ ያሉ አብዛኞቹ ማሕበራዊ እሴቶቻችን ስለማንጠቀምባቸው ነው እንጂ ለችግሮቻችን መፍቻ ቁልፍ መሆን ሊሆኑን ይችሉ ነበር። ከነዚህ አንዱ የሆነው የሽምግልና እሴታችንን መውሰድ ይቻላል።

ሽምግልና የራሱ የሆነ የአካሄድ ስርዓት አለው። በአንድ ጀምበር ተጀምሮ ላይጠናቀቅ ይችላል፤ ከዚህ የተነሳ ቀጠሮዎች ይቀጠራሉ፤ ቀጠሮው በሚፈጥረው ምልልስ ውስጥ እርስ በእርስ የበለጠ የመተዋወቅ እድል ይፈጥራል። ይህ በምልልስ ብሎም በቅርርብ የሚገኝ ውይይት ነው። መፍትሄ በማፈላለግ ሂደት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

ከዚህ በተቃራኒ ያለው የ‹‹ዘራፍ!›› ነገራችን የሽምግልና እሴቶቻችንን እየበላው መጥቷል። በአሁኑ ወቅት ከጊዜ ወደጊዜ እየፋፋ የመጣው ‹‹የዘራፍ!›› ጉዳይ ነው። ስለዚህ የ‹‹ዘራፍ!››ን እሴት ማስታገስ ያለብን በእነዚህ መልካም በሆነ እሴቶቻን በመታገዝም ጭምር መሆን አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ‹‹ዘራፍ!›› ለመባሉ የራሱ ምክንያት አይኖረውም ይላሉ ?**

**አቶ ግርማ፡-** መልካም፤ ወደተነሳሽበት ጥያቄ ልምጣና የችግሮቻችንን ምንጭ መዘርዘር ይቻላል፤ ለምሳሌ የቅርቦቹን ችግሮች ብንጠቅሳቸው የተሳሳቱ ትርክቶች አሉ። ከትርክቶቹ አንዱ የማንነትና የብሔር ፖለቲካን እናስፋፋለን የሚሉ ኃይሎች የፈጠሩት ያልተገባ ቁጭት ተጠቃሽ ነው።

ለምሳሌ የትግራይ አርሶ አደርን ራቁቱን ያስኬደው፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መሬቱ አፈር እንዳይኖረው ያደረገው ‹‹አማራ›› ነው ብለው እንዲያምኑ አድርገዋል። የኦሮሞ ሕዝብ ጭቆና ደርሶብኛል ብሎ እንዲያምን እና የሚጨቁነው ደግሞ ‹‹ነፍጠኛ›› የሚባል ‹‹አማራ›› ነው ብለው እንዲያምኑ የሚያደርጉም አሉ። ሱማሌ ዘንድ ሔደው ደግሞ የደረሰብህ ጭቆና እንዲደርስብህ ያደረገው ‹‹አማራ›› ነው በሚል የተሳሳተ ትርክት እንዲፈጠር ተደርጓል። ይህ ትርክት ደግሞ ‹‹አማራ›› የሚባለውን ማኅበረሰብ ያለስሙ ስም አሰጥቶታል።

አማራ ‹‹ለምን?›› እንደዚህ አደረገ ተብሎ ቢጠየቅ በእርግጥ አማራ እንደዚያ አላደረገም። አንድ እንደቀልድ የሚወራ ነገር አለ። አንድ ፕሮግራም ውጫሌ ላይ እየሰራን ባለንበት ጊዜ ከሱማሌ ክልል ወደ አማራ ክልል የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሱማሌ ተወላጆች አባይን ተሻግረው አማራ የተባለውን ማኅበረሰብ እያዩ ሲሄዱ ‹‹አማራ ማለት ይህ ነው?›› ሲሉ ጠየቁን። ‹አዎ!› የሚል ምላሽም ሰጠናቸው።

‹‹እነዚህ ናቸው በደሏችሁ ያላችሁን?›› ሲሉም ጠየቁንና መልሰው ‹‹ወላሒ! ይቅር ብለናል›› አሉን። ምክንያቱም እውነታው መሬት ላይ ሲታይ የለም። በዚህ አይነት ሌላው እንዲሁ ነው። ይህ አይነቱ የተሳሳተ ትርክት አሁን ላለንበት ግጭት አንዱ ምክንያት ነው። በዚህ መልክ ፍላጎታችን ‹‹ዘራፍ!›. እስከሆነ ድረስ ብዙ ነገራችን የግጭት መንስዔ ይሆናሉ።

ሌላው የችግሮቻችን ምንጭ ደግሞ መንግስት የማያቀርበውን ነገር ‹‹አቀርባለሁ›› ብሎ ማቅረብ አለመቻል ነው። ቃል የተገባለት ነገር ሳይቀርብ ሲቀር ዜጋው ይናደዳል፤ ለምሳሌ መንግስት ስኳር፣ ጤፍ፣ ማዳበሪያና ሌላም ነገር ‹‹አቀርባለሁ›› ይላል። ሳይቀርብ ሲቀር የቅሬታ ምንጭ ይሆናል። የመንግስትም የፖሊሲ ችግር የቅሬታ ምንጭ ሊሆን ይችላል። መንግስት ቃል ገብቶ የሚፈጠሩ ቁጭቶች እንኳን እዳው ገብስ ነው። ማለቴ ጥሩ ነው፤ በተለይ እንደ እኔ ላለ ተቃዋሚ መንግስትን ከስልጣን ለማስነሳት ይጠቅማል.....ሃሃሃ.....።

> በአገራችን በተለያዩ ማኅበረሰቦች ዘንድ ያሉ አብዛኞቹ ማሕበራዊ እሴቶቻችን ስለማንጠቀምባቸው ነው እንጂ ለችግሮቻችን መፍቻ ቁልፍ መሆን ሊሆኑን ይችሉ ነበር። ከነዚህ አንዱ የሆነው የሽምግልና እሴታችንን መውሰድ ይቻላል

ነገር ግን የኅብረሰብ ግጭቶች፤ በተለይ ማንነትን መሰረት አድርገው የሚፈጠሩ ግጭቶችን የበለጠ የሚያባብሱና የሚያቀጣጥሉ አሉ። እነዚህ ኃይሎች ግጭትን የኑሯቸው መሰረትና የገቢያቸው ምንጭ ማድረጋቸውን ተረድተን እና ነቅተን መረባረብ ይጠበቅብናል።

በአስር ሺ ማይልስ ርቀት ላይ በሚገኝ አገር ተቀምጠው ይህ ብሶት እንዳይከስም እያራገቡ የሚያጋግሉ አሉ። እነርሱ በሰው አገር በነጻነት እየኖሩ ሌላው ከአንዱ ቦታ ወደሌላ ቦታ እንኳ በቅጡ እንዳይዘዋወር፣ አንድ ቦታ ላይ ብቻ በማንነቱ ተሸብቦና ተከርችሞ እንዲቀመጥ ቅስቀሳ ሲያደርጉ የሚውሉ አሉ።

ይህንኑ ጉዳይ ብቻ ስራዬ ብለው የያዙ፣ ምንም ሙያ የሌላቸውና ምንም አይነት ኃላፊነት የማይሰማቸው አሉ። በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ቦታ ይዘው ግጭት እየጠመቁ ያሉት እነርሱ ናቸው። የሚጠቀሙት ከዚህ ቀደም የነበሩ የተሳሳቱ ትርክቶችን ሊሆን ይችላል፤ ለእነርሱ ይህ የገቢ ምንጫቸው ነው።

ከምንመሳሰለው ይልቅ በጣም ጥቂት የሆነውን የማንመሳሰለውን ጉዳይ በማጉላት በዚያ ዙሪያ እንድንጣላ አጥብቀው የሚመክሩን ሰዎች አሉ። እኛ ኢትዮጵያውያን ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ብትሄጂ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብም ብታቃኚ ከምንለያይበት ይልቅ የምንመሳሰልበት ደምቆ የሚታይ ሕዝብ ነን። ልዩነቶቻችን ራሳቸው ቢሆኑ የሚያጣሉን አይደሉም።

በመጀመሪያ ደረጃ መታወቅ ያለበት በእኛ አገር ብዙ ማንነቶች እንዳሉ አስመስለው የውሸት ፖለቲካ የሚያስወሩ አካላት መኖራቸው ነው። የውሸት ብዙ ማንነት እንዳለ የሚያስመስሉ አሉ። ከእኛ በቅርብ ርቀት ያለችውና በሕዝብ ቁጥርም በጣም የምታንሰው ደቡብ ሱዳን ከእኛ የበለጠ ማንነት አላት።

ቢያንስ እኛ አንድ የሚያደርገን ኢትዮጵያዊ የሆነ ትልቅ ስም፣ ፊደልም ቋንቋም ያለን ሰዎች ነን። ፊደል ስል ሁሉም ሰው በግድ አማርኛ ይናገራል ማለት አይደለም። ነገር ግን ኢትዮጵያዊ ማንነት ውስጥ ያለ መሆኑን ስንረዳ ብንችል የመጣላታችን ምክንያት አይሆንም።

ብቸኛ አፍሪካዊት ፊደል ያላት አገር ተብሎ መጠራት እና በዚህ ጥላ ውስጥ መገኘት እንዴት ይጠላል? ስለዚህ የሚያቀራርበንና የሚያመሳስለንን ከምንወስድ ይልቅ የሚያጣላን ላይ እንድናተኩር ይጎተጉቱናል። ለመጣላት ሁሉንም ልዩነት ይሰብካሉ። ልዩነትማ ከተባለ በአንድ እናትና በአንድ አባት ልጆች መካከልም ቢሆን ልዩነት አለ፤ ችግሩ ልዩነት መኖሩ አይደለም፤ ልዩነታችንን እንዴት እናስቀጥለዋለን በሚለው ላይ መስማማትና መተጋገዝ አለመቻላችን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህን ችግሮች በመፍታት የተሻለች ሀገር ለዜጎች ለመፍጠር ትኩረት ሰጥተን ልንሰራቸው የሚገቡን ስራዎች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ግርማ፡-** ከግጭት ለማትረፍ የሚተጉ ሰዎችን ማንነት አውቆ እነርሱን ንቆ መተው አንዱ ማድረግ የሚገባን ጉዳይ ነው። አስቀድሜ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የእነርሱ ያልሆኑ ትውልድ መፍጠር አለብን። ያልቀነጨረ ወጣት መፍጠር መቻል አለብን። ካልቀነጨርን የሰው መባላትና መጋጨት የቢዝነስ ሐሳብ ሆኖ አይሰራም። እንድንጣላ ሌት ተቀን የሚተጉ አካላት አካሔዳቸው እናት አባት፤ እህት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹በዚህች ሀገር መሣሪያ የመያዝ...

ከገጽ 6 የዞረ

ወንድም ሞቶባቸው እድር ለመብላት እንደመፈለግ ነው። የእድር ገንዘብ አገኛለሁ ብሎ ሰው እንዲሞትበት የሚፈልግ አለ? ግጭት እየፈጠሩ ቢዝነስ የሚሰሩ ሰዎች ግን ከዚህ የሚሻሉ አይደሉም። ስለዚህ እነዚህን ንቆ መተው የተሻለ ነው።

በጣም አበዛኸው ካልተባልኩ በስተቀር እንደቻይና የራሳችንን የምንገናኝበትን ኔትዎርክ ከማበጀት ውጭ ከውጭ የሚተላለፉ የማሕበራዊ ትስስር ገጾች ቢዘጉ የሚል ሁሉ ሐሳብ አለኝ። እኔ በነጻነት በጣም የማምን ሰው ነኝ፤ ለነጻነት የምሰጠውን ዋጋ ያህል ለሌላ ነገር የምሰጠው ዋጋ የለኝም። ማንም ነጻነቴን እንዲጋፋ እንደማልፈልግ ሁሉ የማንንም ነጻነት መጋፋት አልፈልግም። ነገር ግን ከነጻነቶቼ አንዱ ሐሳቤን በነጻ መግለጽ ነው ብዬ ሰዎች እርስ በእርሳቸው እንዲጋደሉ ከፈለኩ እሱ ችግር ነው።

ለምሳሌ አንድ አካባቢ ኔትወርክ ተዘጋ ሲባል፤ ሕዝቡ መረጃ የማግኘት መብቱ ተነፈገ ብለው ሲጮኹ ይደመጣል፤ አንዳንዱ አካል ጩኸታቸው እውነት ይመስለዋል። በተለይ ደግሞ ፈረንጆቹ ጅሎች ሳይሆኑ አይቀርም ያስብላል። ለምሳሌ አማራ ክልል ያለ አርሶ አደር የዩቲዩብ ፍቅር አላስችል ስለሚለው ነው? እውን ለአርሶ አደሩ አዝነውለት ነው መረጃ የማግኘት መብት ተነፈገ ብለው የሚጮኹት? አይደለም።

አንዱ አንዱን ሲገድል ፊልም አንስተው ‹‹ይኸው እየተገዳደሉ ነው›› ብለው ሊያሳዩ ነው እንጂ። ይህ ቢዝነስ ነው። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በዩቲዩብ ተከታዮቻቸው ብዛት ገንዘብ ያገኛሉ። ስለዚህ ማለት የሚጠበቅባቸው ሱቃችን ወይም ገበያችን ተዘጋብን ነው እንጂ የዩቲዩብ መዘጋት ለአማራ አርሶ አደር ምንም የሚያመጣው ፋይዳ ኖሮት አይደለም። በኦሮሚያም ሆነ በሌላው ቦታ እንደዚያው ነው።

ለምሳሌ በቅርቡ አዲስ አበባ ላይ የኢሬቻ በዓል ተከበረ፤ እኔ የአዲስ አበባ ነዋሪ ነኝ። ተወልጄ ያደግሁትም ሆነ ከ50 ዓመት በላይ የኖርኩት አዲስ አበባ ውስጥ ነው። ስለዚህ ከእኔ የበለጠ ስለአዲስ አበባ የሚያገባው ሰው ያለ አይመስለኝም። ታዲያ ኢሬቻ አዲስ አበባ ውስጥ በመከበሩ እኔ ምን እጎዳለሁ?

‹አዲስ አበባ ውስጥ ኢሬቻ ተከበረ፤ የማንነት ጫና ሊፈጠርብህ ነው፤ እንትን ሊሆን ነው›› እያሉ ጠብ ማጫር የያዙ አካላት ዓላማቸው ምን እንደሆነ ራሱ አይታወቅም፤ አዲስ አበባ ውስጥ ጨምበላላም፣ ጊፋታም፣ ሌላው ቀርቶ ከአገራችን ውጭ ያሉ ፌስቲቫሎች በየተወሰነ ጊዜ መጥተው ቢከበር ምንድን ችግሩ? እኔ የሚታየኝ ከበዓሉ መከበር በተጓዳኝ ገቢው ነው።

በእርግጥ በዓሉ ሲከበር መንግስት ጣልቃ ገብቶ የሚያደርገውን ቢያቆም ደስተኛ ነኝ። መንግስት የእኔ ነው የሚለውን አቋሞ ለኅብረተሰቡ ቢተውለት እወዳለሁ። ከዛ ውጭ ግን በአዲስ አበባ በዓመት አንዴ ብቻ የሚከበር በዓል ሳይሆን ለምን ሶስት አራቴ እንኳ አይሆንም? መከበሩ ችግሩ አይታየኝም።

ይህ የበዓላት መከበር የከተማ ባህሪ ነው፤ አዲስ አበባ የምታድገው በኢንዱስትሪ አይደለም። አዲስ አበባ የምታድገው በቱሪዝም ነው። መሆን ያለባትም የቱሪዝም ማዕከል ነው። የቱሪዝም ከተማ ሰዎች የሚመላለሱበት እና የሚዝናኑበት ነው። መሆን ያለበትም ይህ ነው። አዲስ አበባ የአየር ንብረቷም ምቹ እንደመሆኑ 24 ሰዓት መንቀሳቀስ የሚያስችል የቱሪስት ከተማ መሆን አለባት።

ይህ ግጭት እንዲነሳ የሚቀሰቅሱና አዲስ አበባ ውስጥ ‹‹‹ለምን የኢሬቻ በዓል ይከበራል?›› የሚሉ አካላት በአሜሪካ አገር ‹‹የኢትዮጵያ ቀን!›› በሚል የሚያከብሩ አካላት ናቸው። ‹‹ተከብረሽ የኖርሽው በአባቶቻችን ደም!›› እያሉ በአሜሪካ አገር ድንኳን ጥለው እየጨፈሩ ያሉ ሰዎች ናቸው።

እንዲህ ስል በኢሬቻ በዓል ከበዓሉ ዓላማ ውጭ ያልተገባ ነገር ያደረጉ አካላት ልክ ናቸው የሚል መታወቂያ እየሰጠሁ አለመሆኑ ልብ ይባልልኝ። ኢሬቻ አከብራለሁ ብሎ አደባባይ ወጥቶ ለሌላው አካል ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው ልክ ነው እያልኩ አይደለም። ኢሬቻ፣ ጥምቀት፣ ታላቁ ሩጫና ሌላውም ሲከበር አላስፈላጊ መልዕክት ለማስተላለፍ የሚገቡ ባለጌዎችን የሚያካትት አይደለም።

በአሜሪካ አገር ‹‹የኢትዮጵያ ቀን!›› ብለው ለማክበር ወጥተው የሚሰዳደቡ አሉ፤ በዓሉ እነዚያን ባለጌዎች የሚያካትት አይደለም። በእኔ አመለካከት እንደ እነዚህ አይነት ችግሮችን መፍታት ያለብን አርቀን እያሰብንና እየተቻቻልን መሆን አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ለችግሮቻችን መፍትሄ ከማፈላለግ አንጻር ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ምን ተስፋ ይዞ መጥቷል?**

**አቶ ግርማ፡-** እኔ ለምን ተስፋ ቆርጣለሁ? አንድ ነገር ሰው ለመስራት ሲፈልግ በመጀመሪያ መነሳት ያለበት ተስፋ አድርጎ ነው። ተስፋ እንደሌለው የሚያስብ ሰው ካለ ራሱ ተስፋ የቆረጠ ስለሆነ ያንን ሰው መስማት አያስፈልግም ባይ ነኝ። እያንዳንዷ ትንንሽ ነገር የምትደረገው ለበጎ እና ለመልካም ነገር የምትደረግ ከሆነ መስራት ያለብን እዛ በጎ ነገር ላይ ምን ባዋጣ ይሻላል ብለን ነው።

እኔ ይህንን በምሳሌ ለመግለጽ አንድ በጽኑ ሕመም ያለን ሕመምተኛ እያከመ ያለ ሐኪም ታማሚው ተስፋ የለውም ብሎ ከጀመረ ለምን ጓንትስ ያደርጋልን? ስለዚህ የአገራችንን ችግር ይፈታል ብለን ተስማምተን እያለ አይሆንም ሊባል አይገባም።

ስለዚህ ምክክር መድረኩ ብዙ ተስፋ ያለው ነው። እኔም ደግሞ በዛ ውስጥ የማዋጣው ብዙ ነገር አለኝ ብዬ አምናለሁ። ተስፋ የለውም የሚሉ ካሉ እነርሱ ለእኔ የከሸፉ ሐኪሞች አይነት ናቸው። ተስፋ የለውም የሚል አባባል የሰነፎች መገለጫ ነው። ሰነፎች ደግሞ በምክክር መድረኩ ምንም ተስፋ የለም ብለው ሌላ ቦታ ደግሞ በሁለት ዓረፍተ ነገር ጽሁፍ ጽፈው ሕዝብን ሲያበጣብጡ የሚስተዋሉ ናቸው።



> **ተስፋ የለውም የሚል አባባል የሰነፎች መገለጫ ነው። ሰነፎች ደግሞ በምክክር መድረኩ ምንም ተስፋ የለም ብለው ሌላ ቦታ ደግሞ በሁለት ዓረፍተ ነገር ጽሁፍ ጽፈው ሕዝብን ሲያበጣብጡ የሚስተዋሉ ናቸው**

እንዲህ አይነቱ ሰነፍ ሰው በእርግጥ ተረት ለመናገር ምንም ችግር የለበትም። ወይም ደግሞ የቀድሞውን የተሳሳተ ትርክት እንደ ቀልድ በማህበራዊ ትስስር ገጽ ለማስፈር አያፍርም። እንደዚህ አይነት ሰው ደግሞ ቁስል ላይ እንጨት የሚሰድ ነው።

**አዲስ አበባ፡- ለኮሚሽኑ ተልእኮ ስኬታማነት ከማን ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ግርማ፡-** ከሁሉም አካላት የኮሚሽኑ እንቅስቃሴ ስኬታማ ይሆን ዘንድ አለመበጥበጥ ይጠበቃል። ከዚህ ጎን ለጎን ለምክክሩ ስኬታማነት ሁሉም የሚጠየቀው የሚችለውን እንዲያደርግ ነውና የሚችለውን ሁሉ ማድረግ ይኖርበታል ። ትልቁ ችግራችን አንዱ ሲደክመው አገር ሁሉ የደከመው መምሰሉ ነው። እሱ እንቅልፋ ስለመጣ ብቻ ሁሉም መተኛት ያማረው መምሰሉ ነው። የደከመው ካለ ወይም እንቅልፉ የመጣበት ካለ ማድረግ ያለበት ማረፍ ወይም መተኛት እንጂ ሌላውን ይዤ ልረፍ አሊያም ልተኛ ማለት አይደለም። ኑ! እንተኛ ማለት አይሰራም። የሚያበረክተው ነገር ከሌለው እጁን መሰብሰብ ይጠበቅበታል።

ሌላው አብዛኛው ሰው ወይም አብዛኛው ባለድርሻ አካል ሚናውን መለየት አለበት። በማያገባው ነገር አለመግባት ያስፈልጋል። አሁን ላይ አብዛኛው ሰው በማያገባው ከመግባት አልፎ ፖለቲከኛ ሆኗል። አንድ ሐኪም በሰለጠነበት የስራ መስክ መስራት ቢችል ምናለበት? ፖለቲካውን ለፖለቲከኞች መተው ተገቢ ነው።

ምክንያቱም ሁሉም ሰው ፖለቲከኛ መሆን አይጠበቅበትም።፡ ‹‹አይ...እኔ ፖለቲከኛ እሆናለሁ›› የሚል ከሆነ የምሩን ፖለቲከኛ መሆን አለበት እንጂ ባልኮኒ በመደገፍ፣ ቡና እየጠጣ እና ማሕበራዊ ትስስር ገጽ ላይ በመጣድ ፖለቲከኛ መሆን አይቻልም። ፖለቲካ ሲባል መስጠትን የሚፈልግ ነው፤ ዋጋ መክፈልንም የሚጠይቅ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። ለዛ የሚመጥን እውቀትና ብቃት ያለው ሰው መሆን የግድ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቁ ችግር ፖለቲካ የእውቀት ሳይሆን የደፋሮች መሆኑ ነው። ደፋሮች ደግሞ ብዙ ጊዜ እውቀት አልባ ናቸው። እውቀት የሌለው ሰው ደግሞ ፖለቲከኛ ልሁን ሲል በጣም አደገኛ ነገር ይፈጠራል። የፖለቲካውን ቁንጮ የሚጨብጥ ሰው ትልቁን ነገር የያዘ ማለት እንደሆነ የሚታወቅ ነው፤ እሱን ደግሞ የሚይዘው ያለአዋቂ ሰው ከሆነ በስሌት ሳይሆን በስሜት የሚንቀሳቀስ ስለሚሆን ከባድ ጉዳት ሊፈጠር ይችላል።

ስለዚህ ሁሉም በየተሰማራበት ዘርፍ መስራት አለበት። የኢትዮጵያ ፖለቲካ የደፋሮችና የደንቆሮዎች መሆን የለበትም። ፖለቲካ በባህሪው ሁለገብ እውቀት የሚጠይቅ ነው። በአንድ ነገር ብቻ ስፔሻላይዝድ በማድረግ ስኬታማ መሆን የማይቻልበት ነው። በመሆኑም ፖለቲካ በምን አገባኝ ለደፋሮች ሊተው አይገባም። ሁሉንም ሊያርቅ የሚችል ኃይል በመሆኑ ጥንቃቄ የሚያሻው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከታሪክ ትርክቶች ጋር በተያያዙ የሚነሱ አለመግባባቶችንና ቁርሾዎችን ማከም የሚያስችል እንዴት ነው ይላሉ?**

**አቶ ግርማ፡-** ቁርሾውም ትርክቱም ሆነ ሌላ ሌላውም ነገር አለ፤ አስቀድሜ ልገልጽልሽ እንደሞከርኩት የእነዚህ መድኃኒት ‹‹ዘራፍ!›› አይደለም። ‹‹ለምን?›› ማለት ነው። ለምሳሌ እኔ በደል ደርሶብኝም አድርሼም አላውቅም። ፖለቲካ ውስጥም የገባሁት በቁጭት ሳይሆን ለአገሬ ማበርከት የሚገባኝ ነገር አለ በሚል ነው።

ተበድያለሁና አንድ የበደለኝን አካል ፈልጌ ቁጭቴን ልወጣ በሚል ሐሳብ ለማወራረድ አይደለም። ወይም ደግሞ ቆስያለሁና ገብቼ ልታከም በሚል ስሌት አይደለም። ፖለቲካ በመሰረቱ የቁጭት ማብረጃ ሊሆን አይገባም። እንዲህ አይነት ሰዎች ካሉ መሄድ ያለባቸው ማገገሚያ ማዕከል ነው፤ ለእነርሱ ኒውክሌር ወይም ባንክና ታንክ አይሰጥም። ከተሰጣቸው የሚያስቡት ቁጭታቸውን ለማወራረድ ነው።

እኔ ከፖለቲካ ትርፍ አልፈልግም። የምሳተፈው የምሰጠው ስላለኝ ነው። ፓርቲ ውስጥም ስሳተፍ ብቻ ለብቻ ከምንሆን በጋራ የተሻለ ነገር ለአገር እናበረክታለን በሚል ስሌት ነው። መቆጨት ካለብን አገራችንን የተሻለ ለማድረግ ነው። ስለዚህ ከ‹‹ዘራፍ!›› ወደ ‹‹ለምን?›› እንምጣ እላለሁ።

ለችግሮቻችን ከስር መሰረቱ መፍትሔ ሊሆን ሚችል መድሀኒት ያስፈልገናል። ለራስ ምታት ሁሌ አስፕሪን በመውሰድ፤ ለጉበት በሽታ መዳረግ አይገባም። የራስ ምታቱ መነሻ ምን እንደሆነ በአግባቡ መታወቅ አለበት፤ ይህን ማድረግ ሲቻል ነው ራስ ምታቱን ለዘለቄታው መዳን የሚቻለው፤ የኛም ጉዳይ በዚህ መልኩ ሊታይ የሚገባ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ተፎካካሪ ፓርቲ አመራርነቶ እና እንደ አንድ ዜጋ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሰላምና መረጋጋትን ለማምጣት ምን መደረግ ይኖርበታል ብለው ያምናሉ ?**

**አቶ ግርማ፡-** እንደሚታወቀው እኛ እንደ ኢዜማ የጸጥታ መዋቅር የለንም። በጣም ትልቁ የምናደርገው ነገር የፓርቲያችን አባላት በምንም መልኩ የአገርን ሰላም በሚያደፈርስ አጀንዳች ውስጥ እንዳይሳተፉ ማድረግ ነው። ይህን እንዳያደርጉ ምክርም እንሰጣለን።

የፓርቲያችንም አባላት ሰዎች እንደመሆናቸው ሌላው ሊሰማው የሚችል አይነት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። ነገር ግን ከስሜት እንዲወጡ እና ተረጋግተው እንዲያስቡ እናደርጋለን።

ቢያንስ እኛ እንደ ፓርቲያችን የችግር አባባሾች መሆን የለብንም ብለን እናምናለን። ከሁሉም በላይ ግን ለጸጥታው መደፍረስ ከውጭም ከውስጥም የሚሳተፈው አካል ረጋ እንዲል ምክራችንን እንለግሳለን።

ለምሳሌ መንግስት መሳሪያ ይዞ አስቸግሮ ከሆነ መንግስትን በጋራ ሃይ! ለማለት እንጥራለን፤ ግን ደግሞ መሳሪያ ተይዞ ፖሊስ ጣቢያ በመውረር እስረኛን ለማስለቀቅ መጣር አግባብነት የሌለው ተግባር ነው፤ ሌባን የሚጠብቀውን ፖሊስ ጣቢያ መውረር የመብት ታጋይ ምናምን መባሉ ይቀርና ሌባ መሆን ነው።

ፖሊስ ጣቢያ ወርሮ እስረኛ ማስለቀቅ አሁን አሁን ትልቅ ፋሽንና ጀብዱ ሆኗል። ስለዚህ ይህ ማለት ከተማ ውስጥ ሌባ ማሰማራት ማለት ነው። እንዲያ ከሆነ ደግሞ ሕገ ወጥነት ነው።

በዚህች አገር መሳሪያ የመያዝ ሙሉ ኃላፊነት ያለበት መንግስት ነው። በነገራችን ላይ ግለሰቦች መሳሪያ ለምን ይይዛሉ የሚል ሙግት የለኝም፤ እኔ በግሌ መሳሪያ አልይዝም። ቢያንስ የግል መሳሪያ መያዝ መብት ነው፤ ነገር ግን መሳሪያ የያዙ ሰዎች በአንድ ቀበሌ ውስጥ ተሰብስበው ራሳቸውን በሆነ ቡድን ሰይመው መንቀሳቀስ ግን በፍጹም መፈቀድ የሌለበት ጉዳይ ነው።

መሳሪያ እየታጠቁ የፈለጉ ቀን እየወጡ ታክስ የሚሰበስቡ፤ የፈለጉ ቀን ደግሞ ‹‹ወንድ የሆነ በዚህ ያልፋል›› ለሚሉ መፈቀድ የለበትም። በግል ደረጃ ግን መብት ነውና መፈቀድ አለበት፤ መንግስትም ያንን የከለከለ አይመስለኝም። እንዲያውም ምናልባት አካባቢያቸውን በመጠበቅ ተባበሩኝ ሊላቸው ይችላል። ለመንግስትም ስራ ያቀላሉ።

ነገር ግን በጎጥ በመደራጀትና መሳሪያ በመያዝ ከዚያኛው ጎጥ ጋር ግጥሚያ እና ዘራፍ ዘራፍ አይሰራም። እሱ ጸረ ሰላምነት ስለሆነ እኛ እንደ ፓርቲ እሱን አናበረታታም። ከዚህ ጎን ለጎን የምክክር ኮሚሽኑን ከመጀመሪያው ጀምሮ እየደገፍነው ነው። ያለንንም እያበረከትን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ግርማ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።



# በአውሮፕላን አብራሪነት በግል ከፍለዉ መማር ለሚፈልጉ

የኢትዮጵያ አቪዬሽን ዩኒቨርሲቲ በግል ከፍለዉ በአብራሪነት ሙያ መማር የሚፈልጉ ተወዳዳሪዎችን መልምሎ ለማሰልጠን ዝግጅቱን ጨርሷል። ስልጠናው የሚካሄደው በአዲስ አበባ፣ ሐዋሳ፣ ድሬዳዋ እና ባህርዳር፣ እንዲሁም በሁሉም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የኢትዮጵያ አቪዬሽን ዩኒቨርሲቲ ስልጠና ማዕከላት ነው።

All In One
Ethiopian Aviation University

ስልጠናው 18 ወራት የሚወስድ ሲሆን ተማሪዎች በኮሜርሻል ፓይለት ላይሰንስ (ሲ.ፒ.ኤል.) መስክ ብቁ ሆነው ይወጣሉ።

ተወዳዳሪዎች ስልጠናውን ለመውሰድ የሚያስፈለገውን ክፍያ መክፈል ይጠበቅባቸዋል።

ሰልጣኞች ከተመረቁ በኋላ በግላቸው ሥራ መፈለግ እንደሚኖርባቸው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ማስታወስ ይወዳል።

## የመግቢያ መስፈርቶች፡ -

- ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት መስክ ቢ.ኤስ.ሲ. ዲግሪ እና ዝቅተኛ ሲ.ጂ.ፒ.ኤ. 2.75፤
- ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በማንኛውም የትምህርት መስክ ቢ.ኤስ.ሲ/ቢኤ ዲግሪ እና ዝቅተኛ ሲ.ጂ.ፒ.ኤ. 3.00፤ እንዲሁም የ10ኛ ክፍል የሒሳብ፣ ፊዚክስ እና እንግሊዘኛ ቋንቋ የትምህርት ዓይነቶች ቢያንስ 'B' ውጤት ያላቸው፤ ወይንም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሒሳብ፣ ፊዚክስ እና እንግሊዝኛ የትምህርት ዓይነቶች የመግቢያ ፈተና 50% ዉጤት ያስመዘገቡ፤

- ዕድሜ፡- ከ18- 30 ዓመት
- ቁመት: ለወንድ - ቢያንስ 1.70 ሜትር
  ለሴት - ቢያንስ 1.65 ሜትር
- ጠቅላላ የሥልጠና ጊዜ፡ 18 ወራት
- የጤንነት ሁኔታ፤ በህክምና ባለሙያ የተረጋገጠ ጤነኛ

**ለበለጠ መረጃ: - Etauinfo@ethiopianairlines.com**

**ድረ ገጻችንን https://eau.edu.et/ ይጐብኙ ወይም**
**በ +2511 15174600/8598 ይደውሉ።**

Ethiopian የኢትዮጵያ
Aviation University
PIONEER OF AVIATION EXCELLENCE

ዜና

# በአዲስ አበባ ከ802 ሺህ በላይ....

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከምገባ ሥርዓቱ በተጨማሪ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችንም ጭምር ለተማሪዎች በመስጠት ላይ ያለ መሆኑን ያነሱት የቢሮ ኃላፊው፤ የምገባ መርሐ ግብሩንም መንግሥት ሙሉ በሙሉ በራሱ ወጪ እንደሚሸፍን ጠቅሰዋል፡፡

በትምህርትና ተማሪ ላይ የሚደረገው ኢንቨስት መንት ለሀገር ብልጽግና ጉዞ የሚደረገውን ጉዞ በብርቱ እንደሚደግፍ ታምኖበት በከፍተኛ ተነሳሽነት በመሥራት ላይ እንደሚገኝም ኃላፊው አመላክተዋል፡፡

እንደ ቢሮ ኃላፊው ንግግር፤ በትምህርት ቤት ምገባ መርሐ ግብሩ ምክንያት ተማሪዎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ማግኘት የቻሉ ሲሆን በትምህርት ውጤታቸው ላይም መሻሻል መታየቱን ገልጸዋል፡፡

ሀገር የምትለወጠው በትውልድ መሆኑን በመረዳት ትውልድ ላይ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ያመላከቱት ኃላፊው፤ የትምህርት ምገባ መርሐ ግብሩም የዚህ ጉዞ አካል ስለመሆኑ ጠቅሰዋል፡፡

የቢሮ ኃላፊው በንግግራቸው በጉብኝቱ ላይ የተገኙት ዓለማቀፍ ኃላፊዎች ኢትዮጵያ በትምህርት ምገባ ላይ እየሠራች ያለችውን ሥራ በበጎ ጎን የሚመለከቱት መሆኑን መግለጻቸውን በመጥቀስ ለዘርፉ የአይነት ድጋፍ ለመስጠት ቃል መግባታቸውንም አመላክተዋል፡፡

የደጃዝማች ወንድይራድ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ ሰለሞን ከቤ በበኩላቸው፤ የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም ከተጀመረ አንስቶ በትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ውጤትም ሆነ ሥነምግባር በከፍተኛ ደረጃ መሻሻሉን ተናግረዋል፡፡

ትምህርት ቤቱ የከተማ ግብርናን ተግባራዊ በማድረግ ለምገባ ፕሮግራሙ ድጋፍ የሚሆኑ ግብዓቶችን በማቅረብ ላይ ይገኛልም ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ሚስተር ሬሚ መርችዋክስ በጉብኝቱ ባስተላለፉት መልዕክት በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው የትምህርት ቤት ምገባ ለሌሎች ተሞክሮ መሆን የሚችል ነው ብለዋል፡፡

የፈረንሳይ እና የፊላንድ መንግሥታት በጋራ በመሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ 400 ሚሊዮን የሚደርሱ ሕጻናትን በትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም ተጠቃሚ ማድረጋቸውንም በጉብኝቱ ወቅት ተመላክቷል፡፡

በመርሐ ግብሩ ላይ የፊላንድ ሚሽን ምክትል ዳይሬክተር ሚስ ላራ ኔልቶናን እና በዓለም አቀፉ የምግብ ፕሮግራም የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ክሪስ ሪኮይ የተገኙ ሲሆን፤ ባለሥልጣናቱ በእለቱ ከጉብኝታቸው በተጨማሪ ተማሪዎቹን በመመገብ ሥራ ላይ ተሳትፈዋል፡፡

# "በኢትዮጵያ የተመድ ሰብዓዊ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጀነራል ዳይሬክተር አምባሳደር ዘነበ ከበደ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የተመድ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መርማሪ ኮሚሽን የጊዜ ቆይታ መቋረጡ ለኢትዮጵያ ትልቅ የዲፕሎማሲ ድል ነው። ኢትዮጵያ በራሷ ምርጫ ሰላምን ካወረደች በኋላ ከአውሮፓ ኅብረት፣ ከአሜሪካና ከሁሉም የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብና ከአጋሮች ጋር የመቀራረብ የዲፕሎማሲ ሥራ ሲሠራ ነበር፤ ውጤቱም ታይቷል።

እንደ አምባሳደር ዘነበ ማብራሪያ፤ ኮሚሽኑ እንዲቋረጥ ጥያቄዎችን ከማቅረብ ባሻገር ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ ተሠርቷል። ነገር ግን የኮሚሽኑን ሚና የማስቀጠል ወይም ኮሚሽኑን የሚተካ «አይተም ቴን» የሚባል አማራጭ ለማቅረብ ፍላጎት ቢኖርም ለኢትዮጵያም ለነሱም እንደማይጠቅም ለወዳጆቻችን በመግለጽ ሳንቀበለው ቀርተናል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ተጠያቂነትን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኛ በመሆኗ የኮሚሽኑን ሚና ማስቀጠልና ኢትዮጵያን አጀንዳ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን በሰፊውና በየደረጃው የማሳመን የዲፕሎማሲ ሥራ በመሠራቱ የተመድ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መርማሪ ኮሚሽን የጊዜ ቆይታ መቋረጡን የገለጹት አምባሳደር ዘነበ፣ እንዲሁም የኮሚሽኑን ሚና የሚተካው «አይተም ቴን» አማራጭ እንዳይቀጥል ማድረግ ተችሏል ሲሉም አስረድተዋል።

የኢትዮጵያን መልካም፣ ሰላም፣ ልማትና እድገት የማይወዱ የውጭና የውስጥ ፀረ- ሰላም ኃይሎች የሠሩት ሥራ ብዙ ዋጋ እንድንከፍል አድርጎናል ያሉት አምባሳደር ዘነበ፤ በዚህ የኮሚሽኑ ሥራ እንዲቀጥል የቻሉትን ሁሉ ሞክረዋል። ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግሥት በሠራው የዲፕሎማሲ ሥራ ሴራዎችን ማክሸፍ ችሏል፤ ኮሚሽኑም ተቋርጧል ብለዋል።

አምባሳደር ዘነበ እንደገለጹት፤ የኮሚሽኑ ሥራ አይቀጥልም ማለት የኢትዮጵያ መንግሥት ሰብዓዊ መብትን አያከብርም ወይም ተጠያቂነት አይሰፍንም ማለት አይደለም። ተጠያቂነትን ተግባራዊ ለማድረግ የሽግግር ፍትሕ ዘዴንና የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽንን ሥራ እየተሳለጠ ነው። በዚህም ተጠያቂ የሚሆኑትን በመጠየቅና ይቅርታ በመደራረግ የሀገርን ሉዓላዊነት በጠበቀ መልኩ በመተባበርና በመተሳሰብ ለመሥራት ተስማምተናል። ከሁሉም በላይ በውስጥ ጉዳያችን መሥራት ያለብን እኛው ኢትዮጵያውያን ነን። መንግሥትም ለዜጎቹ ሲል በሕገ መንግሥቱ መሠረትና የተቀበልናቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ አድርጎ ይሠራል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ የኢትዮጵያና የምዕራባውያን የዲፕሎማሲ ግንኙነት በመልካም ሁኔታ ላይ ይገኛል። ለዚህ ማሳያው የአውሮፓ ኅብረት የዓለማቀፍ አጋርነት ኮሚሽነር ጁታ ኡርፒላይነን በኢትዮጵያ ጉብኝት አድርገዋል። ወደ መደበኛና እርቅ እየተመለስን ስለሆነ የተገኘውን የዲፕሎማሲ ውጤት ማጠናከር ያስፈልጋል። በተለይ በውጭና በሀገር ውስጥ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገሩን ሰላም ዘላቂ ለማድረግ ከግጭትና ከጥላቻ ፊቱን ወደ ልማት መመለስ መቻል አለበት።


# የመጀመሪያ ዙር የሐራጅ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሀዋሳ ዲስትሪክት በአዋጅ ቁጥር 97/90 (እንደተሻሻለው) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለሰጠው ብድር ለመያዣነት የያዘውን ከዚህ በታች የተጠቀሰውን ንብረት ባለበት ሁኔታ በሐራጅ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ. | የተበዳሪው ስም | የአስያዡ ስም | አበዳሪው ቅርንጫፍ | የቤቱ (ሕንፃው) አገልግሎት | ህንፃው የሚገኝበት አድራሻ | | | | | መነሻ ዋጋ (በብር) | ሐራጁ የሚካሔድበት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ከተማ | ክ/ከተማ | ቀበሌ | የይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር | የቦታ ስፋት (በካሬ) | | ቀን | ሰዓት |
| 1 | አቶ መስፍን በቀለ | ተበዳሪው | አለታወንዶ | ለመኖሪያ | አለታ ወንዶ | - | ዴላ | 1285 | 640.0 | 1,472,469.80 | 11/03/2016 ዓ.ም | 5:00-6:00 |
| 2 | አቶ መስፍን በቀለ | ወ/ሮ ታደለች ድጋሎ | አለታወንዶ | ለመኖሪያ | አለታ ወንዶ | - | ዴላ | 2696 | 413.60 | 236,502.77 | 11/03/2016 ዓ.ም | 8:00-9:00 |
| 3 | አቶ መስፍን በቀለ | ተበዳሪው | አለታ ወንዶ | መጋዘን | አለታ ወንዶ | - | ዴላ | 665 | 30.0 | 258,525.44 | 11/03/2016 ዓ.ም | 9:00-10:00 |
| 4 | አቶ መስፍን በቀለ | አቶ መሳይ መስፍን | አለታ ወንዶ | ለመኖሪያ | አለታ ወንዶ | - | መሳለሚያ | 2301 | 318.0 | 1,723,818.17 | 11/03/2016 ዓ.ም | 10:00-11:00 |
| 5 | አቶ በላይ ቶጋ | ተበዳሪው | አሮሬሳ | ለመኖሪያ | ሀዋሳ | ታቦር | ሂጣታ | 18887 | 200.0 | 2,364,686.46 | 18/03/2016 ዓ.ም | 4:00-5:00 |
| 6 | አቶ በላይ ቶጋ | ተበዳሪው | አሮሬሳ | ለመኖሪያ | መጀ | - | 01 | 511/2002 | 510.0 | 984,611.18 | 21/03/2016 ዓ.ም | 4:00-5:00 |
| 7 | አቶ በላይ ቶጋ | ተበዳሪው | አሮሬሳ | ለመኖሪያ | መጀ | - | 01 | 1495 | 330.0 | 210,143.54 | 21/03/2016 ዓም | 8:00-9:00 |

1. ማንኛውም ተጫራች ወይም ህጋዊ ወኪሉ የሐራጁን መነሻ ዋጋ 1/4ኛውን በጥሬ ገንዘብ ወይም በሲ.ፒ.ኦ. በማስያዥ መጫረት ይችላል፡፡
2. አሸናፊው ያሸነፈበትን ቀሪ ገንዘብ በ15 ቀናት ውስጥ አጠቃሎ ካልከፈለ ለሐራጅ መነሻ ያስያዘው ገንዘብ አይመለስለትም፡፡ ሐራጁም ተሰርዞ ሌላ ሐራጅ ወጥቶበት ሲሸጥ የሐራጅ ሽያጭ ዋጋ ከቀድሞው ሽያጭ ዋጋ ከቀነሰ ልዩነቱንም ለመክፈል በህግ ይገደዳል፡፡
3. ከተራ ቁጥር 1-4 ባሉት ንብረቶች ላይ ሐራጁ የሚካሔደው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በአለታ ወንዶ ቅርንጫፍ በግልጽ ጨረታ የሚሸጥ ሲሆን በተራ ቁጥር 5 ላይ ባለው ንብረት ላይ ሀዋሳ ዲስትሪክት በሠራተኞች ክበብ ይሆናል፤ ከተራ ቁጥር 6-7 ባሉት ንብረቶች ላይ ሐራጁ የሚካሄደው አሮሬሣ ቅርንጫፍ ግቢ ውስጥ ነው።
4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ሆነ የንብረቱን ስም ዝውውር ወጪዎችን ገዥው ይከፍላል፡፡
5. ንብረቱን ተጫርቶ ያሸነፈና ከፊል ብድር ለመውሰድ ለሚፈልግ ተጫራች የባንኩን የብድር መስፈርት ለሚያሟላ ገዥ የብድሩን ሁኔታ ባንኩ ሊያመቻች ይችላል፡፡
6. የጨረታው አሸናፊ የሚታወቀው የቀረበውን ዋጋ ባንኩ መቀበሉን ለገዥው(ለአሸናፊው) በጽሁፍ ሲያረጋግጥለት ነው፡፡
7. ባንኩ ሐራጁን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
8. የንብረቱን ሁኔታ በአካል በመገኘት መጎብኘት ይቻላል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር 046-220- 6136 ወይም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሀዋሳ ዲስትሪክት 1ኛ ፎቅ ወርክአውት ሎን ክፍል በግንባር ቀርቦ መጠየቅ ይቻላል፡፡

# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሀዋሳ ዲስትሪክት

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## ከወደቅንበት ተነስተን አባራችንን እናራግፍ

**ግለ ሂሳዊ መሬር ወግ፤**

"የድልና የስኬትህን ዜናና ትርክት አዘግይተህ፤ በተሸነፍክበት ውድቀትና ድካም ላይ በርትተህ ጀግን!" የሚለውን ብሂል አዘውትረው የሚጠቀሙበትና ለሕይወታቸውም እንደ ዋና መርህ የሚገለገሉበት "የእስያ ነብሮች" ወይንም "የእስያ ድራጎኖች" በመባል የሚታወቁት የሩቅ ምሥራቆቹ የደቡብ ኮሪያ፣ የሲንጋፖር፣ የታይዋንና የሆንግ ኮንግ ሀገራት ዜጎች ናቸው።

በኢኮኖሚ ግስጋሴያቸውና በእድገታቸው ሽምጥ እየጋለቡ ያሉትን እነዚህን ሀገራት እግር በእግር እየተከተሉ ያሉት "ታዳጊዎቹ የነብር ደቦሎች ‹ግልገሎች›)" (ታይላንድ፣ ፊሊፒንስና ኢንዶኔዢያን የመሳሰሉት ሀገራትም) በእርምጃቸው ፈጠን ፈጠን እያሉ "በአቦ ሸማኔ ፍጥነት" ሽምጥ እየጋለቡ ያሉትን ጎረቤቶቻቸውን ሳይርቁ በቅርበት ሊደርሱባቸው በግስጋሴ ላይ ናቸው። ስለዚህም ነው በነብር ግልገልነት የተመሰሉት።

ከላይ የተጠቀሱት "ነብሮች ወይንም ድራጎኖች" በመሮጫቸው መም ላይ ቆመው ኢኮኖሚያቸውን ወደፊት ለማስፈንጠር ቃል ኪዳን በመግባት ለዕድገታቸው የመሠረት ድንጋይ የጣሉበትን እ.ኤ.አ 1960 ዓ.ምን መነሻ ብናደርግ እንኳን እነዚህ ሀገራት ዛሬ ለደረሱበት ከፍተኛ የኢኮኖሚና የተጽእኖ ፈጣሪነት ደረጃ ላይ ሊደርሱ የቻሉት በስድስት ዐሥርት ዓመታት ጊዜ ውስጥ መሆኑን ታሪካቸው ምስክር ነው። የዕድገታቸው ምሥጢር ደግሞ ለትምህርት ሥርዓታቸው የሰጡት ተቀዳሚ ትኩረት ነው።

ሀገራቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለ እድገታቸው የሚሞካሹትና አንቱታን ያተረፉት በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች መሆኑን የጥናት መረጃዎችን ጭምቅ ሃሳብ (Summary) ዋቢ ማድረግ ይቻላል፡- "Hong Kong and Singapore are among the most prominent worldwide financial centers, while South Korea and Taiwan are essential hubs for the global manufacturing of automobile and electronic components, as well as information technology... these Tigers share common characteristics, including a sharp focus on exports, an educated populace, and high savings rates."

በዓለም ቀዳሚ የኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ በሁለተኛነትና በሦስተኛነት የተሰለፉት ቻይናና ጃፓንም እንዲሁ ከላይ የተጠቀሰውን ብሂል ሕዝባቸው በመርህነት እንዲመራበት "ስላሰለጠኑት" እነሆ ለራሳቸው በቅተው ለእኛም እስከ መትረፍ ደርሰዋል። ሀገራቱ በአብዛኛው ትርክቶችን ሲቀምሩ ውለው የሚያድሩት የትምህርት ሥርዓታቸውን ሌት ተቀን እያዘመኑ እድገትና ብልጽግና እንዴት የሀገራቸው እሴት እንደሚሆን እንጂ እንደኛ ካለፈው ታሪክ የማያግባባ ትርክቶችን በመፈልፈል ራሳቸውን እየተበተቡ አይደለም። በእኛ ዘንድ ዋጋ አጥቶ የረከሰው "መማር ያስከብራል፤ ሀገርን ያኮራል" የሚለው ዓይነት "የጥንት" እንጉርጉሮ ለእነርሱ "እንደ ብሔራዊ መዝሙር" በየዕለቱ የሚያቀነቅኑትና የሚግባቡበት ብሂል ብቻ ሳይሆን የዕለት ተዕለቱን ሕይወታቸውን የሚመሩበት መርሃቸው ጭምር ነው።

ልዩነቱ እኛ ከትናንት ታሪኮቻችን ውስጥ በእንክርዳድ የምንመስላቸውን የነበር ዘለላዎች እየመዘዝንና እየነቀስን አዳዲስ የሚያጋጩና የሚያናንቁ "አስካሪ" ትርክቶችን ስንጠምቅ፤ እነርሱ ግን ነባር ታሪኮቻቸውን በክብር አቆይተው ሲጨነቁና ሲመክሩ የሚውሉት ለዛሬውና ለነገው እድገታቸው የሚረዷቸውንና የሚያግዟቸውን አዳዲስ ሃሳቦች እንዴት በተግባር ላይ እንደሚያውሉ ነው።

እኛ ያልኖርንበትን ዘመን፣ የዘመኑን ታሪክና "ታሪክ ሰሪዎቹን" የዘመኑን ሰዎች ፍርድ ቤት ካላቆምን እያልን ያዙኝ ልቀቁኝ እያልን ለገላጋይ ስናስቸግር እነርሱ ግን "የነበራቸውን" በአግባቡ እየተፈተሹ ዛሬያቸው ላይ ታሪክ በመሥራት ተጠምደዋል። እኛ ግባ መሬታቸው ከተፈጸመ ሙታን አጽሞች ጋር "ይህንንና ያንን ሠርተው አልፈዋል" በማለት ግብግብ ካልገጠምን እያልን መቃብራቸውን ስንቆፍር እነርሱ ግን ለህያዋን ዜጎቻቸው ሕይወታቸውን ለማስዋብ ይጨነቃሉ።

ይህ ጸሐፊ አራት ዓመታትን በውጭ ሀገር አብሮ ከተማረው የኮሌጅ ጓደኛው የቀሰመውን አንድ እውነት ለመመስከር ርዕሰ ጉዳዩ ስለሚፈቅድለት እዚህ ቦታ ቢያስታውሰው ተገቢ ይሆናል። ይህ ታይዋናዊ ጓደኛው ቺሆንግ ኪ. ይባላል። ይህ ሰው ቀንም ሆነ ሌሊት እረፍት ነስቶት የሚያብከነክነው የሀገሩ ሥልጣኔና እድገት ጉዳይ ነበር። ከትምህርት ሰዓት ውጪ ውሎው ፋብሪካዎችንና ኢንዱስትሪዎችን መጎብኘት፣ የቴክኖሎጂ ተቋማትን ማሰስ፣ አዳዲስ የሸቀጥ ምርቶችን ማጥናትና አሠራራቸውን መመርመር ነበር። በተለየ ሁኔታ ግን ለአዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የነበረው ፍቅርና አትኩሮት በልዩ ሁኔታ የሚያስገርም ነበር።

የዚህን የጓደኛዬን ጥረትና ትጋት አዘውትሬ ስለማስተውልም፡- "ከትምህርትህ እኩል ትኩረት የምትሰጥበት ይህ የዕውቀት ኀሠሣ ትጋትህ ምክንያቱ ምንድን ነው?" ብዬ በጠየቅሁት ዕለት የሰጠኝ መልስ እንዲህ የሚል ነበር፤ "ሀገሬ ታይዋን አሜሪካን ድረስ ልካ ያስተማረችኝ የወረቀት ማስረጃ ይዤ እንድመለስ ብቻ ሳይሆን ለሀገሬ እድገትና ብልጽግና የሚበጅና የሚረዳ የቴክኖሎጂ ዕውቀት ቀስሜ እንድመለስ ጭምር ነው።

ትምህርት ብቻ ቢሆንማ በሀገሬ ያሉት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በምንም መልኩ በጋራ እየተማርንበት ካለው ከዚህ ዩኒቨርሲቲ የሚተናነሱ አይደሉም። የእኔ ተልዕኮ በአንድ የዕውቀት ዘርፍ ሰልጥኖ መመረቅ ብቻ አይደለም። ሀገሬ ምን ይዘህ መጣህ ብላ ለምትጠይቀኝ ጥያቄ መልስ ማዘጋጀት ስላለብኝ አንዲትም ደቂቃ ቢሆን ጊዜዬን ለማባከን አልፈልግም።"

ይህ "ትንግርተኛ" ጓደኛዬ ትምህርቱን ጨርሶ እንደተመለሰ በርግጥም ሀገሩ የተቀበለችው በከፍተኛ ክብርና አድናቆት መሆኑን ከምንጻጻፈው እውነታ ተረድቻለሁ። የእኔ ሀገር ግን ተምረውም ሆነ በግላቸው ሀብት ትንሽም ቢሆን ለሀገሬ አስተዋጽኦ ላድርግና ላገልግላት ብለው የባዕድ ሀገር ኑሯቸውን እርግፍ አድርገው የሚመጡትን ልጆቿን እንኳንስ በክብር ልትቀበላቸው ቀርቶ እንደ ጥፋተኛ ሕጻን "ምን ልትፈይዱ ሀገር ብላችሁ ተመለሳችሁ?" በማለት "በቢሮክራሲና በንቀት ልምጭ ቆሌያቸውን ገፋ" ፊት እንደምትነሳቸው ከዚህ ጸሐፊ በተጨማሪነት የብዙዎችን ተመሳሳይ ምስክርነት ማድመጥ ይቻላል። ይህን ጉዳይ ለጊዜው "በሆድ ይፍጀው" ትዕግሥት በይደር ማስተላለፉ ይበጃል።

"ሀገሬን ካልጎበኘህልኝ" በማለት በስንት ውትወታ ገፋፍቼ የጋበዝኩት ሌላኛው የተሳካለት አሜሪካዊ ወዳጄም እንዲሁ ለኢትዮጵያ በጎ ለመዋል አስቦ ፕሮጀክቶች ቀርጾና ሀብቱን ይዞ አደራ ያልኩትን ሕዝቤን ለማገልገል ጨክኖ መጥቶ በሙስናና በክፋት የቆሸሸው ቢሮክራሲ አላላውስ ብሎት ተስፋ መቁረጡን የገለጸልኝ እንዲህ በማለት ነበር። "ሀገርህ በውብ ታሪኮች ያሸበረቀች መሆኑ እውነት ቢሆንም የቢሮክራሲያችሁ ቆሻሻ ግማት ግን እንኳን ለባዕዳን ቀርቶ ለእናንተ ለተወላጆችም የሚከረፋው ሽታ የሚያስቀርብ ስላይደለ ፕሮጀክቴን ወደ ኬኒያ ለማዘዋወር ተገድጃለሁ።" በእጅጉ ልብ ሰባሪ ክስተት ነበር።

እንደ ክፉ ልክፍት የተጠናወተን ብሔራዊና መልከ ብዙ የመገፋፋትና የመናናቅ አዚም መገለጫው የትዬለሌ የሚባል ዓይነት ስለሆነ ልክ እንደ ቅዱስ መጽሐፉ ናቡከደነፆር "ሕልሙም ፍቺውም ጠፍቶብን" ሕልም ተርጓሚዎችን የምንፈልግባቸው ጉዳዮቻችን ብዙዎች ናቸው። ከብዙዎቹ መካከል በአባራ የሚመሰለውን አንድ ጉዳይ ብቻ አስታውሼ እንደተለመደው ኢትዮጵያችን ወደ ዕድገት ማማ ከፍ እንዳትል ያሽመደመዳትን ልክፍት ለማሳያነት በማመላከት አንድም ፈጣሪ ፊቱን መለስ እስኪያረግልን፣ አንድም ቅጥ አንባሩ የጠፋበት ወፈፌው ፖለቲካች ሰክኖ እስኪያስክነን ድረስ በቁዘማ እህህ ማለትን እንቀጥል።

**የትምህርት ሥርዓታችን "መጭ"፤**

መጭ ሳይፈለግ የሚበቅል ኑግ መሰል ባዕድ የአዝዕርት አይነት ነው። "ሀገር ሲያረጅ መጭ ያበቅላል" መባሉም ስለዚሁ ነው። "ሀገር ሲያረጅ ጃርት ያፈራል" የሚለው ብሂልም የላይኛው አባባል መንትያ ጓደኛ ነው። የሀገሬ የትምህርት ሥርዓት ዛሬ ላይ ጣፋጭ ፍሬ ከማፍራት ይልቅ "የመጭ አዝመራ" ወደ ማምረት ደረጃ ላይ የተሸጋገርንበትን ምክንያት መመርመሩ ጊዜ የማይሰጠው ብሔራዊ ጉዳያችን ይመስለናል። የትምህርቱ ሥርዓት የወረሰውን አባራ አራግፎን በተቻለ መጠን ተንገዳግደንም ቢሆን በመቆም ሀገሪቱን ካልታደግን በስተቀር የነገዋ ኢትዮጵያ መልክ ምን ሊመስል እንደሚችል ለመተንበይ አይገድም።

በቅርቡ ለሁለተኛ ጊዜ ድፍረት ተሞልቶበት ይፋ የተደረገው የሀገሪቱ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤት ሀገርን ብቻ ሳይሆን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወላጆችንና ዜጎችን ማቅ ያለበሰ ብሔራዊ ሀዘን ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ከወላጆችም አልፎ ተርፎ ዋነኞቹን ባለጉዳዮች ተማሪዎችን፣ መምህራንንና የትምህርት አስተዳደር ባለሙያዎችን አንገት ያስደፋና መሳለቂያ ያደረገ ውጤት ነው ቢባልም ግነት አያሰኝም። አንድ ሁለት ዓለም አቀፍ ዜናዎች እየተሳለቁብን የሠሩትን ዜና እንዳልደገመው "ከሰደበኝ መልሶ የነገረኝ ገደለኝ" እንዳይሆንብኝ ጉዳችንን አምቄ መያዙን መርጫለሁ።

"በ2015 ዓ.ም ብሔራዊ ፈተና ከወሰዱት 845,099 የሀገሪቱ ተማሪዎች መካከል 50 ከመቶና በላይ ያመጡት ተማሪዎች ቁጥር 27,267 ወይንም 3.2% ብቻ ነው። ብሔራዊ ፈተናውን ካስፈተኑ 3,106 ት/ቤቶች መካከል 1,328 (42.8%) ት/ቤቶች አንድም ተማሪ ማሳለፍ አልቻሉም" የሚለው ሪፖርት የተደመጠበትን ዕለት እንደዚህ ጸሐፊ እምነት ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ዝቅ ብሎ እየተውለበለበ የሀዘን ቀን ሆኖ ቢውል ተገቢ ነበር ብዬ አምናለሁ። ለሀዘኑ ከፍታ ለመጨመር ካስፈለገም መምህራኑና በየደረጃው ያሉ የትምህርት ሥርዓቱን የሚመሩት ኃላፊዎችም ጥቁር በጥቁር ለብሰው ለቅሶ መቀመጥ ነበረባቸው።

መቼም ብሔራዊ ማመካኛ ስለማይጠፋ ብዙ ሰበብ አስባቦች መስጠትን ስለተካንበት እንጂ እንዲህ ዓይነት ብሔራዊ ውድቀት ሲከሰት ቁንጮዎቹ የትምህርት አመራሮች በሕዝቡ ፊት በይፋ ንስሐ ገብተው ኃላፊነታቸውን በመልቀቅ ራሳቸውን ማዋረድ ነበረባቸው። ዳሩ "ማንን ወንድ ብለሽ" እንዳለችው ሆደ ባሻ እንስት መሆኑ በጃቸው።

ይህ ጸሐፊ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጠንከር ብሎ ለመሄስ ብዕሩን ያደፋፈረው ለትምህርት ሥርዓቱ ይነስም ይብዛ የዜግነቱን አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ስለሚሰማው ነው። በዘመነ ወጣትነቱ በሁለት የሀገራችን ተጠቃሽ ትምህርት ቤቶች (ጄኔራል ዊንጌት እና ሕይወት ብርሃን የልጃገረዶች ትምህርት ቤት) በትርፍ ሰዓት በመምህርነት ለዓመታት ያህል አገልግሏል። ከዝቅተኛ ክፍሎች እስከ ከፍተኛ ክፍሎች ዛሬም ድረስ በአገልግሎት ላይ ያሉት በመቶዎች የሚቆጠሩ መጻሕፍት ሲዘጋጁም በአስተባባሪነትና ራሱም ጸሐፊ በመሆን አገልግሏል።

ምንም እንኳን በስም እንጂ በግብር እንደሚገባ ባይሰራበትም "የፀረ ኩረጃ አምባሳደር የመሆን ማዕረግም" ከወቅቱ የፈተናዎች ኤጀንሲ አደራ ተሰጥቶት አሰሪ በመጥፋቱ ማዕረጉ በከንቱ ባክኗል። በዚህ አንጋፋ ጋዜጣ ላይም በሀገራችን የትምህርት ጉዳይ ላይ የአቅሙን ያህል ሃሳብ ከመሰንዘር አልቦዘነም። ስለዚህ አስተያየቱ ጠንከር ቢል ምክንያት አለው ለማለት ነው።

ለመሆኑ ለሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት እንዲዚህ ለመዝቀጡ ተጠያቂዎቹ እነማን ሊሆኑ ይገባል? ወፈፌ ፖለቲካችን ነው? የካሪኩለም ቀረጻና አተገባበሩ ነው? ተገቢ የትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦት ችግር ነው? ከፈተና አዘገጃጀትና ከምዘና ጋር ያልተጣጣመ መርህ ውጤት ነው? የወላጆች ችግር ነው? የተማሪዎች የሥነ ልቦና አገነባብ፣ የሰብዕና ግንባታ መዛነፍና በነገ ተስፋቸው ላይ እምነት ማጣት ነው? የትምህርት አስተዳደሩ አንካሳነትና የመምህራኑ አቅም ማነስና ከሙያ ፍቅር ጋር የተያያዘ ችግር ነው? ወይንስ ሌላ የተሰወረብን ብሔራዊ ዓይነ ጥላ ተጠናውቶናል?

ምንም እንኳን በፈተና የመውደቅና የማለፍ ጉዳይ ያለ፣ የነበረና ወደፊትም የሚኖር እውነታ ቢሆንም "በጅምላ" ወድቃችኋል ተብሎ የተፈረደባቸውን የሀገሪቱን ልጆች ሞራል እንደምን ማስጠበቅ ይቻላል? "አንድም ተማሪ ማሳለፍ አልቻላችሁም" ተብለው አንገት የደፉት የ1,328 ትምህርት ቤቶች የወደቀ ሞራልስ በምን ዘዴ ተገንብቶ "ዳግመኛ ት/ቤት ሊባሉ" ይችላሉ። የተማሪዎች ወላጆች፣ መምህራንና የትምህርት አስተዳደሩ ጉዳይስ መፈተሽ የለበትም? የእስከዛሬ የፈተና ምዘናው የጉዞ እርምጃ በዚሁ መቀጠል ይኖርበታል? የትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦት ችግርስ "ብሔራዊ የማመካኛ ሰበብ" ሆኖ እስከ መቼ ሊቀጥል ይችላል?

መቼም ፈታኝም ቢሆንም በሚመጥነው ልክ በጥያቄዎች ሊሞገት ስለሚገባው የትምህርት ሥርዓታችንን የወረሰው አባራ እንዲራገፍ ካስፈለገ በእነዚህና በመሳሰሉ "ብሔራዊ አባራዎቻችን" ላይ ሳንሸኮረመም ተወያይተን መፍትሔው ላይ መስራት ይኖርብናል። "መማር ያስከብራል ሀገርን ያኮራል" እያሉ ያስጨበጨቡን የጥንቶቹ ዘማሪዎች በሕይወት ኖረው ከሆነ ዛሬ በስተእርጅና ዘመናቸው የትምህርት ውድቀታችንን መርዶ በሰሙ እለት ምን ብለው ይሆን? ሰላም ለሀገራችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ነውርነት - በሕጋዊነት

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ምሳ ሰአት ነው። በርካታ ታዳሚ ከምግብ ቤቱ ቅጥር ተገኝቷል። ወጪ ገቢው በሚተራመስበት ሰፊ አጻድ ቦታ ይዘው የሚመገቡ ፣ ያዘዙትን ምግብ በተስፋ የሚጠብቁ ብዙ ናቸው። ከእነሱ ጠረጴዛ የቅርብ ርቀት የሚገኘው የእጅ መታጠቢያ እንደልማዱ በሰዎች አጀብ ተከቧል። በልተው የጨረሱና ገና ለመብላት ያሰቡ ተመጋቢዎች ፊትና ኋላ ተሰልፈውበታል ።

በልተው ከጨረሱት አብዛኞቹ እጃቸውን እየታጠቡ ለሌሎቹ ይለቃሉ። አንዳንዶች ግን ከኋላቸው የቆሙትን ፍጹም የረሱ ይመስላል። እጃቸውን ቀስ እያሉ ያሻሉ ። ውሃ እየጨመሩ መልሰው መላልሰው ይታጠባሉ ። ጠባቂዎቹ አሁንም እንደቆሙ ናቸው።

እጅ ታጣቢዎቹ ጨርሰዋል ሲባል ደግመው ሳሙና ያነሳሉ። ውሀውን እየጨመሩ፣ በዝግታ እየታጠቡ ይቆያሉ። አንዳንዱ በትዕግስት ይጠብቃል። ሌላው በንዴት ይቁነጠነጣል ። እነሱ ግን የማንም ስሜት ምናቸውም አይደለም ። ይባስ ካቀረቀሩበት ቀና ብለው ከፊት ለፊታቸው መስታወት መልካቸውን አየት፣ ጸጉራቸውን ነካ፣ነካ እያደረጉ በዝግታ ይጎነበሳሉ።

ይህን ሁሉ ጨርሰው መለስ ባሉ ጊዜ ከኋላቸው የተሰለፈውን ወረፋ ጠባቂ ማየታቸው አይቀርም። እነሱ ግን ድንጋጤና ሀፍረት አይነካቸውም። ከበባውን ጥሰው ፣ ሰልፉን አቋርጠው እየነጠሩ ይሄዳሉ ።

ወዳጆቼ ! አሁንም ከምግብ ቤቱ ሰፊ ግቢ አልወጣሁም ። ‹‹ዓይን አያሳየው የለም ›› እንዲሉ ሆኖ በየቀኑ የማስተውለን ጉዳይ ዛሬም እንዲሁ እየታዘብኩ ነው ። ሰውዬው ምሳውን በልቶ እንደጨረሰ ወደ እጅ መታጠቢያው አምርቷል። ውሀውን ከፍቶ እጆቹን ከታጠበ በኋላ በዛ መከረኛ መስታወት ፊቱን አየት አድርጎ መልሶ አቀርቅሯል ።

ዛሬም በግቢው ዙሪያ የተሰበሰቡ በርካታ እንግዶች የምሳ ገበታ ይዘዋል። አዲስ የሚገቡ ደንበኞችም የሚያሻቸውን አዘው በመጠባበቅ ላይ ናቸው። የሰውዬው ወደ መታጠቢያው ማቀርቀር ለእጅ ጽዳት ብቻ አልሆነም። ውሀ በአፉ ሞልቶ ጉሮሮውን ለማጽዳት እየሞከረ ነው።

ይህን እንደጨረሰ ከአፉ የቀረውን የምግብ ቅንጣት በጣቶቹ እያጸዳ አፍንጫውን ይናፈጣል። መናፈጥ ሲባል እንዲህ በዋዛ አይምሰላችሁ ። ‹‹ እንፍ፣ እንፍ ፣ እንፍ..... ›› እየደጋገመ ። ወዲያው በእጁ የያዘውን ነውር ከፊት መታጠቢያው አዝረክርኮ መልሶ ጉሮሮውን ያፀዳል።

ደረቱን ይዞ ወደ አፍንጫው የሚስበው ትንፋሽ ታዲያ በዝምታ የሚወጣ አይደለም። ደጋግሞ ‹‹አክ አክ ..›› ሲለው ለተመጋቢው ጆሮ ፈጥኖ የመድረስ ኃይል አለው ። ድርጊቱን አስተውለው ሁኔታው ያልተመቻቸው እንግዶች ፊታቸው ሲኮሳተር ይታያሉ። የዓይናቸውን እውነት በትዝብት ብቻ ማለፍ የማይሹት መብላት የጀመሩትን ከእጃቸው ጥለው ቦታውን ለቀው ይሄዳሉ። ሰውዬው ግን ይቀጥላል። ‹‹እንፍ ፣ እንፍ፣ እንፍ ››

እንግዲህ ይህ የሚሆነው ሰዎች ምግብ በሚበሉበት ፣ የብዙኃን መገናኛ ውስጥ ነው ። እንዲህ አይነት ዓመለኞች ይህን ድርጊት ሲፈጽሙ ያሉበትን፣ የቆሙበትን ስፍራ የሚያስቡት አይመስልም ። ክፉ ልምዳቸውን ቀረብ ብሎ የሚነግራቸው ስለማይኖርም በስህተት መንገዳቸው ሲመላለሱ ይስተዋላል።

አንዳንዴ ደጋግመን የምንፈጽመው ልማድ ነውር መሆኑን የሚጠቁመን ከሌለ ትክክል ነን ብለን ልንቀጥልበት የሚያግደን የለም። አስተውላችሁ ከሆነ አንዳንድ የመስሪያ ቤት መጸዳጃዎች የስልክ መነጋገሪያ ቦታዎች እየሆኑ ነው ።

በተለይ እነዚህ ስፍራዎች ንጽህናቸው የተጠበቀ ከሆነ በእጃቸው ስልክ የያዙ ሰዎች ያዘወትሯቸዋል። እንዲህ መሆኑ ምናልባት የሌሎችን ሰራተኞች የሥራ መንፈስ ላለመረበሽ ይሆናል። አልያም ሚስጥር ነክ የሆኑ ጉዳዮችን አርቆ ለማውራት ጭምር ። እንዲህ ማሰቡ ጨርሶ አያስከፋም ። ለሥራ ባልደረቦች ሰላም ተጨንቆ አማራጭ መጠቀም የሚያስመሰግን ነው ።

ይህ እውነታ የሚደነቅ ሆኖ የመጠቀሚያ ቦታው ለዚህ ዓላማ አለመታሰቡ ደግሞ ሌሎችን እንዳይረብሽ ሊታሰብበት ይገባል ። እዚህ ላይ ‹‹ሌሎች›› የሚለው ቃል የመጸዳጃ ቤቱ ተጠቃሚዎች በሚል ይታሰብልኝ።

አዎ! በዚህ ስፍራ የመጀመሪያ መብት ያላቸው የመጸዳጃ ቤቱ ተጠቃሚዎች ናቸው። ስፍራውን ሊገለገሉበት ሲመጡ በዙሪያቸው ሰዎች መኖራቸውን አይተው ሊሸማቀቁ አይገባም። ግልጹን እናውራ ከተባለ ብዙ ጊዜ ስልክ የሚያወሩ ሰዎች መጸዳጃዎችን መምረጣቸው የተጠቃሚዎችን የቆይታ ጊዜ የሚያሻማ ነው።

እንደ እኔ ዕምነት ስልኩን የሚያወራው ወይም በዝምታ የሚያዳምጠው ሰው ‹‹ሄደ አልሄደ›› በሚል ተጠቃሚው መሳቀቅ አይገባውም። በመጸዳጃው እንዳሻው የመጣበትን ፈጽሞ ለመውጣት ነጻነቱ ሊኖረው ይገባል እንጂ ።

የመጸዳጃ ቤቱን ጉዳይ ካነሳነው አይቀር የጥቂት ጽዳት ሰራተኞችን ልማድም ጠቆም ማድረጉ አይከፋም። የጽዳት ሰራተኞች ሁሌም የመጸዳጃ ቤቶችን ንጽህና ለመጠበቅ በእጅጉ የሚተጉ ናቸው። የእንጀራ ጉዳይ ሆኖባቸው እንጂ የአንዳንድ ተጠቃሚዎች ያልተገባ ልማድ ከእነሱ አልፎ ለሌሎች ጭምር እንደሚያበሽቅ አናጣውም። እነሱ ሁሌም ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያደርጉት ጥረት በእጅጉ ያስመሰግናቸዋል።

አንዳንዴ ግን አንዳንድ የጽዳት ሰራተኞች ስራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከስፍራው መራቅን አይሹም። በየአፍታው ለማጽዳት እንዲያመቻቸው ይመስላል የመጸዳጃ ቤቶቹን የመግቢያ በሮች አይለቁም። እንደውም አንዳንዴ ጥሩ ወንበር ይዘው ከበራፉ ተቀምጠው መዋል ምርጫቸው ይሆናል ።

ችግር የሚሆነው የእነሱ ተቀምጦ መታየት አይደለም። አሁንም መጸዳጃውን መጠቀም የሚሻ ሰው ቢኖር እነሱን አልፎ ለመግባት ይቸገራል። ከዚህ ባለፈ ወደ ውስጥ ዘልቆ የልቡን መሻት ለመከወን ሙከራው ነውር መስሎ ሊታየው ሁሉ ይችላል። ተጠቃሚው ለጊዜው ‹‹ይቅርብኝ›› ብሎ ቢተወው እንኳን ሰራተኞቹ ለአፍታ ከስፍራው ዞር ካላሉ ተቸግሮ መዋሉ አይቀሬ ይሆናል ።

እንግዲህ እንዲህ አይነቶቹ ልማዶች ቀላል የሚመስሉንና በየዕለቱ የምናያቸው ስህተቶች ናቸው። ልማዶቹ ከዚህም ባለፈ ነውር ብለን ስያሜ ብንሰጣቸው የሚበዛባቸው አይሆንም። እነዚህ አጓጉል ጉዳዮች በአንድም በሌላም በሌሎች የሚፈጸሙ አልያም እኛው የምናደርጋቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ነውር መሆናቸውን ልቦናችን ቢያውቅም ደፍረን እንደምንፈጽመው ሁሉ ቆርጠን ለመተው የምንቸገርባቸው ይሆናሉ።

መቼም ከእስከዛሬው ልምዳችን በማህበረሰቡ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የትኛው በጎና ነውር መሆኑ አይጠፋንም ። ብዙ ጊዜ በቸልተኝነት ንቅን የምንተዋቸው ድርጊቶች ግን ከመተዛዘብ አልፎ የሌሎችን ሥነ ልቦና እስከ መጉዳት ይሄዳሉ።

ነውርነትን ህጋዊ ባደረግነው ቁጥር ትክክል የሆንን መስሎን ለሌሎች ክፉ አርአያ እንሆናለን። እንዲህ በሆነ ጊዜ ራስ ወዳድነት ይበረታል። ስህተቶች ሳይታረሙ እንዲጓዙ ያስገድዳል ። ይህ እንዳይሆን ከድርጊት በፊት ቆም ብለን ማሰቡ አይከፋም። አስቀድሞ ማሰብ መተሳሰቡ ለሁላችንም ይበጀልና አበቃሁ !

# ዓለም አቀፍ



## ቻይና የሩሲያን ጋዝ በመግዛቷ 10 ቢሊዮን ዶላር ማትረፏ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ቻይና የሩሲያን ጋዝ በመግዛቷ 10 ቢሊዮን ዶላር ማትረፏ ተገለጸ፡፡

ሩሲያ ጦሯን ወደ ዩክሬን መላኳን ተከትሎ በአሜሪካ፣ አውሮፓ ህብረት እና ሌሎች ሀገራት ከ12 ሺህ በላይ ማዕቀቦች ተጥለውባታል፡፡ በማዕቀቡ ምክንያትም ዋነኛ የነዳጅ ግብይት ስትፈጽምባቸው የነበሩ የአውሮፓ ሀገራትም ፊታቸውን ወደ ሌላ ሀገራት ሊያዞሩ ችለዋል፡፡

ሌላኛዎቹ ኢራን እና ቬንዙዌላም በምዕራባዊያን ሀገራት ማዕቀብ የተጣለባቸው ሀገራት ሲሆኑ፤ ሀገራቱ በዋናነት ነዳጃቸውን ለዓለም ገበያ ማቅረብ አልቻሉም፡፡ እነዚህ የምዕራባዊያን ማዕቀቦች ለዓለማችን ሁለተኛዋ ልዕለ ሀያል ሀገር ቻይና ጥሩ የገበያ እድል እንደፈጠረላት ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

እንደ ዘገባው ከሆነ በነዳጅ ሀብታቸው የበለጸጉት ሩሲያ፣ ኢራን እና ቬንዙዌላ በምዕራባዊያን ሀገራት ማዕቀብ መጣሉ ነዳጃቸውን ለቻይና ረከስ ባለ ዋጋ እንዲሸጡ አድርጓል ተብሏል፡፡ አሜሪካ የሩሲያን መከላከያ ይደግፋሉ ባለቻቸው 42 የቻይና ኩባንያዎች ላይ የንግድ ገደብ ጣለች።

በተያዘው የፈረንጆቹ 2023 ዓመት ባሉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ቻይና ከሶስቱ ሀገራት 2 ነጥብ 7 ሚሊዮን በርሜል ነዳጅ እንደገዛች ተገልጿል፡፡

ቻይና ማዕቀብ ለተጣለባቸው ሶስቱ ሀገራት ጥሩ የገበያ አማራጭ ሆናለች የተባለ ሲሆን፤ በአንጻሩ ቻይናም ያለፉክክር የሀገራቱን ነዳጅ እንድትገዛ አስችሏታልም ተብሏል፡፡

ቻይና የሩሲያን ነዳጅ በመግዛቷ ብቻ ከ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ አትርፋለች የተባለ ሲሆን፤አንድ በርሜል የቬንዙዌላን ነዳጅ በ10 ዶላር እንዲሁም አንድ በርሜል የኢራንን ነዳጅ ደግሞ በ15 ዶላር እንደገዛች ተገልጿል፡፡

## አንጋፋው የአሜሪካ የምክር ቤት አባል በግብፅ ወኪልነት አዲስ ክስ ቀረበባቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ቦብ ሜኔንዴዝ

የአሜሪካ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበር የነበሩት ቦብ ሜኔንዴዝ በግብፅ ወኪልነት አዲስ ክስ ቀረበባቸው።

አንጋፋው የምክር ቤት አባል ቦብ ሜኔንዴዝ ከዚህ ቀደም የግብፅ መንግሥትን ለመደገፍ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዶላር ጉቦ ተቀብለዋል በሚል የሙስና ክስ ተከፍቶባቸዋል።

ሜኔንዴዝ እና ባለቤታቸው ናዲን የግብፅ መንግሥትን የረዱ “የአሜሪካ መንግሥት ምሥጢራዊ መረጃ” አሳልፎ በመስጠት ነው ክስ የተመሠረተባቸው። ጥንዶቹ ከሳምንታት በፊት በአሜሪካ የፍትሕ መንግሥት መሥሪያ ቤት የቀረበባቸውን የሙስና ክስ ጥፋተኛ አይደለንም ብለዋል። ሴናተሩ ክሱን “ሐሰት” በማለት አስተባብለዋል።

የሴናተሩን ተጽዕኖ በመጠቀም አሜሪካ ለግብፅ የምትሰጠውን እርዳታ እና ወታደራዊ ድጋፍ ለመጨመር በተያዘው ዕቅድ መሠረት የገንዘብ፣ የወርቅ፣ የቤት ብድር ድጋፍ፣ የቅንጦት መኪና ከሦስት የኒው ጀርሲ ነጋዴዎች በመቀበል ወንጀል ዐቃቤ ሕግ ሜኔንዴዝ እና ባለቤታቸው ናዲን ላይ ክስ መሥርቷል።

ባለፈው ዓመት በኒው ጀርሲ የሚገኘው የሴናተሩ መኖሪያ ቤት ላይ በተደረገው ፍተሻ መርማሪዎች 480 ሺህ ዶላር እና 155 ሺህ ዶላር የሚገመት ጠፍጣፋ ወርቅ ተደብቆ አግኝተዋል። ሐሙስ ዕለት በኒው ዮርክ የፌዴራል ዐቃብያነ ሕጎች የቀረበው አዲስ ክስ ሜኔንዴዝ “ተጽእኗቸው እና ሥልጣናቸውን በመጠቀም የግብፅን መንግሥት በሚጠቅም መልኩ ኃላፊነታቸውን አላግባብ ተጠቅመዋል” ብሏል።

አሁን ከኃላፊነት ከተነሱበት የሴኔቱ የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ ለግብፅ እንዳይሰጥ ተይዞ ነበረ 300 ሚሊዮን ዶላር ዕርዳታ እንዲለቀቅ ሴናተሮችን አበረታተዋልም ተብሏል።

የአሜሪካ መንግሥትን ምሥጢራዊ መረጃንም አሳልፈው ሰጥተዋል ሲል ዐቃቤ ሕግ ገልጿል። በተጨማሪም ሜኔንዴዝ እና ባለቤታቸው ናዲን ከግብፅ ባለሥልጣናት ጋር በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ 'ስቴክ' ሲመገቡ የተነሱትን አዳዲስ ፎቶዎች አካቷል። ሚስታቸው ናዲንም “የእኔ ፍቅር [ሜኔንዴዝ] ሌላ ምን ሊያግዛችሁ ይችላል?” ማለታቸውንም ዐቃቤ ሕግ አክሏል።

ጥንዶቹ ባለፈው ወር ሦስት ክሶች የተመሠረቱባቸው ሲሆን፤ እነዚህም ጉቦ ለመፈጸም በማሴር፣ አገልግሎት ለማጭበርበር በማሴር እና ሥልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ገንዘብ ለማግኘት የሚሉ ናቸው።

ከአውሮፓውያኑ 2006 ጀምሮ በአሜሪካ የምክር ቤት አባልነት ያገለገሉት የ69 ዓመቱ ሜኔንዴዝ ባወጡት መግለጫ ከአዲሱ ክስ ራሳቸውን ተከላክለዋል። “በክስ ላይ አዲስ ክስ መደራረብ ክሱን እውነት አያደርገውም። በሕይወቴ በሙሉ ታማኝነቴ ለአንድ ሀገር፣ እሱም ለአሜሪካ ብቻ ነው” ሲሉ አክለዋል።

ውዝግብ ውስጥ የገቡት ሜኔንዴዝ የኒው ጀርሲ ሴናተር ኮሪ ቡከርን ጨምሮ ከ30 በላይ የዲሞክራት ፓርቲ የምክር ቤት አባላት ከአባልነታቸው እንዲለቁ ጠይቀዋቸዋል። የፔንሲልቬንያው የምክር ቤት አባል ጆን ፌተርማን አዳዲሶቹን ክሶች ተከትሎ ሜኔንዴዝ ከሕግ መወሰኛው ምክር ቤት እንዲባረሩ ውሳኔ እንዲሰጥ ጠይቀዋል። ፌተርማን በሰጡት መግለጫ “በአሜሪካ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ውስጥ ተጠርጣሪ የውጭ ወኪል ሊኖረን አይገባም” ብለዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ አማርኛ ነው።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# ሰውና የ“ከ– እስከ” ጉዞው

ግርማ መንግሥቴ

**ወደ መጣሁባት ምድር፣**
**እስክመለስባት በክብር፤**
**ሰውን ከማስደሰት በቀር፣**
**አይወጣኝም ክፉ ነገር።**
**(ተወዳጇ ድምፃዊት ብዙነሽ በቀለ)**

መጽሐፉ የሰውን ልጅ የ“ከ— እስከ” ጉዞ በግልጽ ሲያስቀምጥ “አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ” በማለት ነው። ይህ ማለት ግን እርስ በርስህ ተላለቅ፤ በወንድምህ ላይ ዝመት፣ ዘገር ነቅንቅ” . . . ማለት አይደለም፤ ፈፅሞም እንደሱ ማለት አይደለም።

ዛሬ ስለ ሰው ልጅ ጉዞ፣ እየሄደበት ስላለው መንገድ፣ እየረገጠው ስላለው . . . እንነጋገር ዘንድ ምርጫችን ያደረግነው በወቅታዊው የዓለማችን ሁኔታ ሲሆን” በተለይም ሰሞኑን በእስራኤልና ሀማስ ጦርነት ንፁሃን ላይ የወረደው ያልተጠበቀ ውርጅብኝ ነው። ስለ እስራኤልና ሀማስ/ጋዛ ጉዳይ እናወራለን ማለት ግን አይደለም። የምናወራው ጠቅለል አድርገን “ሰው” ስለተባለው ፍጡር ነው። አዎ “ሰው” ስለተባለው . . .። በፈጣሪ አምሳል ስለተፈጠረው ሰው። (“እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር፣ የባህር ዓሳዎችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዛ፡፡ እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው” ዘፍ 1፡2627፡፡)

መቼም ከላይ የጠቀስነው የብዙነሽ ዜማ ከመጽሐፍ ቅዱስ አይቀድምምና ዜማው መጽሐፍ ቅዱስን መነሻው እንዳደረገ፤ በምንጭነት እንደተጠቀመው፣ “ዋቢዬ”ባይለውም ዋቢው ስለመሆኑ በሙሉ ድምፅ መስማማት ይቻላል። በመሆኑም ሁለቱን በመሳነት ማስኬድ ይቻላል ማለት ይሆናል። እንዲሁም፣ ካስፈለገ “ክብር ለሚገባው ክብር እንስጥ” (ይህ አገላለፅ መሰረቱ መጽሐፍ ቅዱስ (ሮሜ 13፡7) መሆኑን ልብ ይሏል) የምትባልና በአንድ ወቅት የአንድ ኤፍኤም ሬዲዮ ጣቢያ መርህ የነበረችውን፤ እንዲሁም የእጅጋየሁ ሽባባው(ጂጂን)፡-

**የሰው ልጅ ክቡር**
**ሰው መሆን ክቡር**
**ሰው ሞቷል – ሰው ሲያድን፣**
**ሰውን ሲያከብር**
**በደግነት፣ በፍቅር፣ በክብር ተጠርቶ፣**
**በክብር ይሄዳል፣ ሰው ሲኖር - ሰው ሞቶ፤**

ጨምሮ እየተነጋገርንበት ስላለው ጉዳይ የኋላ ደጀን ማስከተል ይቻላል። (ጋዜጣ ሆነ እንጂ፣ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ቢሆን ኖሮ “የብዙዬንና የጂጂን ግጥሞች አንድነትና ልዩነት ፈልግ”ብሎ የክፍል ሥራ መስጠት ይቻል ነበር።)

ልክ እየተግባባንበት እንዳለው ቋንቋ ሁሉ (የ“ሪፖርተር” አምደኛ የሆኑት ታከለ ታደሰ (ዶ/ር) “የኢትዮጵያ ቁልፍ ችግር” በሚል ርእስ ባሰፈሩት ጥናት አከል ሙያዊ ጽሑፍ እንዳስቀመጡት ከሆነ የኢትዮጵያ ቁልፉ ችግር ቋንቋ ከማህበረሰብ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚመለከተው፣ የማህበራዊ ሥነልሳን (Sociolinguistics) ነው - መናናቅ፣ አንዱ አንዱን ዝቅ አድርጎ ማየት፣ የንግግር ብልግና እና ሌሎች በርካቶች)፣ የሰውን ልጅ “መወለድ”፣ “ማደግ” እና “መሞት” የተረዳው “ወደ መጣሁበት ምድር” ስንኝ ሰው ከአፈር መምጣቱን ሲያስረግጥ (“አፈር”ና “ምድር” የተለያዩ ናቸው ካልተባለ በስተቀር)፣ ለ“አፈር ነህና”ም እጁን ሰጥቶ እናገኘዋለን። “እስክመለስባት”ም በቀጥታ የተወሰደ ሆኖ የምናገኘው ሲሆን፤ ልዩነቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልፅ ያልተቀመጠው፤ ነገር ግን በስንኙ ውስጥ “በክብር” ተብሎ የተገለፀው የሰው ልጅ የ“ከ-እስከ”የሕይወት ሙሉ ጉዞ ነው።

በታላቁ መጽሐፍ “ትመለሳለህ” ሆኖ በትእዛዛዊ ቃል ይቀመጥ እንጂ “መመለስ”ከ“ጉዞ” ጋር አንድ አካልና አንድ አምሳል ናቸው። አሁንም ልዩነት አላቸው ከተባለ የባህርይው ሆኖ መጽሐፉ በጥቅል ያስቀመጠውን (በአንድምታ አይተረጎምም ማለታችን አይደለም) የብዙዬ ዜማ “በክብር” ማለቱ ነው። አዎ፣ እንደ ብዙነሽ ዜማ የሰው ልጅ ወደ መጣበት የመመለሱ ጉዳይ አይቀሬ ከሆነ፤ የመመለሱ ጉዳይ በነውር ታጥሮ፣ በነውር ሰክሮ፣ በሀጢያት ተጨማልቆ፣ ከፈሪሀ ፈጣሪ

> **እርግጥ ነው፤ “ክፉ ነገር ከአፍ ሳይወጣ መኖር ይቻላል ወይ?” የሚለው ተወደደም ተጠላ ከዲያቢሎስ በስተቀር ክፉ ነገር ከአፍ ይወጣ ዘንድ የሚፈቅድ አንድም አካል እስከ ዛሬ አልተገኘም። ይልቁንም - ባፍ ይጠፋ በለፈለፋ፤ አፍና ቅብቅብ ሁልጊዜ አያበላም፤ ካፍ የወጣ አፋፍ ... እና ሌሎችም ሥነቃላዊ እሴቶቻችን የሚነግሩን ይህንን የብዙዬን “አይወጣኝም ክፉ ነገርን ነው። ››**

ርቆ . . . ሳይሆን፤ መሆን ያለበት ከእነዚህ ሁሉ ፅድት ብሎ፣ እንዳማረበት በክብር ነው።

ብዙዬ እንደ ዋዛ “ክብር” ያለችውን መሰረታዊ ጉዳይ በተመለከተ ሊነሱ የሚገባቸው ጥያቄዎች ቢኖሩ “ይህ ክብር እንዴት ይገኛል፣ ከወዴት ይገኛል፤ በቀላሉስ ይገኛልን???” የሚሉትና የመሳሰሉት ሲሆኑ፣ ለምላሻቸውም ወደ የትም ከመሄድ በፊት እዚሁ ብዙነሽ በቀለ ዜማ ላይ በሙብሰልሰል (ሜዲቴት በማድረግ) ምላሹን ማግኘት የሚቻል ሆኖ፤ የተገኘውን ምላሽ ለማጠናከር፣ ማደንደንና ማወፈር ሲባል ከሌሎች ምንጮች ተጨማሪ መረጃዎችን መፈለግ ይቻላል።

እዚህ ጋ በክብር ወደ'ዚህ ምድር መጥታ፣ በክብር ተመልሳ ወደ መጣችበት ከሄደችው፣ ከብዙዬ ዜማ “በክብር” ለመመለስ የሚያስፈልገው መሰረታዊ ጉዳይ በዋናነት አንድ ሲሆን፤ እሱም፡-

**ሰውን ከማስደሰት በቀር፣**
**አይወጣኝም ክፉ ነገር።**

የሚለው ነው (ወይም ይሆናል)።

“ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ” (መዝ 19፥1) (እዚህ ጋ ሁለንታ (universe) የሚለውን እሳቤ ማሰላሰል ይገባል።)፤ ጆን ፓይፐር እንደ ጻፉትና አማረ ታቦር የተባሉ ሰው እንደ ተረጎሙት “ይህ የተፈጠረ ሁለንታ ምክንያቱ ለክብር ነው። የሰው ልጆች ልብ ውስጣዊ ምኞትና የሰማይ የምድር ውስጣዊ ምንነት በሚከተለው ሐረግ ሊጠቀለል ይችላል። ሁለንታ የተፈጠረው ይህንን ለማሳየት ነው፤ የእኛም ህልውና ይህንኑ ለማየትና ለመጠማት ነው። ከዚህ ያነሰው ረብ የሌለው ይሆናል። ዓለም ሥርዓት የለሽና ተግባረ ቢስ የሆነችውም በዚህ ሳቢያ ነው። የእግዚአብሔርን ክብር በሌላ ለውጠነዋል (ሮሜ 1፥23)። እዚህ ላይ “ዓለም ሥርዓት የለሽና ተግባረ ቢስ የሆነችውም በዚህ ሳቢያ ነው።” የሚለውን ከስሩ አስምረንበት ብናልፍ የሚያመልጠን ነገር የለምና እናድርገው።

(ካስፈለገም፣ ኢሳይያስ 43፥6-7፣ ሮሜ 9፥23፣ ሮሜ 5፥2፣ ዮሐንስ 17፥24 ...ወዘተርፈ በመመልከት ከጸሐፊውም ሆነ ከተርጓሚው፤ እንዲሁም ከራሳችን ጋር መግባባት ባይቻል እንኳን በጉዳዩ ላይ መብሰልሰል ይቻላል።) ይህንን ስንል “ከማንም በላይ ክብር ሊሰጠው የሚገባ እግዚአብሔር ነው” የሚለውን ዘንግተን እንዳልሆነ ሊታወቅልን ይገባል።

አሁንም ከዚሁ ከብዙዬ ስንኞች ከተገኘው መልስ ተነስቶ ሊነሳ የሚችል አቢይ ጥያቄ ሊኖር የሚችል ሲሆን፣ እሱም “ሰውን ማስደሰት እንዴት ይቻላል፣ ክፉ ነገርንስ ከአፍ ሳያወጡ እንዴት መኖር ይቻላል???” የሚለው ይሆናል። ለተሟላም ባይሆን ለከፊል ምላሹ ሙሉ የብዙዬን ዜማ ማዳመጡ (“መስማት”አልተባለም) ተገቢ መሆኑን እየጠቆምን መቻል አለመቻሉን እንመልከት።

እርግጥ ነው፣ “ክፉ ነገር ከአፍ ሳይወጣ መኖር ይቻላል ወይ? የሚለው ተወደደም ተጠላ ከዲያቢሎስ በስተቀር ክፉ ነገር ከአፍ ይወጣ ዘንድ የሚፈቅድ አንድም አካል እስከ ዛሬ አልተገኘም። ይልቁንም – ባፍ ይጠፋ በለፈለፋ፤ አፍና ቅብቅብ ሁል ጊዜ አያበላም፤ ካፍ የወጣ አፋፍ ../”እና ሌሎችም ስነቃላዊ እሴቶቻችን የሚነግሩን ይህንን የብዙዬን “አይወጣኝም ክፉ ነገርን ነው። (እዚህ ላይ እየተነጋገርንበት ያለው ጉዳይ ከዝምታ ጋር እንደማይገናኝ ልብ ማለት ይገባል።)

ርእሳችን “ሰውና የ‘ከ— እስከ' ጉዞው” (ከልደት እስከ ሞት) ሲሆን፣ ርእሰ ጉዳያችንም እንደ ረጅም ልቦለድ (ለምሳሌ፣ ፍቅር እስከ መቃብር) ከዚሁ ማእቀፍ ውስጥ ሊወጣ የሚችል አይደለም። በመሆኑም ከበደ ሚካኤል፡-

ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም፣
ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም።

እንዳሉትም ሆነ፣ ፈሪሀ ፈጣሪ ያደረባት ብዙዬ “አይወጣኝም ክፉ ነገር” እንዳለችው ፅድቅ ኖረም አልኖርም፤ ሃይማኖት ኖረንም አልኖረንም . . . ሰውን ከሰው የሚያኖረው ደግነት እንጂ ክፋት አይደለም። “ቅንነት ለራስ ነው” ይሉ አባባል የሚዘወተረው ለሌሎች ቅን በሆንን ቁጥር ለእኛም ቅን የሚሆኑ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አለመሄዱን ታሳቢ ያደረገ ሰብአዊ አገላለፅ ነው።

አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት፣ እኛም ባቅማችን እንደምናብሰለስለው፣ ዘመኑ ከእነዚህ፣ ከላይ ስንላቸው እዚህ ከደረስናቸው ሁሉ የተለየ፣ ከሁሉም የተጣላና የሰው ልጅ የአውሬ ጠባይን ያህል እንኳን እያጣ የመጣበት መሆኑ ነው። የሥነ ልቡና ጉዳይ ዘልቆ የገባቸው ሰዎች ሲሉ እንደሚሰማው የዱር አውሬ የራሱ ቤተሰብ የሆነን የዱር አውሬ (ለምሳሌ ነብር ነብር)ን አያሰቃይም፣ ለጠላት አሳልፎ አይሰጥም፤ ባጭሩ፣ ነብር ነብርን አይገድልም። ተባብሮ፣ ተረባርቦ፣ ተጋግዞ . . . እራሱንና ቤተሰቡን ከጠላት ይከላከላል እንጂ እርስ በእርሱ በጭካኔ አይጠፋፋም። በአሁኑ ዘመን ይህ እየታየ ያለው በሰው ልጅ ዘንድ ብቻ ነው።

በዛሬዋ ዓለማችን እዚህም እዛም እየታየና እየተሰማ ያለው የድምፃዊት ብዙነሽ በቀለ፡-

**ወደ መጣሁባት ምድር፣**
**እስክመለስባት በክብር፤**
**ሰውን ከማስደሰት በቀር፣**
**አይወጣኝም ክፉ ነገር።**

ሳይሆን፤ በተቃራኒው ግደል፣ ዝረፍ፣ አቃጥል፣ አውድም፣ አዋርድ፣ ክብር ለሚገባው ክብር አትስጥ፣ ወደ መጣህበት በክብር መመለስም ሆነ አለመመለስን ማሰብ ያንተ ሥራ አይደለም፤ እንደዚህ የሚሉትንም አትመናቸው፤ በገጀራ (አንገቱን) በለው . . . ወዘተ ወዘተ ነው።

ብዙነሽ “አይወጣኝም ክፉ ነገር” ትበል እንጂ፣ በአሁኒቱ ዓለማችን አየሩ በሙሉ የተጨናነቀው በጥላቻ ንግግር ነው። የሀሰት ትርክት እንደ ሰው በአካል ቆሞ ሲሄድ እየታየ ነው።

የዛሬዋ ዓለማችን በሀሰት ትርክት (ታሪክ ነገራ) ከዳር እስከ ዳር የተጥለቀለቀችበት፤ አንዱ ባንዱ ሲዝት ጀንበር የምትጠልቅበት፤ አንዱ አንዱን ሊገድል ገጀራ የሚስልበት ወዘተርፈ ሲሆን፤ ለዚህም የሰሞኑና ምንም ሳይታሰብ ድንገት የንፁሐን እስራኤላዊያንን ሕይወት የቀጠፈው የጋዛው ሀማስ ሰይፍ ነው። ከእስራኤል እየተሰጠ ያለው አፀፋም ቢሆን የንፁሐን አንገት ላይ ከማረፍ ወደ ኋላ አላለም።

ዘመናችን ወደ መጣንበት በክብር ለመመለስ የምንመኝበት ሊሆን ቀርቶ ከየት እንደ መጣን እንኳን የማናውቅበት ድንዛዜ ውስጥ ያለንበት ነው።

ዘመናችን “አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ” የሚለውን ከነጭራሹ የሚያውቅ ሁሉ አይመስልም። እራሱ ዘመኑ በእኛ ምክንያት “አብዷል”። “አይፈረድበትም” የሚሉ ወገኖች “ትክክል ናቸው” እስኪባል ድረስ አብዷል፤ ከራማው ተገፏል ማለት ይቻላል። ሶሪያዊያን ቢጠየቁ ከዚህ ውጪ ምን ሊመልሱ እንደሚችሉ ለመናገር ያስቸግራል። ሊቢያዊያንም ቢሆኑ ከሶሪያዊያን ምን እንደሚለያቸው ለመናገር አንደበት ያላቸው አይመስሉም፡፡ ደቡብ ሱዳን – ተመሳሳይ።

ጋዛና አካባቢው ላይ ሰሞኑን እየፈሰሰ ያለው ደምና እየተከሰከሰ ያለው አጥንት እየተፈፀመ ያለው “አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህን” በራሱ፤ ወይም፣ መኖሩንም በማያውቁ ሰዎች አንጎል እና እጅ ነው። በአፍጋኒስታንም እንደዛው።

**ወደ መጣሁባት ምድር፣**
**እስክመለስባት በክብር፤**
**ሰውን ከማስደሰት በቀር፣**
**አይወጣኝም ክፉ ነገር።**

በማለት፣ ከአንደበቷ እንኳን ክፉ እንዳይወጣ የመጠንቀቋን ያህል ዛሬ ሰው አውሬ እማያደርገው ተግባር መፈፀም ላይ ሲተጋ ይታያል። የሰው ልጅ ከአፈር እንደ መፈጠሩ ሁሉ በክብር ተመልሶ ወደ አፈር ያለመሄዱ ጉዳይ አሻሚ ባልሆነ መልኩ እየታየ ይገኛል።

በተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች ዘንድ “የመጨረሻው ዘመን” መምጣት እየተቃረበ እንደሆነ በተደጋጋሚ ሲነገር ይሰማል። በተለይ በፈረንጆቹ አካባቢ በ“ዘ ኢንድ ኦፍ ...”፤ “ኢንድ ታይም ፕሮፌሲ” እና በመሳሰሉ ርእሶች የተሰየሙ ድርሳናት ለአደባባይ እየበቁ ነው።

ዓለም ስጋት በስጋት ከሆነች ቆየች። መጽሐፉ (ለምሳሌ ዘፀአ.20፥ 12 (1 ኔፊ 17፥55) “አባትና እናትህን አክብር” ይበል እንጂ ያለው ሁኔታ የተገላቢጦሽ ይመስላል። ቃሉ (ዘህልቁ ምዕ·2) እየተፈፀመ ያለ ያህል እስኪመስል ድረስ መጨራረስ የትጉህን ተግባር እየሆነ ነው።

አዲስ የዓለም ሥርዓት (NWO) እየተባለ ከበሮ መመታት፣ በገና መጎሰም ከተጀመረ ቆየ። እንደ አንዳንዶች “የዋህ” አተያይ ከሆነ ይህ ለዓለምና ህዝቦቿ መርዶ እንጂ ብስራት ይዞ የሚመጣ ጉዳይ አደለም። መፍትሄው ወደ አውሬ ባህርይነት መመለስ ነው ባይ ናቸው። መፍትሄው ሁሉም የብዙዬን “ወደ መጣሁበት ምድር” በጋራ ማዜም ይገባዋል ነው የሚባለው።

በመጨረሻም፣ ሰውን በአምሳሉ የፈጠረው ፈጣሪ እንዲወለድ፣ ጥሮ ግሮ በወዙ፣ በላቡ እንዲኖር፣ ወንድሙን እንደ ራሱ እንዲወድ፣ ተፈጥሮን ያለ ምንም ገደብ እንዲጠቀም፣ ታላላቆቹን እንዲያከብር፣ እንዲማር፣ እንዲመራመር፣ ጭንቅላቱን ለተሻለ ነገ እንዲጠቀም፤ የፍጥረታት ሁሉ ገዥ እንዲሆን፤ በመጨረሻም “አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ” ባለው መሰረት እንዲሆንና ነፍሱ በገነት እንድትኖር እንጂ፤ እንዲህ እንደሚታየው እርስ በርሱ እንዲተላለቅ አልነበረም። “የማን ቤት ፈርሶ ...” እንዳለው ባለ ቀረርቶ ዓለምን ያውሬ መውለጃ ትሆን ዘንድ እንዲያመቻች አይደለም። የሰው ልጅ የ “ከ- እስከ” ጉዞ ክብ ነው የሚባለውም ለዚሁ ነው፤ ሁሉ ነገራችን ክብ። ዞሮ ክቡን ለመግጠም ግን መከራ። ሠላም!!!


በአዲሱ ዓመት
ሽክ ብለናል
ስፔሻል ይሁንልን
5.5%
የደስደስ ነው
በደሌ ስፔሻል
ALC. 5.5 VOL.
ሁለት አይነት ጌሾ
GOLD
BEDELE SPECIAL
PREMIUM BEER OF ETHIOPIA
EXPORT QUALITY

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ሌላኛው የኤሌክትሪክ ኃይል ተስፋ - የኮይሻ ግድብ ፕሮጀክት

**በኃይሉ አበራ**

የኢትዮጵያ መንግሥት የሀገሪቱ ልማት እና የሕብረተሰቡ ፍላጎት እየጠየቀ ያለውን ከፍተኛ መጠን ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል በተለያዩ አማራጮች እያመረተ ወደ ሥራ ሲያስገባ ቆይቷል፤ በአሁኑ ወቅትም ተመሳሳይ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። የኤሌክትሪክ ኃይሉን በዋናነት ከውሃ ለማመንጨት እየተሰራ ሲሆን፣ ከንፋስ፣ ከጸሀይ እንዲሁም ከእንፋሎት የኃይል አማራጮች እየተመረተ ነው።

ኃይል የማመንጨት አቅምም በሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት ወደ 17 ጊጋ ዋት ለማድረስ እየተሠራ መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በቅርቡ አስታውቋል። በቀጣዮቹ ስድስት ዓመታትም የኢኮኖሚውን ፍላጎት ማሟላት የሚችል ኃይል ከውሃ፣ ከንፋስ፣ ከፀሐይ እና ከከርሰምድር እንፋሎት ለማመንጨት ታቅዷል።

በአሁኑ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅም ከአምስት ጊጋ ዋት በላይ መድረሱን ሚኒስቴሩ ጠቅሶ፣ ይህንን አሀዝ የዓባይ ግድብ ሙሉ በሙሉ በሚጠናቀቅበት ጊዜ እጥፍ እንደሚያደርገውም አመልክቷል። በእዚህ ላይ የኮይሻና ሌሎች የኃይል ምንጮች ሲጨመሩበት በቀጣይ ስድስት ዓመታት የኢትዮጵያ ኃይል የማመንጨት አቅም 17 ጊጋ ዋት ይደርሳል።

በቅርቡ አራተኛው ዙር የውሃ ሙሌት የተደረገለት የአባይ ግድብ ግንባታ በአብዛኛው ተጠናቋል፤ ሁለት ተርባይኖች የኤሌክትሪክ ኃይል እያመነጩ ሲሆን፣ ዘንድሮም አምስት ተርባይኖች ሥራ እንደሚጀምሩ ይጠበቃል።

ሌላው በግንባታ ላይ ያለውና በኦሞ ወንዝ ላይ ግንባታው እየተካሄደ የሚገኘው የኮይሻ ግድብ ነው። ይህ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ ዞን እየተገነባ ያለው የኮይሻ ኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ገደብ ለቀጠናው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትም ተጨማሪ አቅም ያበረክታል ተብሎ ታምኖበታል። ከኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነቱ በተጓዳኝ ከኢትዮጵያ አልፎ ለቀጠናው አረንጋዴ ልማት የጎላ አስተዋፅኦ እንዳለውም እየተገለጸ ነው።


የኮይሻ ኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮጀክት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር አባይነህ ጌትነት በቅርቡ በመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት አስተባባሪነት በአካባቢው ጉብኝት ላደረገው የብዙኃን መገናኛ ባለሙያዎች እንደገለጹት፤ የኮይሻ ኃይድሮኤሌክትሪክ ፕሮጀክት በኦሞ ወንዝ ላይ ከተከናወኑት ፕሮጀክቶች አራተኛው ነው፤ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ በአንድ ጊዜ አንድ ሺህ 800 ሜጋ ዋት ኃይል፤ እንዲሁም ዓመታዊ ስድስት ሺህ 400 ጊጋ ዋት ሰዓት ኢንርጂ ያመነጫል።

ፕሮጀክቱ በሁለት ነጥብ 42 ቢሊየን ዩሮ እየተገነባ ሲሆን፣ የግንባታ ሥራው የተጀመረው የወንዙን የፍሰት አቅጣጫ እንዲቀይር ከተደረገ በኋላ ነው፤ ግንባታውም ያለማቋረጥ ለ24 ሰዓታት እየተከናወነ ሲሆን፣ አሁን ላይ የግድቡ ሥራ 38 በመቶ ደርሷል። በአሁኑ ወቅት የፕሮጀክቱ የሲቪል ሥራ 52 በመቶ፣ የግድቡ አርማታ ሙሌት 30 በመቶ፣ የማስተንፈሻው ግንባታም 13 በመቶ የደረሰ ሲሆን፣ የኤሌክትሮሜካኒካል ሥራው በጥናት ላይ ይገኛል።

የኮይሻ ግድብ ቁመቱ አንድ ኪሎ ሜትር ይጠጋል፤ ከግድቡ ወደ ኋላ 130 ኪሎ ሜትር የሚተኛ ሀይቅም ይፈጠራል። የሚፈጠረው የውሃ አካል እስከ ጊቤ ሶስት ግድብ ይደርሳል።

የ200 ሜትር ከፍታ ያለው ሲሆን፣ በRCC (Roller Compacted Concret) ቴክኖሎጂ እየተገነባ እንደሚገኝ የፕሮጀክቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ጠቅሰው፣ ለዚህም ሰባት ነጥብ ስድስት ሚሊየን ሜትር ኪዩብ አርሲሲ ያስፈልጋል ብለዋል። ግድቡ አሁን ላይ ከጠቅላላ 200 ሜትር ከፍታ ግንባታው 70 ሜትር ከፍታ ላይ መድረሱን አመላከተዋል።

ሌላኛው የፕሮጀክቱ አካል የሆነው እና 60 ሜትር ቁመት ያለው እና ከጂ + 18 ህንጻ ግንባታ ጋር አኩል የሆነው የተርባይን ማስቀመጫው ግንባታ ነው። የዚህም ግንባታ 52 በመቶ መድረሱን ምክትል ሥራ አስኪያጁ አስታውቀዋል። የዚህ የፓወር ሀውስ ግንባታ ሲቪል ስራም ተጠናቋል ብለዋል። ኃይል ማመንጫው እያንዳንዳቸው 300 ሜጋ ዋት ኃይል የሚያመነጩ ስድስት ተርባይኖች እንደሚኖሩት ጠቁመው፣ አሁን ላይ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራው በዲዛይን ደረጃ ላይ እንደሚገኝም ነው የተናገሩት።



ፕሮጀክቱ ግንባታው ተጠናቆ ወደ ሥራ ሲገባ አንድ ሺ 800 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ያመነጫል

እሳቸው እንዳሉት፤ ከፍተኛ የውሃ ክምችት በሚኖርበት ወቅት የሚያስፈልገው የማስተንፈሻ ግንባታ ሥራም የፕሮጀክቱን መዋቀር በማይጎዳ መልኩ ለማስተንፈስ የሚያስችሉ እያንዳንዳቸው 70 ሜትር ከፍታ እና 40 ሜትር ስፋት ያላቸው ስድስት የውሃ ማስተንፈሻዎች /መውጫዎች/ እየተገነቡ ናቸው። ሌሎች ከግድቡ ጋር ተያያዥ የሆኑ የመንገድ፣ ካምፖች፣ ወርክሾፖች ግንባታዎች ተከናውነዋል። በጠቅላላውም ፕሮጀክቱ 61 በመቶ ያህል የደረሰ ሲሆን ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅም ከሶስት እስከ አራት ዓመታት ያስፈልጋሉ።

የፕሮጀክቱ ግንባታ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጭ ግድብ መገንባት ብቻ ሳይሆን ለዘርፉ ልማት ወሳኝ የሆነው የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚደረግበትም ነው። ምክትል ሥራ አስኪያጁ ፕሮጀክቱ ለአምስት ሺህ የአገር ውስጥ ሰራተኞች እንዲሁም 140 ኤክስፐርቶች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉንም ገልፀዋል። ከሀገር ወስጥ የሥራ ዕድሉ ተጠቃሚዎቹ 30 በመቶ ያህል የሚሆኑት የግድቡ አቅራቢያ በሆኑ አካባቢዎች ነዋሪ የሆኑ ነዋሪዎች መሆናቸውንም ጠቅሰዋል። በሜጋ ፕሮጀክቱ ክፍ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸውንም ተናግረው፣ በዚህም የሀገር ውስጥ ሰራተኞች በርካታ ልምዶችን እያገኙ እና እየቀሰሙበት መሆኑንም አመላክተዋል።

የኮይሻ ሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ለኢትዮጵያውያን የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ የላቀ ድርሻ እንዳለው በፕሮጀክቱ በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ ሰራተኞች አመላከተዋል። ሰራተኞቹ እንደገለጹት፤ ከሆነ በእንደነዚህ አይነት ትላልቅ ፕሮጀክቶች መሳተፋቸው አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ትልቅ ዕድል ፈጥሮላቸዋል።

የ33 ዓመቱ ሙሉቀን ተከስተብርሃን፣ በፕሮጀክቱ የሴፍቲ ሱፐርቫይዘር ነው። ወጣቱ ላለፉት 15 ዓመታት በበለስ፤ በአባይና ግድብ ግንባታዎች ሰርቷል። አሁን ደግሞ በኮይሻ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ እየተሳተፈ ይገኛል። በመሰል ፕሮጀክቶች መሳተፉ የተለያየ እውቀት እንዲቀስም እንዳስቻለው ጠቅሶ፣ በዚህ ስራ ላይ መሰማራቱ በሙያም ራሱን ለማሳደግም ሃገሩን ቤተሰቡን ለመለወጥ እንዳስቻለው ይናገራል።

"አሁን እኔ የሴፍቲ ባለሙያ ነኝ። በሃገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ አገር ሄጄ መስራት የሚያስችል እውቀት አግኝቻለሁ። የሚያሰራኝ ድርጅት ለረጅም ጊዜ አብረውት የሰሩትን ውጪ አገር ድረስ ልኮ ያሰራል። እኔም ወደፊት ባካበትኩት እውቀትና ልምድ የዚህ እድል ተጠቃሚ መሆኔ አይቀርም።" ብሏል።

መሀመድ ደልዋናም እንዲሁ ላለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት በፕሮጀክቱ አናጺና የክሬን ረዳት ሁኖ ሰርቷል። ፕሮጀክቱ ላይ በመሳተፉ እድለኛ መሆኑን ይገልጻል። መሃመድ በእስከ አሁኖቹ ፕሮጀክቶች ባለመሳተፉም እየተቆጨ ነው። ቀደም ሲል ስራ አጥና ጊዜዬን ባልባሌ ቦታዎች የማሳልፍ ነበርኩ የሚለው መሀመድ፣ አሁን ግን የሙያ ባለቤት ሁኜ፤ በራሴ ሰርቼ፤ የወር ደመወዝ ቆጥሬ መቀበል መቻሌ በራሱ ትልቅ ለውጥ ነው ሲል ይገልጻል።

የ28 ዓመቱ ወጣት ነዚፍ አባመጫ የግልገል ግቤ ሦስት የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግንባታ በሚከናወንበት ወቅት ነው በኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ግንባታ መስራት የጀመረው። ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በኃይል ማመንጫ ግንባታ ስራ ላይ መሰማራቱ የራሱንም ሆነ የቤተሰቡን ኑሮ ማሻሻል እንዳስቻለው ይናገራል። "በፕሮጀክቱ ያገኘሁትን ልምድና ተሞክሮ በመጠቀም ወደፊት የራሴን ስራ ፈጥሬ ከጓደኞቼ ጋር አብሬ በመስራት ለመለወጥ ሃሳብ አለኝ ሲልም ነው የተናገረው።

ቤዛዊት ኃይሉ በፕሮጀክቱ የጂኦሎጂ ኢንስፔክተር ነች። በፕሮጀክቱ መስራት መቻሏ በሙያው የካበተ ልምድ ካላቸው የሃገር ውስጥና የውጪ ባለሙያዎች በርካታ እውቀትና ልምዶችን እንድትቀስም እድል እንደፈጠረላት ተናግራለች። "ይህን መሰል እውቀትና ክህሎት ማግኘት መቻላችን በንድፈ ሃሳብ ያገኘነውን እውቀት በተግባር አንድንፈትሸው ያግዛል›› ስትል ገልጸ፤ በሃገሪቱ የሚታቀዱ ተመሳሳይ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችን በውስጥ አቅም ለመስራት እንደሚያስችልም ነው ያመለከተችው።

የፕሮጀክት ኮንትራክተሩ ድርጅት ኃላፊ ኢንጂነር ዞፒስ ኢውጊኒዮ እንደሚሉት፤ በአሁኑ ወቅት ፕሮጀክቱ 5000 ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድል ፈጥሯል። እነዚህ ሰራተኞች እውቀትና ልምዳቸውን እንዲያሳድጉ ብቻ ሳይሆን የስራና የደመወዝ እድገት እንዲያገኙም እየተደረገ ነው። "ይህ አይነቱ የአቅም ግንባታ ስራ ሀገሪቱ ወደፊት በራስዋ አቅም ለምትገነባቸው መሰል ፕሮጀክቶች ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ‹‹እኛም በዚህ እንኮራለን›› ሲሉ ነው ኃላፊው የተናገሩት። ብዙዎች ከዝቅተኛ የስራ ደረጃ ተነስተው የትልቅ ሙያ ባለቤቶች መሆናቸውንም ጠቅሰዋል።

የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሰላማዊት ካሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮጀክት ከአረንጓዴ ልማት ጋር የተጣመረ ነው። በፕሮጀክቱ ዙሪያ የሚገኘው የአረንጓዴ ልማት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት እየተካሄደ ያለው የጨበራ ጩርጩራ ፓርክ አካልና በመላ አገሪቱ ከሚገነቡት ሦስቱ ዋና ዋና የቱሪዝም መስህብ ፕሮጀክቶች አንዱ ነው። ይህ ፕሮጀክት ለአገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ ሌላ መስህብ ስፍራ ይጨምራል።

በዚህ ግድብ የሚፈጠረው ሰው ሰራሽ ሀይቅ አስደናቂ እይታ ይፈጥራል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ ይህ ፕሮጀክት በቱሪዝም ልማትና እንቅስቃሴ በተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ረገድ የሚኖረው አበርክቶው ሰፊ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ የመጣው መንግስት ካደረገው ማሻሻያ በፊት ሜጋ ፕሮጀክቶች ትልቅ ችግር ውስጥ ነበሩ ሲሉ አስታውሰው፣ ያን ሁኔታ ለመቀየር መሰራቱን ገልጸዋል። የመንግስት አንዱ ትኩረት የዚህን ግዙፍ ፕሮጀክቶች አስተዳደር ማሻሻል እንደነበርም ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በተለይ በኢኮኖሚው ዘርፍ ብዙ ማሻሻያዎችን ሲደረጉ ቆይተዋል። ለዚህ በአባይ ግድብና ሌሎች ፕሮጀክቶች የተሰሩት ስራዎች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ። ሀገራዊ ሪፎርሙ የእነዚህን ፕሮጀክቶች አስተዳደር አቅም በማሳደግ ላይ ያተኮረ መሆኑን አመልክተው፣ በዚህም በጥቂት ዓመታት ውስጥ ጥሩ አፈፃፀም እያሳየ መምጣቱን ተናግረዋል።

ግድቡ አንድ ሺህ 800 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ ብሔራዊ የኃይል ቋት ይጨምራል ያሉት ሚኒስቴር ዴኤታዋ፣ የሕብረተሰቡን የኃይል ፍላጎት ከማሟላት በዘለለ የሀገሪቱን ኢኮኖሚና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ያሳድጋል ብለዋል።

መንግስት በአገራችን ብቻ ሳይሆን በጎረቤቶቻችን እና በዓለም አቀፍ ደረጃ አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብርን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ ፕሮጀክትም ከተፈጥሮ ሃብት ልማትና ክብካቤ ጋር ያለውን ተዛምዶ በግልፅ ያሳያል ብለዋል። ይህ አካባቢ ግድቡ ከጀርባው በሚፈጥረው ኃይቅ ምክንያት ወደ ተፈጥሯዊ መስህብነት ሲሸጋገር ለቱሪዝም ልማት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑንም ጠቁመዋል። አካባቢው ብዙ የዱር እንስሳት ማለትም ዝሆኖች፣ አንበሶች፣ ብርቅዬ ወፎች እንዲሁም ዕፅዋት እና ሌሎች የዱር አራዊት በብዛት ያሉበት መሆኑን የገለፁት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ ፕሮጀክቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የተፈጥሮ ጥበቃ ጽንሰ-ሀሳብን ይጨምራል ብለዋል።

በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎች በፕሮጀክቱ ውስጥ በመቀጠር የዚህ ፕሮጀክት መገኘት ቀጥተኛ ተጠቃሚ መሆናቸውንም ተናግረዋል። በዚህ ፕሮጀክት ምክንያት ከ50 ኪሎ ሜትር በላይ መንገድ ተገንብቶ በኦሞ ወንዝ ምክንያት ተለያይቶ ለነበረው ሕብረተሰብ በኢኮኖሚና ማሕበራዊ ትስስሩ እንዲጠናከር ሆኗል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስለኢትዮጵያ በሚመለከት የሚወጡ መግለጫዎች መሬት ላይ ያለውን ሃቅ የሚያሳዩ ይሁኑ!

መንግሥት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሰላም ጋር በተያያዘ ያጋጠሙንን ችግሮች በውይይት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሰፊ ጥረቶችን አድርገናል። በተለይም በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ተፈጥሮ የነበረውን ደም አፋሳሽ ግጭት በሰላማዊ መንገድ በድርድር ለመፍታት ረጅም ርቀቶችን ተጉዟል።

ሀገራዊ የሰላም እሴቶቻችንን በመጠቀም ችግሩን በሰላማዊ መንገድ በሀገር ሽማግሌዎች በውይይት ለመፍታት ጥረት አድርጓል። የግጭት ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ የሆኑ እናቶችን የሰላም ሐዋሪያት በማድረግ የሄደበት ርቀትም ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የነበረውን ጠንካራ አቋም በአደባባይ በተጨባጭ ያሳየ ነበር።

ወደ ጦርነት ከተገባም በኋላ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የተደጋገሙ ጥሪዎችን በማድረግ እንደ ሀገር የትኛውም በግጭቱ ተሳታፊ የሆነ አካል ከግጭት ተጠቃሚ ሊሆን እንደማይችል በማሳሰብ፤ ሀገር እና ሕዝብን ከግጭት እና ግጭት ሊያስከትል ከሚችለው የከፋ ጥፋት ለመታደግ በቁርጠኝነት ተንቀሳቅሷል።

በርግጥ የመንግሥት ጥረቶች ሰሚ አጥተው፤ እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ የከፈልንበት ጦርነት ውስጥ ገብተናል። በዚህም ከፍ ያለ ሰብአዊ፣ ሥነልቦናዊ እና ቁሳዊ ውድመት ለማስተናገድ ተገድደናል። ከችግሩም እስካሁን ማገገም የምንችልበትን አቅም መፍጠር አልቻልንም።

ገና ከጅምሩ ለሰላም ከፍ ያለ ፍላጎት ያሳየው መንግሥት፤ በተደጋጋሚ ስለሰላም ያቀረባቸው ጥሪዎች በሕወሓት በኩል ተቀባይነት አግኝተው በአፍሪካውያን ወንድሞቻችን አሸማጋይነት በደቡብ አፍሪካ ፣ ፕሪቶሪያ የሰላም ድርድር መጀመሩ ይታወሳል።

"ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ" በሚል መርህ በተካሄደው የሰላም ድርድር በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የነበረው ደም አፋሳሽ ጦርነት በሰላም ስምምነት ማብቂያ ማግኘቱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በዚህም አካባቢው ከጥይት ድምጽ ነጻ ሆኗል። ሕይወትም በአዲስ ተስፋ ቀጥሏል።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎም ሰላሙን ዘላቂ ማድረግ የሚያስችሉ፤ በስምምነቱ ላይ የሰፈሩ ነጥቦች ተግባራዊ ተደርገዋል። በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ከመመስረት ጀምሮ በክልሉ ሰላማዊ ሕይወት የሚቀጥልበት የተለያዩ ተጨባጭ ተግባራት ተከናውነዋል፤ እየተከናወኑም ነው።

እንደ ሀገር የተሀድሶ ኮሚሽን በማቋቋም በግጭት ውስጥ የነበሩ ታጣቂዎችን ትጥቅ የማስፈታትና ወደ ማኅበረሰቡ የመቀላቀል ሥራ በአግባቡ እየተከታተለ ነው። ፍትህና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ይገኛል። በሀገር አቀፍ ደረጃ ውይይቶችን በማድረግ ቁርሾዎችን በመሻር የተሻለች ኢትዮጵያ ለመፍጠር እየተሠራ ነው።

በክልሉ በሁለንተናዊ መልኩ ሕይወትን ወደ ቀድሞ ስፍራው ለመመለስ የጊዜያዊ አስተዳደሩ ሰፊ የመልሶ ግንባታዎችን አቅዶ ወደ ተግባር ገብቷል፤ የክልሉ ሕዝብ ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ የደረሰበትን ሰብአዊ ፣ ሥነልቦናዊ እና ቁሳዊ ውድመት እንዲያገግም በሀገር አቀፍ ደረጃ እየሠራ ነው።

ለዚህም የፌዴራል መንግሥት ጨምሮ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በስፋት እየተንቀሳቀሱ ነው፤ እየተመዘገበ ያለውም ውጤት ተስፋ ሰጪ ነው።ይህ ውጤት ከሰላም ስምምነቱ ማግስት ጀምሮ እየተከናወኑ ባሉ ተጨባጭ ሥራዎች የተገኘ ስለመሆኑ በችግሩ ውስጥ ለነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአደባባይ ምስጢር ነው።

ይህንን በተጨባጭ የሚታይ፤ የሰላም ስምምነቱ ለትግራይ ሕዝብም ሆነ ለመላው ሕዝባችን ይዞት የመጣውን እፎይታ አቅልሎ ማየት ሆነ ባልተገባ መልኩ በአደባባይ መካድ የሚቻል አይደለም።

በተለይም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የዘር ማጥፋት ወንጀል መከላከል ልዩ አማካሪ ኢትዮጵያን በተመለከተ ሰሞኑን ያወጡት መግለጫ ይህንን ተጨባጭ እውነታ የዘነጋ ፣ በትክክለኛ መረጃ ላይ ያልተመሰረተ ኃላፊነት የጎደለውና መሬት ላይ ያለውን ሃቅ የካደ ነው።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሰላም የሚሻው የቱሪዝም ዘርፍ

ከትዝታ ማስታወሻ

በኢትዮጵያ በቱሪስት መስህብነት የሚታወቁ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ስፍራዎች በርካታ ናቸው።በመልክአ ምድር አቀማመጡና በተፈጥሯዊ ውበቱ፣ መንፈስን በሚያድሱ ምቹ አየርና አፍን በእጅ የሚያስይዝ ምትሃታዊ የውበት ጥግ የሚታወቁ በርካታ የመስህብ ቦታዎች አላት።

ሀገሪቱ በቱሪዝም ሀብቷ ከአፍሪካ ግንባር ቀደም ከሆኑ ሀገሮች መካከል አንዷ ብትሆንም ከዘርፉ የሚጠበቀውን ያህል ጥቅም ግን አላገኘችም። በጎብኚዎች መዳረሻነት ከሚታወቁት ሀገራት ተርታ በቀዳሚነት መሰለፍም አልሆነላትም።

በተለይ የዘርፉን የመዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ፣ ጎብኚዎችን በመሳብና አዳዲስ መዳረሻዎችን በመፍጠር ተጠቃሚነትን ማጎልበት ረገድ ግልፅ ድክመት እንዳለባትም በርካቶች ይስማሙበታል።

የቱሪስት ፍሰቱን ለመጨመር የመሰረተ ልማትና የማረፊያ ቦታዎች ምቹነት እጅጉን ወሳኝ ነው። ሌሎች ሀገራት ያልታደሉት ተፈጥሯዊም ሆነ መልክአ ምድራዊ ሀብት ብትታደልም ኢትዮጵያ የቱሪስት መዳረሻዎቻችንን ማልማት ሳትችል ቆይታለች።

> የቱሪስት ፍሰቱን ለመጨመር የመሰረተ ልማትና የማረፊያ ቦታዎች ምቹነት እጅጉን ወሳኝ ነው

በየቱሪስት መዳረሻዎች በቂ የሚባሉ የእንግዳ ማረፊያዎች ባይኖሩም ያሉትንም በሚፈለገው ደረጃ በማደራጀት ለጎብኚዎች ምቹ መስተንግዶና አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ውስንነትም ጎልቶ ይታያል።

የአይሁድ ዝርያና የደች ዜግነት ያለው ታዋቂው የፍልስፍና ጠቢብ ባሩች ስፒኖዛ Baruch Spinoza « If you want the present to be different from the past, study the past/ዛሬ ከትናንቱ የተሻለ እንዲሆን ከፈለግክ የትናንቱን በሚገባ አጢነው/»የሚል አባባል አለው። ይህን አባባል ዛሬን ከትናንት ለማብለጥ በተለይ ካለፈው ልምድና ተግባራችን ትምህርት መቅሰም እንደሚገባ ያስገነዝባል።

የቱሪዝም ዘርፉ ከትናንት ይልቅ ዛሬ ላይ የተሻለ ቁመና ላይ ቆሞ ለመመልከት ከተፈለገ ይህን አባባል ጠንቅቆ መረዳት የግድ ይላል።በቱሪዝም ዘርፉ ማግኘት የሚገባንን ማግኘት ያልቻልነው ለምን ይሆን ብለን መጠየቅም ተገቢ ነው።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት የቱሪዝም ዘርፉ እድገት ማነቆ የገባው ይመስላል።ዘርፉን የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ለማድረግ የመዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ፣ ጎብኚዎችን በመሳብና አዳዲስ መዳረሻዎችን በመፍጠር ተጠቃሚነትን ማጎልበት እንደሚቻል አምኗል።

የሀገሪቱን የቱሪስት መዳረሻነት ለማሳደግ እየተከናወኑ ከሚገኙ ተግባራት መካከል የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ይገኝበታል። ገበታ ለሀገር በሚል ፕሮጀክት ቀደም ሲል ትኩረት ያልተሰጣቸው ቦታዎችን በመምረጥ የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ ነው። በዚህም ትኩረት ተነፍጎት የቆየው የሀገሪቷን የተፈጥሮ ሀብት የማልማት ሥራ በጎርጎራ፣ በኮይሻና በወንጪ አካባቢዎች በመከናወን ላይ ይገኛል።

የእነዚህእና የሌሎች ፕሮጀክቶች መጠናቀቅ ታዲያ የሀገሪቱን የቱሪዝም ዘርፍ አቅም ይበልጥ በማጎልበት ከዘርፉ የሚገኘውንም ጥቅም ከፍ ለማድረግ ሁለንተናዊ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም።

ይሁንና የቱሪዝም ተስፋ እንዲሰምር የመዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ፣ ጎብኚዎችን በመሳብና አዳዲስ መዳረሻዎችን ከመፍጠር ባሻገር የዘርፉን እንቅስቃሴ ሰላማዊ መንገድ ላይ ማራመድ የግድ ይላል።ለቱሪዝም ዘርፍ ልማት፣ እድገትና ተጠቃሚነት ከሁሉ በላይ ሰላም የማይተካ ሚና አለው።

ሰላም ከጥንት ፈላስፎች እስከቅርብ ጊዜ ሊቃውንት የተጠበቡበት ለሰው ልጆች በጣም አስፈላጊ የሆነ እሴት ነው። ስለ ሰላም ዋጋ የጦርነት አውዳሚነት በመጥቀስ በርካቶች ሰብከዋል። ጽፈዋል። ከእነዚህ መካከል ዕውቁ ግሪካዊ ጸሐፊና የታሪክ ሰው ሔሮዶቱስ የጦርነትን አስከፊነት እና ሰላም የውሃና የአየር ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንዲህ ሲል ገልጾታል።

" In peace, sons bury their fathers. In war, fathers bury their sons!" (በሰላም ጊዜ ልጆች አባቶቻቸውን ይቀብራሉ፤ በጦርነት ጊዜ አባቶች ልጆቻቸውን ይቀብራሉ ) ሲል ይህ ግሪካዊ የታሪክ አዋቂ አባባል የጦርነት እጅግ አስከፊ ገጽን ብቻ ሳይሆን የሰላምን ጥቅም አድማሳዊነት ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል።

በሀገራችን ያለው ሰላም መደፍረስ ሕይወት ከመቅጠፍ ባለፈ የቱሪዝም ዘርፉ ላይ ጥቁር ጥላ ማጥላት ከጀመረ ዋል አደር ብሏል።ይህን ጠንቅቆ ለመረዳትም ደግሞ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ቀላል ነው።

ለአብነትም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የነበረውን ግጭት ተከትሎ እስካሁን ለጎብኚዎች ክፍት ያልሆነው የአክሱም ሐውልት በሰላም እጦት ከተጎዱት ውስጥ አንዱ መሆኑን መጥቀስ ይቻላል።

ከወጥ አለት የተሰራውና ዓለም ስለህንጻ ንድፍ ሳይገባው አያቶቻችን ቀድመው ከላይ ወደታች ያነጹት የላሊበላ ቤተክርስቲያን በሰላም እጦት ጎብኚዎች "ጉብኝት ሰላም ሲኖር ነው" ብለው ርቀውታል። በጎንደር የሚገኘው የፋሲል ቤተመንግሥትም ዕጣ ፋንታው ተመሳሳይ ነው።

ግጭትና ጦርነት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አካባቢዎች የሕገወጦች መበራከትም ለቱሪዝም ዘርፉ ከባድ አደጋ ነው። ይህ የጎበዝ አለቆች መበራከትና እኩይ ተግባርም በተለይም በብዙ ዓመታት መልካም የእንግዳ አያያዝና መስተንግዶ የተገነባው የኢትዮጵያውያን እንግዳ ተቀባይነት ሥም የሚያጎድፍ ነው።

ሰዎች በተፈጥሯችን ከተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ከምናገኘው መረጃ ይልቅ የቅርባችን ሰው ሲነግረን የበለጠ እናምናለን። ለቱሪስቶችም የሚሠራው ይሄ ነው። አንድ ቱሪስት ጎብኝቶ በወደደው ሀገር ቆይታውን ያራዝማል፤ ከቻለ ተመልሶ ይመጣል።ለወዳጅ ዘመድ እንዲጎበኙት ይነግራል።

በተቃራኒው በተለያዩ ምክንያቶች በሄደበት ሀገር ደስተኛ ካልሆነ የጉዞ እቅዱን ሳያጠናቅቅ አቋርጦ በፍጥነት ይመለሳል። እንኳን ለሰው ሂዱ ብሎ ሊመክር ሊሄዱ ያሰቡም ካገኘ ውሳኔያቸውን እንዲቀይሩ ጫና ያሳድራል።

ይህ እንደመሆኑም የቱሪዝም ዘርፉን የመዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ፣ ጎብኚዎችን በመሳብና አዳዲስ መዳረሻዎችን በመፍጠር ተጠቃሚነትን ለማጎልበት የተጀመሩ እንቅስቃሴዎችን ሰላምና መረጋጋት በማስፈንም ይበልጥ ሊታጀቡ ይገባል። የዜጎችንም ሆነ የጎብኚዎችንም በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢ በሰላም የመንቀሳቀስ መብት በተጨባጭ ማረጋገጥም የግድ ነው።

ዓለም እንደ ድሮው በእንግዳ ተቀባይነት ያውቀን ዘንድ ሁላችንም ለሰላማችን ዘብ ልንቆም የግድ ይላል። ችግሮችንም በሠለጠነ መንገድ በመቀራረብ፣ በመነጋገርና መደራደር መፍታት ቀዳሚ አማራጭ ማድረግ ተገቢ ነው። ሀገር ሰላም ስትሆን ኢኮኖሚው ይነቃቃል። ቱሪዝማችንም ይጎለብታል። ከዘርፉ በሚገባን መልኩ ተጠቃሚ መሆንም ቀላል ይሆናል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# መነሻውን ዘጠና ዘጠኝ ብር ከዘጠና ሳንቲም ያደረገው የባለራዕዩ ስኬት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ሰዎች ሥራን ሳይንቁ አቅማቸውን አሟጠው መጠቀም ከቻሉ ውጤታማ እንደሚሆኑ ይታመናል። ‹‹ሰውን ሰው ያደረገው ሥራ ነው›› እንደሚባለው ብዙዎች የሥራን ትርጉም ተረድተው፣ አውቀውና ተገንዝበው መሥራት በመቻላቸው ሙሉ ሰው መሆን ችለዋል። በተለይም ከዝቅታው ዝቅ ብለው ከትንሽ የተነሱቱ ሙሉ ጊዜያቸውንና አቅማቸውን አሟጠው በመጠቀም ትናንት የነበሩበትን ወደ ኋላ ትተው ሽቅብ ወጥተዋል። ከመጨረሻው የድህነት ወለል ተነስተው ከስኬት ማማ ላይ ከወጡ በርካቶች መካከል የዕለቱ እንግዳችን አንዱ ነው።

እንግዳችን ከእጅ ወደ አፍ የሆነው የወላጆቹ ኑሮ እየደቆሰው አድጓል። በአንድ ወቅት የስምንተኛ ክፍል ትምህርቱን አቋርጦ ወታደር እንዲሆንም ሕይወት አስገድዳዋለች። ይሁንና በውትድርና ሕይወት ብዙ አልገፋም፤ ገና በጥዋቱ የመቁሰል አደጋ ገጥሞት በቦርድ ጡረታ ወጥቷል። ከውትድርና የተረፈች ሕይወቱን ለማቆየት ያለችው የዘጠና ዘጠኝ ብር ከ90 ሳንቲም ጡረታ ብቻ ነበረች። በዚሁ ገንዘብ ሕይወቱን ለማቆየት ጥረት ቢያደርግም አንድ ቀን ሲሞላ ሌላ ቀን እየጎደለ በብዙ ተፈትኗል።

በሕይወት መንገድ ውስጥ ይልሰው ይቀምሰው አጥቶ ያውቃል። ማደሪያም ቅንጦት ሆኖ በረንዳ ላይ ተጠልሏል። ታዲያ በዚህ ጊዜ በቂ ገንዘብ ባይኖረውም ሕይወቱን ከማቆየት አልፎ "የተሻለ ኑሮ ይኖረኛል፤ ከራሴ አልፌ ለሌሎችም እተርፋለሁ" የሚል ተስፋን ሰንቆ ራዕዩን ለመኖር ታግሏል። ተስፋውን ዕውን ለማድረግም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሥራ ሳይንቅ አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ ይሠራ ነበር። ከጥበቃ ጀምሮ ቤት ለቤት እየተዘዋወረ በጋሪ ደረቅ ቆሻሻን ሲሰበስብ ኖሯል። ዛሬ ግን ራዕዩን ማሳካት ችሎ ከራሱ አልፎ ለሌሎችም ተርፏል።

በሕይወት ውጣ ውረድ ጠመዝማዛ መንገድ ዛሬ ከስኬት ማማ ላይ የደረሰው እንግዳችን አቶ ሄኖክ ዶንጋቶ በሲዳማ ክልል ሀዋሳ ከተማ ቱላ ክፍለ ከተማ ተወልዶ አድርጓል። የስምነተኛ ክፍል ትምህርቱን አቋርጦ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነትን ወቅት ወታደር ሆኗል። የሕይወት መስዋዕትነትን በሚጠይቀው የውትድርና ሥራ ላይ እያለም በጥይት ተመትቶ ቆስሏል። ባድሜ ሽራሮ ግንባር ላይ በመመታቱ ገና በጥዋቱ በቦርድ ጡረታ የወጣው አቶ ሄኖክ፤ እዛው ወታደር ቤት ቀለል ያለ ሥራ ተመድቦ ስንቅና ንብረት ክፍል ጥበቃ ሆኖ አገልግሏል።

በተጨማሪም ስልጠና ወስዶ የተለያዩ መሳሪያዎችን አቀናጅቶ ወደ ግንባር በመላክ ሂደት ውስጥ ሲያገለግል እንደነበርም ያስታውሳል። የተመቱ ወታደሮች በሙሉ ጡረታ ይውጡ በሚለው የመንግሥት አቅጣጫ መሰረት በ1997 ዓ.ም ዘጠና ዘጠኝ ብር ከ90 ሳንቲም የጡረታ ደምወዙን ይዞ ማህበረሰቡን ተቀላቅሏል። የሕይወት ውጣ ውረዱ ከዚህ ጊዜ እንደጀመረ ነው አቶ ሄኖክ ያጫወተን። ዘጠና ዘጠኝ ብር ከዘጠና ሳንቲም የጡረታ ደምወዙን 100 ብር አድርጎ ለመቀበል ወደ ጡረታ ሚኒስቴር አስር ሳንቲም ይዞ መሄድ ይጠበቅበት እንደነበር ያስታውሳል። በወቅቱ በ100 ብር የእግዜር ውሃ ጠጥቶ እንደነገሩ በልቶ ቢውልም ማረፊያ ጎጆ መከራየት ግን ፈተናው ነበርና በረንዳ ያድራል።

ተጨማሪ ሥራ መሥራት እንዳለበት አብዝቶ ያስብና ያሰላስል የነበረው አቶ ሄኖክ፤ የሸከም ሥራ ጀምሮ እንደነበር አጫውቶናል። ነገር ግን ቁስለኛ በመሆኑ እንደልቡ መሸከም አልቻለም። ያም ቢሆን ግን ሌሎች የሥራ አማራጮችን ለማግኘት ባደረገው ጥረት በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ የጥበቃ ሥራ የመሥራት ዕድል አግኝቷል። በዚህ ጊዜ ታዲያ በረንዳ ከማደር ወጥቶ ቤት መከራየት ቢችልም ኑሮ ያው ከእጅ ወደ አፍ ነውና አሁንም ተጓዳኝ ስራ ማግኘት እንዳለበት በማመን ትጋቱን ጨመረ። ይሄን ጊዜ ነው ውሃ፣ አፈርና ሌሎች ነገሮች የመጫን ሥራን ለመስራት በማሰብ ዕቁብ ሰብስቦ አንድ አህያና ጋሪ መግዛት የቻለው።

ከጥበቃ ከሚያገኘውን 2010 ብር ቆጥቦ አንድ አህያና ጋሪ መግዛት የቻለው አቶ ሄኖክ፣ በወቅቱ በአካባቢው



አቶ ሔኖክ ዶንጋቶ፤

ፎቶ -አሸናፊ ጉደታ

የተለያዩ ግንባታዎች እንደነበሩ ያስታውሳል። በመሆኑም ጭድ፣ ድንጋይ፣ አፈርና ሌሎች ሌሎችንም የማመላለስ ሥራ መሥራት ቀጠለ። ሥራው አዋጭ ሆኖለታል። ከእጅ ወደ አፍ የሆነውን ኑሮም እያሻሻለለት ነው። ያም ቢሆን ግን አቶ ሄኖክ ሥራውን ለማስፋት ሩቅ ሲያስብ አንድ ደንበኛው ከሀሳቡ አነቁት። ተጨማሪ ሥራ እንዲሰራ በር ከፈቱለት። ደረቅ ቆሻሻ ከግቢያቸው ሰብስቦ እንዲያስወግድላቸው ጠየቁት፤ አቶ ሄኖክ አላመነታም ምክንያቱም እሱ ሥራ አይንቅምና ለመሥራት ጓጓ።

አህያና ጋሪውን አቀናጅቶ ከግቢያቸው ያለውን ቆሻሻ ጠራርጎ አስወገደላቸው። በሌላኛውም ቀን እንዲሁ አደረገ። በቋሚነት የግቢያቸውን ቆሻሻ ማስወገድ የዕለት ተዕለት ሥራው ሆነ። በዚህ ጊዜ ታድያ በወር ከጥበቃ ከሚያገኘው ገንዘብ የበለጠ ደንበኛው ይከፍሉት እንደነበር አቶ ሄኖክ ያስታውሳል። ደረቅ ቆሻሻ የማስወገድ ሥራው ወደ ሌሎችም ተጋባና ደንበኞቹ ተበራከቱ። ከተለያዩ ሰዎች ጋር ደንበኝነቱን በማጠናከር የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ ሥራውን አስፋፋ። እየሰፋ የመጣው ሥራ ከአቅሙ በላይ ሆነና አንድ ሁለት እያለ አብረውት ሊሰሩ የሚችሉ ሰዎችን መቅጠር ቻለ።

ገቢው እየጨመረና ደንበኞቹ እየተበራከቱ ሲመጡ ታድያ ተጨማሪ ዕቁብ በመግባት የአህዮቹን ቁጥር አንድ ሁለት እያለ ሶስት ማድረስ ቻለ። በዚህ ጊዜም ለሶስት ሰዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ማታ ማታ ከሚሰራው የጥበቃ ሥራ ጎን ለጎን የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ ሥራውን ሳያቋርጥ ቀጥሏል። ይሁንና ሰዎቹን ወደ ሥራ ከማሰማራት ጀምሮ አህዮቹን የመቀለብ ሥራ የእሱ ነበርና ከጥበቃ ሥራው ጋር ጫና የፈጠረበት በመሆኑ የጥበቃ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ በማቆም ሙሉ ጊዜውን በደረቅ ቆሻሻ የማስወገድ ሥራ ላይ አደረገ።

ሕይወት ፈተናዋ ብዙ ነውና የአህዮቹ ቁጥር ጨምሮ ለሶስት ሰዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ጥሩ እየሠራ ባለበት ወቅት ያላሰበው ችግር እንደገጠመው አቶ ሄኖክ አጫውቶናል። አጋጣሚው እንዲህ ነው። በሀዋሳ ከተማ ውስጥ ያለ አንድ ሰው ቤት ሰርቶ ለማስመረቅ እንዲሁም ልጁን ሊድር ትልቅ ድግስ ደግሷል። በዛ ድግስ ላይ የሚታደሙ በርካታ ሰዎችንም ጠርቷል። ድግሱ እነዚህን በርካታ ሰዎች ታሳቢ ያደረገ ሰፊ ድግስ ነው። ይሁንና ባለታሪካችን በማያውቀው ምክንያት በድግሱ የተገኘ ሰው ባለመኖሩ የበሰለው ምግብ ለአፍ ሳይደርስ ቀረ። በዚህ ጊዜ ታድያ ምግብና መጠጡ ሁሉ ይበላሻል። እናም የተበላሸውን ምግብ ለማስወገድ ሲባል አቶ ሄኖክ ይፈለጋል። ተፈልጎ የተገኘው አቶ ሄኖክ፤ የተበላሸውን ምግብ እንዲያስወግድ በታዘዘው መሰረት ምግቡን ከግቢው ማስወገድ ጀመረ።

ለአፍ ያላለውን ምግብ አንድ ሁለት ጊዜ እንደጣለ ‹‹ለምን እጥላለሁ አህዮቼን ለምን አላበላም›› የሚል ሀሳብ ብልጭ ይልለታል። ድፎ ዳቦን ጨምሮ የተለያዩ የበሰሉና የተበላሹ ምግቦችን አቶ ሄኖክ ለአህዮቹ አስቀርቶ ማታ ላይ ከተለመደው ጊዜ የተለየውን ምግብ ለአህዮቹ ይመግባል። አህዮቹም ተለየብን ሳይሉ እምሽክ አድርገው ይመገባሉ ግና ነገሩ ሌላ ሆነ። ምግቡ አልተስማማቸውምና ሶስቱም አህዮች በዛው ለሊት ሞተው አደሩ። ይሄን ጊዜ ሁሉም ነገር እንዳሰበው ሳይሆን ቀረና ለብዙ ችግር ዳረገው። በወቅቱ የበላው ዕቁብ በመኖሩ ችግሩን ይበልጥ አጠናበት። ገንዘቤን አምጣ የሚሉ ሰዎችም ተበራከቱ ያም ቢሆን ግን አቶ ሄኖክ ተስፋ አልቆረጠም።

ከአህዮቹ ሞት በኋላ ሕይወትን ከዜሮ ለመጀመር ሲነሳ የሚያውቁት ሰዎች እንደተባበሩት አቶ ሄኖክ አጫውቶናል። እሱ እንዳለው ጓደኞቹ አንድና ሁለት ብር ከፍ ሲልም አስር ብር አሰባስበው አንድ አህያ ገዝተው ሰጥተውታል። እንደ ዕድል ሆነና አህያው ታማሚ በመሆኑ በእርዳታ የተገዛው አህያ በ15ኛው ቀን ሞተ። በዚህ ጊዜ ችግሩ ጸንቶ ለአንድ ዓመት ጎዳና ላይ ወጥቷል። ያም ቢሆን ታድያ የሕይወት መንገዱ ብዙ ነውና ሳይታክት ሌላኛውን መውጫ ቀዳዳ ያፈላልግ ጀመረ።

በዚህ ጊዜ ታድያ ችግሩን የተረዱ አንድ ደንበኛው ጋሪ ገዝተው የሰጡት መሆኑን ያስታወሰው አቶ ሄኖክ፤ ተመልሶ በአንድ አህያና ጋሪ የቀድሞ ሥራውን ደረቅ ቆሻሻን ማስወገድ ቀጠለ። ጠንክሮ መሥራት በመቻሉም አሁንም ከቀደመው ጊዜ በበለጠ የአህዮቹን ቁጥር ወደ አስር በማድረስ ለአስር ሰዎች የሥራ ዕድል ፈጥሮ ሲሰራ ሌላ ችግር ይገጥመዋል። ችግሩም አህዮቹ ማታ ማታ ስለሚጮሁ ጅብ ይጠራሉ በሚል ቤት የሚያከራየው አጥቶ ተቸግሯል። ይሄን ጊዜ አህዮቹን በመኪና መተካት እንዳለበት በማሰብ ከጅብ ጋር እየታገለ ሥራውን ቀጥሏል።

በከተማው የሚሰራውን ሥራ ከግምት ውስጥ በማስገባትም የከተማ አስተዳደሩ ማዘጋጃ ቤት አህዮቹን ማሳደር የሚችልበት ቦታ እንደተሰጠው ያነሳው አቶ ሄኖክ፤ እግዚአብሔርም ረድቶት መኪና መግዛት እንደቻለም ነው ያጫወተን። በዚህ ጊዜ ከደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ፕላስቲኮችን ለብቻ በመሰብሰብ መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል ሥራ ለተሰማራ አንድ ኩባንያ ማቅረብ ጀመረ። ከደረቅ ቆሻሻው ይበልጥ ፕላስቲኩ ከፍተኛ ገቢ ያስገባለት ጀመር። በዚሁ ጊዜም መኪኖችን መግዛት ችሏል።

አቶ ሄኖክ እንዳጫወተን ሥራ ሳይንቅ ጠንክሮ በመሥራቱ ውጤት ማምጣት ቢችልም ለስኬት ያበቃኝ ኮባ ኢንፓክት የተባለ የጣልያን ካምፓኒ ነው ይላል። ካምፓኒው የወዳደቁ ፕላስቲኮችን እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል ወደ ውጭ ኤክስፖርት ያደርጋል። በሥራ አጋጣሚ ያገኘው ይህ ካምፓኒ ሁለተኛውን መኪና መግዛት እንዲችል ትልቅ እገዛ ያደረገለት መሆኑን ያስረዳው አቶ ሄኖክ፤ ጥቅም ላይ የዋሉ ፕላስቲኮችን በከፍተኛ መጠን ማቅረብ ከቻለ መኪና እንደሚገዛለት ካምፓኒው ቃል ገብቶለት እንደነበር አስታውሶ፤ በገባው ቃል መሰረትም አዲስ አይሱዙ መኪና ገዝቶ ሰጥቶታል። የመኪናውን ዋጋ ከሚያቀርበው ፕላስቲክ በአንድ ኪሎ ግራም ሃምሳ ሳንቲም እየቆጠበ በሁለት ዓመት ውስጥ የመኪናውን ሙሉ ዋጋ ስምንት መቶ ሺ ብር መክፈል ችሏል። ይህ በሕይወቱ ትልቅ ስኬት ሆነለት።

በአሁን ወቅትም ከዚሁ ካምፓኒ ጋር ለሶስት ካምፓኒዎች ፕላስቲኮችን በጥሬው ሳይሆን በመጨፍለቂያ ማሽን ታግዞ እየጨፈለቀ ያቀርባል። ሁለቱ የቻይና ካምፓኒዎች ዱከም ላይ የሚገኙ ሲሆን ሶስተኛው የጣልያን ካምፓኒ አዲስ አበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ላይ የሚገኙ መሆኑን የጠቀሰው አቶ ሄኖክ፤ የቻይና ካምፓኒዎች ፕላስቲኮቹን በመጠቀም የውስጥ ሱሪ፣ ካልሲ፣ ታይት፣ አርተፊሻል ጸጉር፣ ሚጎ ገመድና ቦንድድ ፍራሽ ጭምር የሚያመርቱ እንደሆነም አጫውቶናል።

አምስት መጨፍለቂያ ማሽኖችን ተጠቅሞ ጨፍልቆ ያዘጋጃቸውን ፕላስቲኮች በአራት መኪኖቹ ወደ ደንበኞቹ የሚያደርሰው አቶ ሄኖክ፤ እነዚህን የወዳደቁ ፕላስቲኮች የሚሰበስበው ከሀዋሳ ከተማ ብቻ ሳይሆን በዙሪያዋ ከሚገኙ 11 ከተሞች እንደሆነም ነው ያስረዳን። በ11 ከተሞች የሚገኙ በርካታ ዜጎች ፕላስቲኮችን ሰብስበው ለአቶ ሄኖክ በማስረከባቸው ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። ከእነዚህ በተጨማሪ በቋሚነት የሥራ ዕድል የፈጠረላቸው 86 ሠራተኞችም አሉት።

ሠራተኞቹ ፕላስቲክ ጠርሙሶቹን ከመለየት ጀምሮ በማጠብ፣ ክዳኑን በመለየት፣ በመጨፍለቅ፣ በጫኝና አውራጅ እንዲሁም በጆንያ ጠቅጥቆ በማሸግና በሾፌርና ረዳትነት ሥራ የተሰማሩ ናቸው። መልሶ ጥቅም ላይ ከሚያውለው የፕላስቲክ ሥራ በተጨማሪ የከተማዋን ደረቅ ቆሻሻ የማስወገድ ሥራም ጎን ለጎን እያስኬደው እንደሆነ አቶ ሄኖክ ተናግሯል።


አቶ ሄኖክ ለ86 የአካባቢው ነዋሪዎች የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን ከእነዚህም መካከል በርካታ ቁጥር ያላቸው ሴቶች እንደሆኑ ነው የገለጸው። ከዚህ ቀደም ምንም አይነት የገቢ ምንጭ ያልነበራቸው እናቶችን ወደ ሥራ በማስጋባት ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል። ከተፈጠረው የሥራ ዕድል በተጨማሪ አቶ ሄኖክ ማህራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም በርካታ ተሳትፎዎችን የሚያደርግ ሲሆን፤ በርካታ ቁጥር ላላቸው ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ በማሟላት ድጋፍ እያደረገ ያስተምራቸዋል።

በመጨረሻም በዘጠና ዘጠኝ ብር ከ90 ሳንቲም ሕይወቱን ለማቆየት ሲጥር የነበረው አቶ ሄኖክ በአሁን ወቅት ያሉትን ንብረቶች ጨምሮ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር የሚደርስ ካፒታል ማፍራት የቻለ ሲሆን፤ በቀጣይም ሥራውን አጠናክሮ የመሥራት ዕቅድ ያለውና ከወዳደቁ ፕላስቲኮች መጥረጊያ ለማምረት ፋብሪካ የመገንባት ዝግጅቱን እያጠናቀቀ የሚገኝ መሆኑን አጫውቶናል።

# ማህደረ ጤና

# ቅድመ ምርመራ - ለጡት ጤና

**እየሩስ ተስፋዬ**



በጡታቸው እና በደረታቸው መካከል አበጥ ያለ ነገር በእጃቸው ሲዳብሱ ህመም ተሰማቸው። ሳያመነቱ በፍጥነት ወደ ህክምና ተቋም አምርተው ምርመራ አደረጉ። ከአንድም ሁለት የህክምና ባለሙያዎች ጋር ሄዱ። ነገር ግን ህመማቸው የጡት ካንሰር እንዳልሆነ ተነገራቸው። ግራ ቢገባቸው ምርመራ ከማድረግ ተቆጠቡ። ጥቂት ቆይተው ዳግም ሲመረመሩ ግን የጡት ካንሰር እንዳለባቸው በምርመራ ተረጋገጠ።

‹‹ያውም በፍጥነት የሚሠራጨው ካንሰር ነበር እኔን የያዘኝ›› ይላሉ ወይዘሮ ያይኔ አበባ ብርሃን በግዜው የነበረውን ነገር ሲያስታውሱ። ከምርመራው በኋላ ሃኪማቸው በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ህክምና እንዲጀምሩ በነገሯቸው መሠረት ለሰባት ወራት ሲከታተሉ መቆየታቸውን ይናገራሉ። ይህንኑ በማድረጋቸውም ከካንሰር ነጻ መሆናቸውን ያስረዳሉ። ይህ የሆነው ታዲያ ከዛሬ ሃያ ሁለት አመት በፊት እንደነበርና ነገር ግን አሁን በካንሰር መታመማቸውን እንኳን እንደረሱት ይገልፃሉ።

ወይዘሮ ያይኔ አበባ ከ1995 ጀምሮ የኢትዮጵያ ካንሰር አሶሴሽን በመሥራችነት እና የቦርድ አባል በመሆን ከጡት ካንሰር መዳን እንደሚቻል ለብዙዎች ደርሰው አስተማሪ ወጣቶችን ለማፍራት በቅተዋል። እርሳቸው እንደሚሉት፣ በእነርሱ ጊዜ ስለ ጡት ካንሰር በቂ ግንዛቤ አልነበረም፤ ደፍሮም አይነገርም። የህክምና ባለሙያዎችም ቁጥራቸው ጥቂት የሚባል ነበር። ዛሬ ላይ ግን የካንሰር ህክምና የሚሠጡ የህክመና ባለሙያዎች ቁጥር ጨምሯል። ጤና ሚኒስቴርም ቢሆን አሁን ላይ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ትኩረት እየሰጠ መምጣቱንና የጡት ካንሰርን በሚመለከት ግንዛቤ ለመስጠት አመቺ ጊዜ አሁን መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል።

በጤና ሚኒስቴር ደረጃ የጡት ካንሰርን በተመለከተ በአግባቡና ሁሉንም ባማከለ መልኩ ግንዛቤ መስጠት ይገባል። በሌላ በኩል በፊልምና በሌሎች የኪነ-ጥበብ ሥራዎች ውስጥ ‹‹ካንሰር ገዳይ ነው›› ወይም የመጥፎ ነገር ምሳሌ እንደሆነ የሚያመለክቱ ሥራዎች መቆም ይኖርባቸዋል። ከነዚህ በተጨማሪ ለህመሙ የሚሰጡ መድኃኒቶች ዋጋቸው በጣም ውድ መሆናቸው በዚህም ላይ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል። በእርግጥ መንግሥት 50 በመቶ ዋጋውን ያስተካከለ ቢሆንም፤ አሁም አቅማቸው የማይችል ታካሚዎች በርካታ በመሆናቸው ይህን ያገናዘበ የዋጋ ማሻሻያ ማድረግ የግድ ይላል።

ዶክተር ማቴዎስ አሰፋ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተባባሪ ፕሮፌሰር እና የካንሰር ህክምና ስፔሻሊስት ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ካንሰር ከየትኛውም የሰውነት ክፍል ሊነሳ ይችላል። ጤናማ የሆኑ ህዋሶች ጉዳት ሲደርስባቸው ሰውነት ወደ ጤናማ ህዋስነት እንዲመለስ ያደርጋል። ነገር ግን ጉዳት የደረሰበትን ወደ ጤነኛ ህዋስነት ለመመለስ ሲያቅተው ወደ ካንሰር ህዋስነት ይቀየራል። ይህም አንድ የነበረው የካንሰር ህዋስ ከተፈጠረ በኋላ ጨምሮ እና ተባዝቶ የተለያዩ ስሜቶች እንዲፈጠር ያደርጋል።

የጡት ካንሰር ደግሞ በዋናነት የሚከሰተው የወተት መተላለፊያ ቱቦ ላይ ከሚገኙ ህዋሳት (ሴሎች) እና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወተት ከሚያመነጩ ሴሎች ነው። ከአንድ ህዋስ ተነስቶ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣት በጣም ከፍተኛ ደረጃ ሲደርስ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚታወቀው በእብጠት መልክ ነው። በዚህም አንዳንድ ሰዎች የጡት ካንሰር የህመም ምልክት የሚያሳይ ይመስላቸዋል። ነገር ግን ይህም የተሳሳተ አመለካከት ነው።

በተለይም በወጣትነት ዕድሜ ጊዜ የሚከሰቱ እባጮች ይኖራሉ። ስለዚህም እባጮች ሁሉ የጡት ካንሰር ናቸው ማለት አይደለም። ዕድሜ እየጨመረ በመጣ ቁጥር የሚታዩ እባጮች ግን ካንሰር የመሆን እድላቸው ከፍተኛ ነው። ታዲያ እብጠቱ በየጊዜው መጠኑ እየጨመረ ከመጣ በፍጥነት ህክምና ካልተደረገ ወደ ብብት አካባቢ ወደሚገኙ ዕጢዎች፣ ሳምባ፣ ጉበት አጥንት፣ ጭንቅላት እና ወደ ተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ሊሰራጭ ይችላል። ይህም እንደ ካንሰሩ ባህሪ የሚወሰን ሲሆን፤ አንዳንድ ጊዜ በጣም ፈጥኖ ሊሰራጭ እና ሊዘገይም ይችላል።

እንደ ዶክተር ማቴዎስ ገለጻ፤ የጡት ካንሰር አጋላጭ ከሚያደርጉት መካከል አንዱ ጾታ ነው። በተለይም ከ97 በመቶ በላይ የሚከሰተው ሴቶች ላይ ሲሆን፤ የወንዶች ታጋላጭነት በሁለት ወይም በሦስት በመቶ ብቻ ነው።ሌላው አጋላጭ ምክንያት ዕድሜ ነው። እድሜ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የጡት ካንሰር ተጋላጭነት እየጨመረ ይሄዳል። ይሄንንም በቁጥር ለማሳየት ያህል አንዲት ሴት በአማካይ ዕድሜዋ 80 ቢሆን ፤ 80 ዓመት ከሞላቸው ስምንት ሴቶች አንዷ ሴት በጡት ካንሰር ትያዛለች እንደማለት ነው። ይህም ለምን ሆነ? ከተባለ የጡት ካንሰር ዋነኛ ምክንያት ሴት ልጅ ከወር አበባ ጋር ተያይዞ የሚመረት ‹‹የኤስትሪጂንን›› የሚባል ሆርሞን በሴቶች ላይ በብዛት ያለ በመሆኑ ነው። በወንዶች ላይ ደግሞ በዝቅተኛ መጠን ያለ በመሆኑ በሴቶች ላይ የመከሰቱን ዕድል ያሰፋዋል።

በመሆኑም አንዲት ሴት ልጅ የወር አበባዋ ቀደም ብሎ ከመጣ እና ለመቆም ከ50 ዓመት በላይ ሲሆን፤ ለዚህ ሆርሞን ተጋላጭነቱ የረዥም ጊዜ ስለሚሆን የጡት ካንሰር ተጋላጭነቱ ትንሽ ይጨምራል። በሌላ በኩል ደግሞ አንዲት ሴት የወር አበባዋ በ15 እና በ16 ቀናት ውስጥ መጥቶ እና በ45 ቀኑ ሲቆም ለዚህ ሆርሞን ተጋላጭ የመሆን እድል ዝቅተኛ ነው። በተጨማሪም ሴቶች የመጀመሪያ ልጅ የሚወልዱበት ዕድሜ በጣም ዘግይቶ ከሆነ ለዚህ ሆርሞን ተጋላጭነታቸው የሚጨምር በመሆኑ ለጡት ካንሰር እንዲጋለጡ ያደርጋቸዋል።

የማያጠቡና አልኮል የሚጠጡ ሴቶችም የጡት ካንሰር ተጋላጭነታቸው ይጨመራል። ስለዚህ እነዚህ በአብዛኛው የጡት ካንሰር በሰውነት ውስጥ ካለ ቅመም ወይም ‹‹ኤስትሮጂን›› የሚባለው ቅመም በሰውነታቸው ውስጥ ለረዥም ጊዜ በመቆየቱ የሚፈጥር በመሆኑ ተጋላጭነታቸውን ይጨምረዋል። ሌላው ደግሞ በዘር የሚሄድ ተጋላጭነት ሲሆን፤ ይህም ሁለት ዓይነት መልክ አለው። አንደኛው የጡት ካንሰር ተጋላጭ የሚደርጉ የተወሰኑ ጂኖች ወይም ዘረመል ጋር የተያያዘ ሲሆን በእንግሊዝኛ መጠሪያ ስሙ /brca 1 እና brca 2/ ተብሎ ይጠራል።

የነዚህ ጂኖች መዳከም ሲኖር አንዲት ሴት የጡት ካንሰር ተጋላጭነቷ ከፍተኛ ይሆናል። ወይም ተጋላጭነቷ እስከ 70 በመቶ ሊደርስ ይችላል። ከዚህ ውጪ ከሆነ ደግሞ ቤተሰብ ውስጥ የካንሰር ታማሚ ካለ ተጋላጭነቱ ይጨምራል። ይህም ማለት የመጀመሪያ ደረጃ ቤተሰብ እንደ እናት፣ እህት አክስት ያለ የቅርብ ዘመድ ሲኖር በዘር የመሄድ አዝማሚያ እንዳለው ያመላክታል።

ዶክተር ማቴዎስ እንደሚገልጹት፤ በወር አበባ ወቅት እንዲሁም የሆርሞን መጨመርና መቀንስን ተከትሎ ሴቶች ጡታቸውን ሲያማቸው የጡት ካንሰር ይመስላቸዋል። ነገር ግን ይህ ስህተት መሆኑን እና ከፍተኛ የግንዛቤ እጥረት እንዳለ ለማወቅ ያስችላል። ሌላው የተዛባ አመለካከት ደግሞ ሴቶች በጡት ካንሰር ከተያዙ በኋላ ‹‹ቀዶ ህክምና ልደረግ ነው፤ ጡቴ ሊቆረጥ ነው›› ብለው ማሰባቸው ነው። በዚሁ ፍራቻ የባህል ህክምና፣ የሃይማኖት እና ሌሎች የህክምና አማራጮች ሲወስዱ ይታያል። በዚህም ከዘመናዊው ህክምና የመዘግየት ሁኔታ ይፈጠራል።

አብዛኛዎቹ ሴቶች ካንሰር ታክሞ የሚድን ህመም እንደሆነም አይረዱም። ባደጉት ሀገራት ህክምናቸውን ተከታትለው የዳኑ ሰዎች ከጡት ካንሰር መዳን እንደሚቻል ወጥተው ያስተምራሉ። በእኛ ሀገር ደረጃ ግን የጡት ካንሰር ታማሚ የሆኑ ሴቶች ህመማቸውን አይናገሩም። እነዚህ ተደማምረው ወደ ህክምና በፍጥነት ያለመምጣቱ ነገር በስፋት ይታያል።

በኢትዮጵያም በተለያዩ ጊዜ በሚደረጉ ጥናቶች መሠረት ከሌሎች የካንሰር ህመሞች የጡት ካንሰር የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል። በቁጥር ደረጃም አንድ ሦስተኛውን ይሸፍናል። በየዓመቱ ወደ 19ሺ የሚሆኑ ሴቶች በጡት ካንሰር ይያዛሉ። በአዲስ አበባ ውስጥ ወደ ስምንት ሺ ስድስት መቶ ሴቶች በዚሁ ጡት ካንሰር ይያዛሉ። ይህም ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም። በዚህ ከቀጠለም ቁጥሩ ሊጨምር እንደሚችል ነው ዶክተር ማቴዎስ የሚገልፁት ።

እርሳቸው እንደሚያብራሩት ለጡት ካንሰር በዋናነት አጋላጭ ከተባሉት ምክንያቶች መካከል ዕድሜና ጾታ በመሆናቸው በመከላከል ብቻ ሊቀየር የሚችል ነገር አይኖርም። ስለዚህ ሴቶች ለጡት ካንሰር ሁሌም ተጋላጮች ናቸው። መፍትሄውም ቅድመ ምርመራ በማድረግ ካንሰሩ ደረጃው ከፍ ከማለቱ በፊት ቶሎ ህክምና አድርጎ ማዳን ይቻላል። ሴቶች 40 ዓመት ከሞላቸው የጡት ራጅ( ማሞግራፊ) ይህም በራጅ አይቶ አመላካች ነገር ካለ ወደ ህክምና ለማምራት የሚረዳ የምርመራ አይነት ነው።

ዕድሜያቸው ከ40 ዓመት በፊት ከሆነ ደግሞ የጡት ካንሰር መጠኑ ብዙ አይደለም።በተጨማሪም ማሞግራፊ እንደ ማህጸን በር ጫፍ ካንሰር ምርመራ፤ ካንሰርን የማሳየት አቅሙ ዝቅተኛ ስለሚሆን ዕድሜያቸው ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ ሴቶች በወር አንድ ጊዜ የወር አበባ መጥቶ ከሄደ በኋላ ሁለቱንም ጡቶቻቸውን በደንብ በመመልከት፣ በመዳበስ እና በሚዳብሱበት ጊዜ አጠራጣሪ ነገር ወይም እንደ ባቄላ እና መሰል ጠጣር ነገር ከታያቸው በአፋጣኝ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከህክምና በፊት የጡት ካንሰር ያለበትን ደረጃ ማወቅ ያስፈልጋል። ደረጃውን ለማወቅም የሚደረጉ የተለያዩ ምርመራዎች አሉ። እነርሱም የራጅ፣የአልትራሳውንድ፣የሲቲስካን እና ሌሎች ምርመራዎች ናቸው።ከዚህ በተጨማሪም የጡቱን ካንሰር አይነቱን ከጡቱ ናሙና በመውሰድ እና ሊያስፈልጉ የሚችሉ የመድኃኒቶች አይነቶችን እንዲወስዱ ይደረጋል።

ዶክተር ማቴዎስ እንደሚያብራሩት፤ ካንሰሩ ከጡቱ ያላለፈ በሚሆንበት ጊዜ በአብዛኛው በቀዶ ህክምና ጡቱን ወይም እብጠቱን እንዲወገድ በማድረግ ቀጥሎም እንደ ደረጃው የኬሞ ቴራፒ፣ የጨረር፣በእንክብል መልክ የሚወሰዱ ተጨማሪ መድኃኒቶችን እንዲወስዱ ይደረጋል። ሌላው ህክምና ከጡት አልፎ ወደ ብብት ውስጥ የገባ ከሆነ ሁለት አማራጮች አሉት። አንደኛው ሁለቱንም ጡቶች ማስወገድ እና በመቀጠል የኬሞቴራፒ እንዲወስዱ እና ሌሎችን ህክምናዎች ይሰጣቸዋል።

ምንም እንኳን ጡቱ ላይ የተገኘው ካንሰር በቀዶ ህክምና ቢወገድም ሳይታዩ የሚቀሩ ሴሎች ሊኖሩ ስለሚችል በተቻለ መጠን በኬሞቴራፒ በማጥፋት እና በማዳከም ዳግም አገርሽቶ ወደ ተለያየ የሰውነት አካል ላይ እንዳይሠራጭ ማድረግ ያስፈልጋል። ሌላው ሰውነት ላይ የተሰራጨ ከሆነ የኬሞ ቴራፒ እና በእንክብል መልክ መድኃኒቶች እና እንደ ደረጃው አይነት የሆርሞን ህክምና እንዲወስዱ በማድረግ ይታከማሉ።

የጡት ካንሰርን መከላከል አይቻልም። ለዚህም ዋና አጋለጮች ጾታ እና ዕድሜ ናቸው። የጡት ካንሰር እንደ ማህጸን በር ጫፍ ካንሰር ክትባት የለውም። ስለዚህ በዋናነት አጽንኦት ሊሰጠው እና በደንብ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ቅድመ ምርመራ ማድረግ ነው።

# ተናጋሪው ዶሴ

## በታዳጊዎቹ ላይ ግብረሰዶም ወንጀል የፈፀመው ግለሰብ አስተማሪ ቅጣት

እፀገነት አክሊሉ

አሁናዊ ሁኔታው በጣም አሳዛኝ ደረጃ ላይ ደርሷል። አደገኛ በሆነ ሁኔታ ግብረሰዶማዊነት እየተስፋፋ ነው። ሆስፒታል ውስጥ ጾታ አንሞላም እስከማለት የተደረሰበት ሁኔታ እያጋጠመም ይገኛል፤ ልጁ ከትምህርት ቤት ወደቤቱ ተመልሶ እማዬ! " እኔ ወንድ ነኝ ሴት? ወደፊትስ ሴት መሆን አልችልም ?" ብሎ እስከመጠየቅ ተደርሷል። ወንዶች የሴቶች ቀሚስ ለብሰው ቦርሳ ይዘው ፋሽን እያሳዩ ነው። አንተ አንቺ አትበሉ ተብሎ በተለያዩ ቦታዎች ስልጠናዎች እየተሰጠ ነው። ይህ እንግዲህ ሲጠቃለል እንደ አገር አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሳችንን ያመላክታል።

ይህ ሁሉ ነገር ግን ሲጠቃለል የሚያሳየው ከባህልና ከሀይማኖታችን አፈንግጠን እየወጣን ስለመሆናችን ነው። ሁላችንም እንደምንገነዘበው አሁን በየቦታው ሺሻ፣ ጭፈራ ቤት ራቁት ጭፈራ፣ ስካር እንዲሁም ገንዘብ መውደድ በጣም በዝቶ ተንሰራፍቷል። ግብረሰዶም ደግሞ እነዚህ ሁኔታዎች በጣም ይመቹታል፤ በመሆኑም እግር በእግር እየተከተለ ትውልዱን ሊያጠፋ እየገሰገሰ ነው ።

ግብረ ሰዶም የፈጣሪ እግዚአብሔርን ሀሳብ በመጻረር ትውልድ እንዳይቀጥል የሚያደርግ ነው። እግዚአብሔር ለአዳም/አደም ቢያስፈልገው ኖሮ ያደርገው ነበር፤ ነገር ግን ሄዋን ስለሆነች የምታስፈልገው ያደረገውም እንደዛ ነው። ኖህም ወደመርከቡ ሲያስጋባ እንስሳትን ወንድና ሴት አድርጎ ነው። እጽዋትን ብናይ ሴቴና ወንዴ ናቸው። ኤሌክትሪክም ኔጋቲቭና ፖዘቲዝ ነው። ከተፈጥሮ ጋር የተቃረነ ስራ እየተሰራ እያየን ግን መሪዎቻችን፣ የሀይማኖት አባቶች እንዲሁም ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ተቃውሞን ካላሰሙ ትውልድ ማለቁ ነው።

በመሆኑም 98 በመቶ በላይ ሀይማኖተኛ የነ ሕዝብ የሚኖሩባት፣ ባህልና ወግ ያላት አገር እስልምናውም ክርስትናውም በእግዚአብሔር ተፈጥረናል፤ ከሞትን በኋላ ደግሞ ገነት ወይም ጀነት እንገባለን ብሎ በሚያምንበት አገር ላይ እንደዚህ አይነት ስራ ነግሶና ተንሰራፍቶ ማየት የማንም ችግር ሳይሆን የራሳችን ንዝላልነት ያመጣው በመሆኑ ሁላችንም ወደምንጫችን ወደቀደመው ማንነታችን መመለስ ይገባናል።

በእኛ ባህልና ወግ ባልና ሚስት እንኳን በሰው ፊት አይሳሳሙም፤ ነገር ግን ድህነታችንን ተጠቅመው የተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች እየመጡ ቆሻሻ ተግባራቸውን ሲፈጽሙብን ዝም ልንል አይገባም። (comprehensive sexual education) በትምህርት ደረጃ ሲሰጥ እንዴት ዝም እንላለን። እንዲህ አይነቱን ጸያፍ ሒደትና ተግባር "አይሆንም!" ብለን በጋራ ልንጋፈጠው ይገባል። መጥፎና ከፈጣሪም የሚያጣላ ተግባር ከመጥፋታችን በፊት ልብ ልንላቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው።

አሁን አሁን ደግሞ እየተሰሙ ያሉ ጸያፍ አባባሎችም ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። በአገራችን ወይዘሮም ወይዘሪትም መባል አንፈልግም የሚሉ ሴቶች እየተስተዋሉ ነው፤ ይህ ከምን የመነጨ ነው? ማዕረግ የለኝም የሚል ሰው ሌላ ችግር አለበት ማለት ነውና ትኩረት ያሻል።

በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎችና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በየመንደሩ፣ በየሥርቻው፣ በየጎድጓዳውና ጉድጓዱ ራሳቸውን ደብቀው ያደፈጡ ሁሉ ቢቆጠሩ ብዛታቸው የትየለሌ ሆኗል። መጠሪያ ስማቸውም ግብረ ሰዶማዊ (ጌይ) ብቻ ሳይሆን 'ዜጋ' የሚለውንም ይጠቀሙበታል። በዚህ ሕይወት ውስጥ ያልገቡ ሌሎች ወገኖች ደግሞ ‹‹ቀጥ›› በሚል ይጠራሉ።

ይህን ሁኔታ የአገራችን በተለይም የከተማችን እውነት ነው። አሁን አሁን በጣም በጥቂቱ ከሰባት እስከ 32 ዓመት ድረስ ሕይወታቸውን በግብረ ሰዶማዊነት ያሳለፉት ግብረ ሰዶማውያንና ግብረ ሰዶማውያት (ወንዶችና ሴቶች)፣ ‹‹ዝምታው ይሰበር ትውልድ ይዳን በእኛ ይብቃ›› በሚል ርዕስ (ዘጋቢ) ዶክሜንተሪ ፊልሞችን እንዲዘጋጁ ትብብር እያደረጉ ትውልድን ለማዳን አንዳንድ ወገኖች እየሰሩበት ነው።

‹‹ስለኢትዮጵያ ዝም አንልም ግብረ ሰዶማዊነት በኢትዮጵያ የ666 አሠራር›› የሚል ርእስ ባለውና ለምረቃ በበቃው በዚሁ ፊልም ውስጥ ይህንኑ ቃለ መጠይቅ ካካሄዱት ከእነዚህ ግብረ ሰዶማውያን ማብራሪያ ለመረዳት እንደተቻለው ሕጋዊና መደበኛ ሚስት አግብተው፣ ትዳር መስርተውና ልጆች ወልደው በሽምግልና ዕድሜያቸው ግብረ ሰዶም የሚፈጽሙ አዛውንቶች አሉ። አንዳንድ ጊዜ ‹‹አባባ መሸቷል እባክዎን ወደ ቤትዎ ሂዱ›› እያሉ ወጣቶች በሽማግሌዎቹ ይቀልዱባቸዋል። ይሳለቁባቸዋልም። እነዚህም አዛውንቶች ታዋቂነታቸው በ‹‹ዜጎች›› ዘንድ ብቻ ስለሆነና በአካባቢያቸው ማኅበረሰብ ዘንድ የሚታወቁት ባለትዳርና የልጆች አባት ስለሆኑ ከማኅበረሰቡ ዘንድ እንዳይገለሉና ተከብረው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል።

አሁን አሁን ችግሩ አይን እያወጣ ብዙዎችም ሰለባ እየሆኑበት ያለ ይመስላል። ለዚህ ደግሞ ማሳያው መንግሥት ወይም የሚመለከተው የክብር መዝገብ ሰጪ አካል የማያውቃቸው ከአንድ በላይ የሆኑና ከተመሳሳይ ጾታ ጋር የሚደረጉ ጋብቻዎች እየተበራከቱ መሆኑ ነው።

በኢትዮጵያ ግብረ ሰዶማዊነት እየተስፋፋና ግብረ ሰዶማዊ ጥቃትም እየተፈጸመ ስለሆነ ድርጊቱ ከመስፋፋቱና ‹‹ለኛም መብት ይሰጠን›› የሚል ጥያቄ ከመነሳቱ በፊት መንግሥት ከእንጭጩ ሊገታው ይገባል።

በዛሬው የዶሴ መደሰናዷችንም በታዳጊዎቹ ላይ ግብረ ሰዶም ወንጀል የፈፀመው ግለሰብ በእስራት የመቀጣቱን ነገር ልንነግራችሁ ወድደናል። ከላይ እንደጠቀስነው ግብረ ሰዶማዊነት በየጓዳችን፣ በየሰፈራችንና በጎረቤትም ጭምር አብሮን እየዋለ እያደረ ነው። ኑሯችን የቀድሞው ማ|ሕበራዊ መስተጋብራችን በጠቅላላው እንዴት ዋልክ(ሽ)? እየተባባልን አንዳችን የአንዳችን ጤንነት የሚያሳስበን ጎረቤታሞች መሆናችን ላይ እያሳየን ያለነው ክፍተት እኔ ካልተነካው ስለሌላው ምን አገባኝ እያልን በዝምታና በቸልታ የምናልፋቸው ነገሮች ሁሉ ለእነዚህ እኩይ ተግባር ፈጻሚዎች የተመቻቸው ሁኔታው ፈጥረዋል።

የአብዛኞቻችን ልጆች እደጅ ወጥተው ከእኩዮቻቸው ጋር መጫወት መቦረቅ በእድሜያቸው የሚመጥናቸው ተግባር ነው። ይህንንም በተግባር ይፈጽሙታል። በዚህ መካከል ግን አንዳንድ ለሰይጣናዊ ድርጊት የሚያጫቸውም አይጠፉ። ታዲያ ምን ቢጠነቀቁ ሰይጣናዊ ድርጊት የተጸናወታቸው ግለሰቦችም ፍላጎታቸውን ለማሟላት ቀን መጠበቅ እና አሳቻ ሰዓትን መምረጥ ማሰብ የተለመደ ነውና ልጆቹን ይከታተሏቸዋል።

የግብረ ሰዶሙ ድርጊት የተፈጸመው በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ ልዩ ቦታው ማር ተራ ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ ነው። ከላይ እንዳነሳሁት የዚህ ሰፈር ልጆችም ተሰብስበው በመጫወት ላይ እያሉ በመካከል መጣላትም መታረቅ ይኖራል። ለምግብ አልያም ውሃ ሲጠማቸው ቤታቸው ድረስ ብሎ መመለስ ሁሌም የሚያዘወትሩት ተግባራቸው ነው። ይህ ተግባራቸው ብዙዎችን የሚያስደስት ቢሆንም እንደ ወንጀል ፈጻሚው አይነት ግለሰቦች ደግሞ ልጆቹን ከመንገዳቸው ለማሰናከል እና በራሱ ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት ምን ዓይነት መንገድ ልጠቀም የሚለው ነገር እንቅልፍ ይነሳዋል።

ታዲያ በዚህ ሰፈር ነዋሪ የሆነው የ43 ዓመቱ ጎልማሳም እነዚህን ህጻናት የሚያጠምድበትን መንገድ ጊዜ ወስዶ አስቦበታል። በምን ቢያታልላቸው እና ቢያማልላቸው እጁ እንደሚገቡም ብዙ አስቦበታል፤ ምናልባትም ከመሰሎቹ ጋር ተማክሮበትም ይሆናል።

በአይኑ የገቡትን የአምስት፡፡ የስድስት እና የአስር ዓመት ታዳጊዎችንም በቀለበቱ ውስጥ አስገብቷል። ግን ደግሞ እነዚህ ልጆች በምን መልኩ ነው ወደእሱ የሚመጡት የሚለውን ማሰብና መወሰን ጊዜ ወደሰበት። ነገር ግን ወደኋላ አላለም። ልጆቹን በተለያየ ጊዜ በመጥራት ፍቅር በማሳየት አንዳንዴም አብሮ በመጫወት እንዲቀርቡት አደረገ። ይህ አካሄዱ ደግሞ ልጆቹ እንዲያምኑት አደረጋቸው። በህጻናቱ ንጹህ ህሊና የታመነው ይህ ግለሰብ ግን እምነታቸውን በልቶ መንገዳቸውን ሊያበላሽ ልጅነታቸውን ሊያሰናክል አሰበ። አሰላሰለም። አስቦም አልቀረ። ሶስቱንም ህጻናት በተለያየ ቀን በየተራ ቤቱ እያስገባ የግብረ ሰዶም ተግባሩን ፈጸመባቸው።

ይህ አስነዋሪ ተግባሩ ደግሞ እንዳይጋለጥ ልጆቹም አስፈላጊውን እርዳታ በጊዜው እንዳያገኙ አስፈራራቸው። የልጅ ነገር ሆኖም ፈሩትና ዝም አሉ። ነገር ግን የስድስት ዓመቱ ልጅ የደረሰበትን ነገር ከእናቱ ሸሽጎ መቆየትን አልመረጠም፤ ክፉና ደጉን ባልለየው አእምሮው



በእኛ ባህልና ወግ ባልና ሚስት እንኳን በሰው ፊት አይሳሳሙም፤ ነገር ግን ድህነታችንን ተጠቅመው የተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች እየመጡ ቆሻሻ ተግባራቸውን ሲፈጽሙብን ዝም ልንል አይገባም

የተፈጠረውን ነገር ባያውቀውም አገናዝቦ ምን እንደሆነ ባይረዳውም እናቱ ታውቅ ዘንድ ግን ሁሉንም ነገር ነገራት።

እናት በሰማችው ነገር እጅጉን ደነገጠች፡፡ አለቀሰች። አነባች ልጇን ያበላሸባትን ጎልማሳ ብትገለው ተመኘች፤ ነገር ግን እሱን ገድላ ልጇን የባሰ ላለማጣትና ላለመጉዳት ወሰነች። ግን ምን ታድርግ። ጠንካራዋ የታዳጊው እናት ሀዘኗን እና ቁጭቷን በውስጧ ይዛ ወደ ህግ ሄደች፤ ፍረዱኝ። ህጻን ልጄን አበላሸብኝ፤ ስትልም ክሷን እና አቤቱታዋን አቀረበች።

የእሷን አቤቱታ የሰሙ የመንደሯ ሰዎችም ልጆቻቸውን መጠየቅ ጀመሩ። አንዱ የታዳጊው ጓደኛ እሱም የችግሩ ተጠቂ መሆኑን እና ግለሰቡ በተደጋጋሚ በቤቱ እየወሰደው የግብረሰዶም ወንጀል እንደፈጸመበት ለወላጅ አባቱ አረዳቸው። ይህንን የሰሙም አባት ቤታቸው ቁጭ ብለው ደቂቃዎችን ማባከን አልፈለጉም በአፋጣኝ ወደአካባቢያቸው ፖሊስ ጣቢያ ሄዱ፤ ፖሊስም ወደ ህክምና ላካቸው። የህክምና ማስረጃቸውን ይዘው በመመለስም ክሳቸውን መሰረቱ።

ፖሊስ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር አውሎ ሶስት የክስ መዝገቦችን አደራጅቶ ምርመራውን በማድረግ ክስ መሰረተበት። ክሱን የመሰረቱት የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ የሴቶችና ህጻናት ወንጀል ምርመራ ማስተባበሪያ ኃላፊ ምክትል ኢንስፔክተር ጸጋዬ ታምራት እንደሚሉትም፤ " ከአንደኛው ከሳሽ በተጨማሪ የሁለተኛና ሶስተኛ ከሳሾችን አቤቱታ በመቀበልና ምርመራውን በማስፋት የህክምና እንዲሁም የአቃቤ ህግ ማስረጃዎችን በማጠናቀር ለፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ እንዲቀርብ ሆኗል"። ለፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ የቀረበው ክስ ላይም ግለሰቡ የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲተላለፍበት አድርጓል።" ያሉት ምክትል ኢንስፔክተር ጸጋዬ፣ በዚህም መሰረት ግለሰቡ በ19 ዓመት 6 ወራት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ፍርድ ተሰጥቷል።

ግብረሰዶማዊነትን ለመከላከል በሚሰራው ስራ ላይ ሁሉም ሰው ጥቆማን ከመስጠት ጀምሮ አጥፊዎችን ለህግ በማቅረቡ ሂደት ላይ የበኩሉን መወጣት እንዳለበትም አሳስበዋል።

"ቤተሰብም ልጆቹ የት እንደሚውሉ፣ ምን እንደሚያደርጉ መቆጣጠር፣ አጠራጣሪ ነገሮችንም ሲያዩ ልጆቹን መጠየቅና መከታተል ያስፈልጋል።" ያሉት ምክትል ኢንስፔክተር ጸጋዬ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ወንጀሉ ተፈጽሞ ሲገኝ ቤተሰብ ልጆቹን መሸሸግ አልያም ሰው ምን ይለኛል ብሎ ሳይሳቀቅ በቀጥታ ወደ ህግ መምጣት እንዳለበትም መክረዋል።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ˆአስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# ካንሰርን - በአሸናፊነት

መልካምሥራ አፈወርቅ

### የመርካቶዋ ጭምት

የመሀል መርካቶ ልጅ ናት። ውክቢያ ግርግር ከበዛበት፣ የሰዎች አጀብ ከሚታይበት ደማቅ ሰፈር አድጋለች። መርካቶ የበርካቶች መገኛ፣ የብዙኃን ንግድ መናኸሪያ ነው። የአካባቢው ጎዳና ጭርታን አያውቅም። ሁሉም በግፊያና ትግል ሲሮጥበት ይውልበታል።

ፍቅርተ አለማየሁ /ስሟ የተቀየረ / ባህርይዋ እንደሰፈሯ አይደለም። ዝምተኛና ጭምት ነበረች። ለቤቱ የመጀመሪያ ናትና የወላጆቿ ዓይን ያርፍባታል። ከድሀ ቤተሰብ ብትገኝም አባቷ ስለእሷ ያላቸው ግምት ለየት ይላል። አቅማቸው ባይፈቀድም ከእኩዮቿ እንዳታንስ ከፍለው ያስተምሯታል። ጠዋት ማታ እጇን ይዘው ትምህርት ቤት አድርሰው ይመልሷታል።

የዛኔዋ ትንሽ ልጅ አድጋ ትምህርቷን እስክትጨርስ ባህርይዋ አልተለወጠም። ዛሬም ጭምትና ዓይናፋር ነች። ወላጆቿ ጌጥ ውበት ሳያምራቸው ስለእሷ ዋጋ ከፍለዋል። በተለይ አባቷ ቁምነገር ደርሳ እንዲያዩ ምኞታቸው ነበር። ፍቅርተ አላሳፈረቻቸውም። በትምህርቷ በርትታ ፣ በጉብዝናዋ ስማቸውን አስጠራች። ዕድሜዋ ከፍ ማለት ሲይዝ ዩኒቨርሲቲ ገብታ ተመረቀች። ይህኔ ወላጆቿ ደስታቸው ጨመረ። ልፋት ድካማቸው ፍሬ ይዟልና ፈጣሪያቸውን አመሰገኑ።

ፍቅርተ ትምህርቷ እንዳበቃ በተማረችበት ዘርፍ ሥራ አግኝታ ተቀጠረች። እንዲህ መሆኑ ራሷን እንድትጠብቅ፣ ቤተሰቧቿን እንድታስብ ዕድል ቸራት ። ከእጇ የገባው ገንዘብ ቁምነገረኛነቷን አጎላው። የቢሮ ሠራተኛ ሆና ደሞዝተኛ ተባለች። ልጅነቷ አበቃ፣ በዝነጣ ቦርሳ አንግታ ሥራ መመላለስ ያዘች።

### ሦስት ጉልቻ...

አሁን ፍቅርተ ውበቷ አብቧል። ወጣትነቷ ከብዙዎች ዓይን እየጣላት ነው። ይህ ዕድሜ ለብዙ ወጣቶች ፈተና ይሆናል። ፍቀርተ ግን የልጅነት ባህርይዋ ከእሷ እንዳለ ነው። ዛሬም እንደትናንቱ ጨዋና ጭምት ነች። ይህ ባህርይ ከሌሎች አስመረጣት። እሷን ያሉ ዓይኖች ከዓይኖቿ አርፈው ከውሃ አጣጪዋ ተገናኘች ።

ፍቅርተ ትዳር መስርታ ጎጆ ስትወጣ ከቤተሰቦቿ ራቀች። ዛሬ አስራ አምስት ዓመታት ከቆጠረችበት ጥምረት ሁለት ልጆች አፍርታለች። ከባለቤቷ ጋር ተዋደው ፣ ተከባብረው ይኖራሉ።

ፍቅርተ በምትሰራበት የመንግሥት መስሪያ ቤት ከበርካቶች ጋር መግባባት ልማዷ ነው። ያየችውን ታከብራለች። የቀረበችውን ትወዳለች። ኑሮና ትዳሯን የምታከብረው ወይዘሮ በሃይማኖት የበረታች፣ በዕምነቷ የጸናች ናት። ጠዋት ማታ ስለሆነላት በጎነት ለአምላኳ ምስጋናን አታጓድልም።

### አንድ ማለዳ ...

ጊዜው የሐምሌ ወር መጀመሪያ ነው ። ማለዳው በዳመና ተይዞ ሰማዩ መጥቁር ጀምሯል። ‹‹መጣሁ›› እያለ የሚያስፈራራው ዝናብ ቀኑን ለማክበድ እንዳሰበ ያስታውቃል። ከአልጋ ለመልቀቅ የሚፈትነው አየር ከቤት ለመውጣት አያስመኝም ። ፍቅርተ ከሞቀ አልጋዋ የቀሰቀሳት እንደልማዷ ሥራ መሄዷ ነበር። ጉዳይዋ ግን ይህ ብቻ አልሆነም። ደርሶ ከብብቷ ስር የሚሰማት ሕመም ሰላም ይነሳት ይዟል።

ቀኝ እጇን ወደ ግራ ብብቷ ሰዳ ቀስ ብላ ዳሰሰችው። አንዳች ነገር ጣቷ ላይ ጎርበጥ ሲል ተሰማት። ደነገጠች። በሃይማኖቷ የጸናች ናትና ቤት ካኖረችው የቤተክርስቲያን ዕምነት አንዱን አንስታ ተቀባባች።

ቢሮ ስትገባ ስለሁኔታው እያሰበች ነበር። እየቆየ የሚጠዘጥዛት ነገር አሁንም አልተዋትም። ስሜቱ እየጨመረ ሲሄድ ለቅርብ ባልንጀራዋ አዋየቻት። ባልንጀራዋ ልብሷን ገልጣ አየችና ድንገት የሚያጋጥም የዕጢ መቆጣት መሆኑን ነገረቻት። ፍቅርተ ለጊዜው እንደመረጋጋት ብላ ሥራዋን ቀጠለች።



ፍቅርተ ዕለቱን ከጓደኛዋ ጋር ቤተክርስቲያን ለመሳለም ሄደች ። በስፍራው ደርሳም ‹‹ይበጃል›› ያለችውን ሁሉ አደረገች። ዕለተ ዓርብ አልፎ ቅዳሜ ተከተለ። ዕሁድ ማለዳ ገላዋን ታጥባ ልብሷን መልበስ ስትጀምር አንዳች ነገር ጡቷን ሲከብዳት ተሰማት።

ለአፍታ በአእምሮዋ ብልጭ ያለው ስሜት ፈጥኖ ከውስጧ ተመላለሰ። ግራ ጡቷ ላይ እየጠዘጠዘ ሰላም የነሳት ሕመም የጤና አለመሆኑን ጠረጠረች። ፍቅርተ ከልጅነቷ ጀምሮ ስትሰማው የኖረችው አንድ እውነት በየአጋጣሚው ሲረብሻት ኖሯል። የጡት ሕመም ይሉትን ጉዳይ አጥብቃ ትፈራዋለች። ከዚህ ችግር ጋር አብሮ የሚነሳው ‹‹ካንሰር›› የተባለ ሕመም ደግሞ አደገኛ መሆኑን አሳምራ ታውቃለች።

ፍቅርተ ስለራሷ ብዙ እያሰበች ጡቷን በዝግታ ዳሰሰች። ከላይ ከታች እያለች ጣቶቿን አመላለሰቻቸው። ከዚህ በፊት አይታው ፣ ነክታው የማታውቅ ዕባጭ ነገር ከመዳፏ ሲገናኝ ተሰማት ። በድንጋጤ ክው እንዳለች በዝምታ ተዋጠች።

### ማግስቱን...

ዕለተ ሰንበት እንደምንም መሸቶ ነጋ። ሰኞ ቀን ስራዋ ስትደርስ የጀመራት ሕመም ተባብሶ ነበር። አሁን ፍቅርተ ሕመሟን ውጣ የምትደብቀው አልሆነም። እየሆነ ያለውን ሁሉ ለሌሎች ማጋራት አለባት። ሁኔታዋን ያስተዋሉ ችግሯን የተጋሩ ለመፍትሄው ተጣደፉ። አሉ የተባሉ የሕክምና ዶክተሮችን ፈልገው አገናኟዋት።

ለአጠቃላይ ምርመራ ከሀኪም ዘንድ ተገኘች ። አሁንም ውስጧ ስለጡት ሕመም የሰማችውን ሁሉ እያመላለሰ ያስጨንቃታል። ከዚህ ቀድሞ በጡቷ ላይ አንዳች ሕመም ተሰምቷት አያውቅም። በእርግጥ አንዳንዴ ራስ ምታት ያስጨንቃታል። ዶክተሩ ምርመራውን አጠናቆ ሊነግራት ሲዘጋጅ የፊቱን ገጽታ በጥንቃቄ ማንበብ ጀመረች።

እሱ ቃል ከማውጣቱ በፊት የሚለውን ገመተች። አሁንም ፊቱ መልካም ነገር አላሳያትም። አስተውላ አየችው። የፈራችው አልቀረም። ዶክተሩ በጡቷ ላይ የሚታየው ውጤት ችግር እንዳለበት የሚያመላክት መሆኑን ነገራት።

### የብርታት ጅማሬ ...

ፍቅርተ ውጤቱን እንደሰማች ራሷን ማጽናናት ፣ ማበርታት ያዘች። እስከዛሬ የፈራችው፣ በሌሎች ሲደርስ ያየችው ሕመም ከእሷ ጋር እንዳይሆን እየሰጋች ነው። እንዲህ በተሰማት ጊዜ ዕምነቷን በፈጣሪ ትታ ውስጧን አበረታች ። ወዲያው እንደብረት የጠነከረ ጽናት በልቧ ሲፈስ ተሰማት።

ምርመራውን ያካሄደው ዶክተር ያሬድ ከጎኗ ለመሆን የቻለውን አደረገ ። ቅንነቱ አግዟት ለቀጣዩ ሂደት አዘጋጃት። የናሙና ምርመራውን ለማካሄድ መፍጠን ነበረባት። ሁኔታዎች ግን እንደታሰቡት አልሆኑም። ይህን ለማድረግ ረዘም ያለ ቀጠሮ ተሰጣት ። ፍቅርተ በሁኔታው ብታዝንም ተስፋ አልቆረጠችም። ዶክተር ያሬድ ተመለሺ ባላት ቀን በስፍራው ተገኘች። ሀኪሙ ተጣድፎ የናሙናውን ውጤት እንድትሰጠው ጠየቀ። እንደከፋት ስለቀጠሮው መራዘም አስረዳችው። ውስጡ እያዘነ ለሌላ መፍትሄ ተጣደፈ። ጊዜ አልወሰደም ። ዳግም የሕክምና ማዘዣውን ጽፎ ሰጣት ።

ከሦስት ቀናት በኋላ ውጤቱን ይዛ ከፊቱ ቀረበች። ዳግም በዶክተሩ ገጽታ የሚያስደነግጥ ምልክት ያስተዋለችው ወዲያው ነበር። እሱ አሁን ይበልጥ እርግጠኛ የሆነበት የናሙና ውጤት ከእጁ ገብቷል። በአንደበቱ ‹‹አዎ ! የጡት ካንሰር ነው›› ለማለት ግን አልደፈረም።

ከሁኔታው ምላሽ ያገኘችው ፍቅርተ ለዶክተሩ እንዳይጨነቅ ነግራ የመጣውን ሁሉ በበጎነት በፀጋ እንደምትቀበል አሳወቀችው ። ብርታት ጥንካሬዋን ያስተዋለው ሀኪም በሁኔታዋ ተደነቀ። ይህ እውነትም ልቡን ለበጎ አዘጋጅቶ ለሌላ መፍትሄ ከሌላ ሀኪም እንድትሄድ መንገድ መራት።

### ከካንሰር ጋር ፍልሚያ ...

ፍቅርተ የቀጣዩን ሀኪም ስም በልቧ እንደያዘች ወደ ፀበል አመራች። ለእሷ ልክ እንደህክምናው የዕምነት ፅናቷ ያስፈልጋታል። ሁለቱንም ጎን ለጎን ሳትለያይ መቀጠል እንዳለባት ወስናለች።

ባለቤቷ በእሷ ላይ የሆነውን ባየ ጊዜ በእጅጉ አዘነ። እስካሁን ላይሆን ይችላል ብሎ የተጠራጠረበት ጉዳይ አሁን በሕክምናው ዕውን ሆኗል። ይህን ሲረዳ ከጎኗ ሊሆን ተዘጋጀ። በወቅቱ ፍቅርተ ሕክምናውን የጀመረችው ዶክተር እንግዳ ከሚባል ሀኪም ዘንድ ነበር ። እሱም እንደቀድሞው ሀኪም በመልካም ትህትና ተቀብሎ አስተናገዳት።

ፍቅርተ በጡቷ ላይ የተከሰተው ካንሰር ሁለተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ተነግሯታል። እሷ በወቅቱ ስለበሽታው ከመጨነቅ ለመፍትሄው ታደላ ነበር። ስለሕመሙ የሚነገሩ፣ መረጃዎችን በመከታተል ግንዛቤ ለመውሰድ ትጥራለች። ሕፃናት ልጆቿ እንዳይጨነቁና ቤተሰብ እንዳያዝን ራሷን ቀድማ ታበረታለች።

### አካልን በስንብት ...

ውሎ አድሮ ወይዘሮዋ ከራሷና ከባሏ ተማከረች። ከሀኪሞች ተነጋግራም ከውሳኔ ደረሰች ። ለቀናት ከሆስፒታል ተኝታ በቀዶ ህክምና ግራ ጡቷ እንዲወገድ ሆነ። ለሴት ልጅ ጡት ማለት የማንነቷ ምልክት፣ የጾታዋ መለያ ነው። ከውበት አልፎ እናትነቷን የምትቸርበት በረከቷ ጭምር።

ፍቅርተ ይህ አካሏ ተቆርጦ ሲወገድ እንደሴት፣ ብሎም እንደእናት ለአፍታ ‹‹ሸው›› ያለባት ስሜት አልጠፋም። እንዲያም ሆኖ ስሜቱ አብሯት አልቀጠለም። ሁሉን ትታ ፈጣሪን ለማመስገን አልዘገየችም። ለእሷ ሕመሟ ታውቆ ለሕክምና መድረሷ ብቻ ታላቅ ጸጋ ነው። ዛሬም ‹‹ሁሉም ለበጎ ነው›› ባይነቷ ማንነቷን አጽንቷል።

### እንዳያልፉት የለም የ‹‹ ኬሞ›› ፈተና ...

በቀዶ ሕክምና አንድ ጡቷ ከተወገደ በኋላ ቀጣዩ ሂደት የጨረርና የኬሞ ቴራፒ ሕክምና ነበር ። ፍቅርተ ይህ አይነቱ ሂደት በእጅጉ ፈትኗት አልፏል ። ዛሬ ላይ ሆና ያን ጊዜ ስታወሳው የመድኃኒቱን ክብደት ገድሎ እንደማንሳት ትቆጥረዋለች ።

ፍቅርተ ሕክምናውን ስትወስድ በእጅጉ ይደክማት ነበር። የምግብ ፍላጎት ማጣት ማስመለስና ሌሎች ችግሮችም ፈትነዋታል። በዚህ ወቅት ጥፍርና ጸጉር ይሏቸው አብረው እንዳልተፈጠሩ ይከዳሉ። ሰውነት ይዝላል፣ ማንነት ይሸሻል። መልካም ባህርይን ይለውጣል።

በዚህ ፈታኝ ወቅት ከጎኗ የነበሩ ቤተሰቦቿና የመስሪያ ቤት ባልደረቦቿ ሕመሟን እንድትረሳ ከጎኗ ቆመዋል። በጎዶሎዋ ተገኝተው ሙላት በረከት ሆነዋታል። ‹‹አይዞሽ ፣ አለንሽ›› ሲሉ ዕንባዋን አብሰዋል። ይህ ወቅት ከማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ጋር የተገናኘችበት ነበር። ተቋሙ በወቅቱ አስፈላጊ የሕክምናና የመድኃኒት እገዛ አድርጎላታል። የባለሙያ ምክር ባስፈለጋት ጊዜም ከጎኗ ተገኝቷል። በተለይ በዘመነ ኮረና ሶሳይቲው ያለውን አካፍሎ ህይወቷን መታደጉን ፈጽሞ አትረሳውም።

ፍቅርተ በስምንት ተከታታይ ዙር የወሰደችውን ‹‹ኬሞ ቴራ›› በብዙ ውጣውረድና ፈተና በድል አጠናቀቀች። ይህ ጥንካሬዋ ዛሬን በህይወት እንድቀጥል ነገን በተስፋ እንድታስብ ዕድል ቸሯታል ። ለዚህ ማንነቷ ከጎኗ የነበሩ የሥራ ባልደረቦቿ ከልቧ ውስጥ ልዩ ስፍራ አላቸው። ፍቅርተ ከእሷ ጋር ሕክምናውን የጀመሩ ብዙዎች ዛሬ በህይወት እንደሌሉ ታውቃለች። ይህን እውነት መለስ ብላ ስታስበው ፈጣሪን ከማመስገን በላይ ቃል የላትም።

### ዛሬና ትናንት ...

አሁን ወይዘሮዋ በሕክምናው ያለፈችበት መንገድ ተቋጭቶ፣ በመልካም ጤንነት ቆማለች። ትናንት የተጎዳ አካሏ ወዝ ተመልሷል፤ የረገፈ ዞማ ጸጉሯ እንደ አዲስ በቅሎ ውበት አላብሷታል።

ስለጡቷ እንዲህ ነው ብላ ካላወጋች ለምን የሚያስብል ምልክት የለባትም። እንደ ቀድሞው ሥራዋ ውላ ትገባለች። ዛሬም የባሏ ሚስት፣ የልጆቿ እናት ከመሆን ያገዳት የለም። ደስተኛና ሰላማዊ ህይወት እየመራች ነው። ፍቅርተ ዘወትር አመስጋኝ ነች። ሁሌም ከአንደበቷ የፈጣሪ ምስጋና አይጠፋም።


ዛሬም በቋሚነት የምትወስደውን መድኃኒት ያለመሰልቸት ትጠቀማለች። አሁን ላይ የሚሰማት ሕመም የለም። አንዳንዴ ከሀኪሞች ስትገናኝ ግን ስላለችበት የጤና ሁኔታ አንድ ነገር እንዲሏት ትሻለች። እስከዛሬ ከተለመደው ምርመራ የዘለለ ስለሕመሙ የሚያስረዳትን ሀኪም አላገኘችም። መጠየቅ መወያየት ብትፈልግም ይህ አይነቱ ዕድል ያለመኖሩ በጥያቄ ውስጥ እንድትኖር አድርጓታል።

### መልዕክት ለሴሎች...

‹‹እኛ ታመን ካልጋ ካልወደቅን በቀር ሀኪም ዘንድ አንሄድም። ማንም ሰው ሕመም በተሰማው ጊዜ ፈጥኖ ሀኪም ቤት የመሄድ ልምድ ሊኖረው ይገባል።ቢቻል ጊዜ ወስኖ በየዓመቱ የጤና ምርመራ ማካሄድ ጥሩ ነው። ውድ ሴቶች ይህ አይነቱ ሕመም ቢገጥማችሁ ፈጥናችሁ ተስፋ አትቁረጡ። በሽታው ገዳይ ነው ብላችሁም ቀድማችሁ አትሙቱ። ሁሌም ለመፍትሔው በመትጋት በጥንካሬ መሻገር እንደሚቻል ከእኔ ህይወት ተማሩ ››

ዛሬ ፍቅርተ የጡት ካንስርን አሸንፋ በድል መራመድ ከጀመረች ስድስት ዓመታት ተቆጥረዋል። አሁንም ውስጧ ታላቅ ተስፋ እንደተሞላ ነው ። ነገ ለእሷ ብሩህ ሆኖ ይታያታል። ራሷን ትጠብቃለች፣ በፈገግታ ትውላለች። ፈጣሪዋን ደግማ ደጋግማ ታመሰግናለች።

# ስፖርት



# አፍሪካውያን የረጅም ርቀት ኮከቦች የሚመሩት የዓመቱ ምርጥ አትሌቶች ምርጫ

ዓለማየሁ ግዛው

እአአ ከ1988 አንስቶ በዓለም አትሌቲክስ መሪነት የሚካሄደው የዓመቱ ምርጥ አትሌቶች ምርጫ ከአፍሪካ ጥቂት ሀገራት የተወጣጡ አትሌቶች ብቻ ተሸላሚዎች ሆነውበታል። ከወር በኋላ ይፋ በሚደረገው የዓመቱ ምርጥ አትሌቶች ምርጫ ላይ ግን አፍሪካዊያን አትሌቶች ቀዳሚ ተፎካካሪ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። በተለይም በሴቶች በሚጠበቀው ምርጫ ላይ የዓለምን ክብረወሰን በመሰባበር ብቃታቸውን ያስመሰከሩ ሶስት አፍሪካውያን አትሌቶች በእጩነት መቅረባቸው የአሸናፊነት ግምት እንዲያገኙ አድርጋል።

ሴት አፍሪካዊት አትሌት ለመጨረሻ ጊዜ በዘርፉ ተሸላሚ የሆነችው ከ7 ዓመታት በፊት ሲሆን፤ በመካከለኛና ረጅም ርቀት አትሌቲክስም ከዓመታት ወዲህ የሚያሸንፍ አትሌት ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል። ከ11ዱ እጩ አትሌቶች አሸናፊ ይሆናሉ ተብለው ከሚጠበቁት መካከል በተጠናቀቀው የመስከረም ወር ሁለት ታላላቅ የዓለም ክብረወሰኖችን የሰበሩት ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ጉዳፍ ጸጋይ እና ትዕግስት አሰፋ ናቸው። ሌላኛዋ አትሌት ደግሞ ኬንያዊቷ ፌይዝ ኪፕዮጎን ናት።

ከቡዳፔስቱ የዓለም ቻምፒዮና አስቀድሞ ድንቅ አቋምና ፈጣን ሰዓት ስታስመዘግብ የቆየችው ኢትዮጵያዊቷ ኮከብ አትሌት ጉዳፍ፤ በዓለም ቻምፒዮና በ10ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ማጥለቋ የሚታወስ ነው።




ዓመቱን በምርጥ ብቃት ያሳለፈችው ጉዳፍ በዳይመንድ ሊግ የ5ሺ ሜትር ውድድር በኬንያዊቷ ፌይዝ ኪፕዬጎን ተይዞ የነበረውን የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን 14:00.21 በሆነ ሰዓት ዩጂን ላይ ማስመዝገቧ ይታወቃል። ይህም በዓመቱ በ5ሺ ሜትር እና 10ሺ ሜትር ርቀቶች የዓመቱ ንግስት ያደረጋት ሲሆን፤ የዓለም አትሌቲክስም በዚሁ ምክንያት ለዓመታዊው ክብር አጭቷታል።

የዓለም የማራቶን ክብረወሰንን ባለፈው ወር የጨበጠችው አትሌት ትዕግስት አሰፋም የዓመቱ ምርጥ ሴት አትሌቶች የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ዝርዝር ውስጥ ከመካተት ባለፈ አሸናፊ ትሆናለች የሚለው የስፖርቱ ቤተሰብ ግምት አግኝታለች። ትዕግስት 2019 ቺካጎ ማራቶን ላይ በኬንያዊቷ አትሌት ብሪጊድ ኮስጌ የተመዘገበውን ክብረወሰን በዘንድሮው የበርሊን ማራቶን ከሁለት ደቂቃ በላይ በማሻሻል 2:11:53 በሆነ ሰአት አዲስ የማራቶን ክብረወሰን ማስመዝገቧ ይታወቃል። አትሌቷ ቀደም ሲል የ800 ሜትር ተወዳዳሪ በመሆን ወደ አትሌቲክስ ገብታ ፊቷን ወደ ጎዳና ውድድሮች ብትመልስም በከባድ ጉዳት ምክንያት ለረጅም ጊዜ ከውድድር ውጪ ነበረች። ሩጫ እንድታቆም በሃኪሞች ቢነገራትም ተስፋ ሳትቆርጥ በማራቶን ታሪክ ክብረወሰን የሰበረች የመጀመሪያዋ ሴት ኢትዮጲያዊት አትሌት ልትሆን ችላለች። ይህ ጽናቷ እንዲሁም ከጉዳት ተመልሳ ለማመን የሚከብድ አስደናቂ ብቃቷን በማሳየቷም ለዓመቱ ምርጥ አትሌትነት ክብር ለመታጨት በቅታለች።

በተለያዩ ርቀቶች ስመጥር አትሌቶች እጩ በሆኑበት ዝርዝር ፌይዝ ኪፕዬጎን የምታሸንፍ ከሆነ ደግሞ በታሪክ የመጀመሪያዋ ኬንያዊት ሴት አትሌት ትሆናለች። 22ቱ አትሌቶች በዓመቱ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና፣ በቤት ውስጥ፣ በመምና ጎዳና ውድድሮች ባስመዘገቡት ውጤትና ባሳዩት አቋም በዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ባለሙያዎች ሊመረጡ ችለዋል።

በዚህ ዘርፍ ለመጨረሻ ጊዜ ያሸነፈችው ኢትዮጵያዊት የረጅም ርቀት ሯጯ አትሌት አልማዝ አያና እአአ በ2016 ሲሆን፤ በ2007 አትሌት መሰረት ደፋር ምርጥ አትሌት በመባል የመጀመሪያዋ ሴት አትሌት ናት። በ2015 ደግሞ አትሌት ገንዘቤ ዲባባ የዓመቱ ምርጥ ሴት አትሌት መባል ችላለች።

በወንዶችም የዓመቱ ምርጥ አትሌቶች እጩ ይፋ ቢሆንም አንድም ኢትዮጵያዊ አትሌት ሳይካተት ቀርቷል። ሞሮኮዋዊ የ3 ሺ ሜትር መሰናክል ቻምፒዮን እና ለ6 ተከታታይ ፍጻሜ ያልተሸነፈው ሶፍያን ኤል ባካሊ እና ኬንያዊው የችካጎ ማራቶን ባለ ክብረወሰን ኬልቪን ኪፕቱን ከአፍሪካ ተካተዋል። ኢትዮጵያዊው የረጅም ርቀት ኮከብ ቀነኒሳ በቀለ በ2004 እና 2005 ባሳየው ብቃትና የዓመቱ ምርጥ አትሌት ሊባል ችሏል። ከዛ ቀደም ብሎ እአአ በ1998 ጀግናው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ የዓመቱን መርጥ አትሌትነት በመጎናጸፍ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ነው። በታዳጊ አትሌቶች ዘርፍም የዓመቱ ምርጥ ወንድ አትሌቶች ምርጫ እአአ 2005 የተጀመረ ሲሆን፤ ኢትዮጵያዊው አትሌት ሰለሞን ባረጋ በወጣቶች ዘርፍ 2019 የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ወጣት አትሌት በመሆን ተመርጧል።

በምርጫው የዓለም አትሌቲክስ ምክር ቤት 50 ከመቶ ድምጽ ያለው ሲሆን፤ የዓለም አትሌቲክስ ቤተሰቦች እንዲሁም የማህበራዊ ድረገጽ ተከታዮች ቀሪውን ድምጽ ይሰጣሉ። የድምጽ መስጫ ጊዜው ለሁለት ሳምንት ሲቆይ፤ ከወር በኋላ ውጤቶቹ ተጠናቀው ኮከብ አትሌቶች የሚለዩ ይሆናል። አሸናፊዎቹ ደግሞ በመጪው ታህሳስ ወር/2016ዓ.ም ይፋ ይደረጋሉ።


## ማስታወቂያ

አመልካች አቶ ሲሳይ አባተ ፍሰሀ በ2007 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ማኔጅመንት ትምህርት ዘርፍ ተመርቄ የተቀበልኩት የመጀመሪያ ዲግሪ ስለጠፋብኝ ምትክ ይሰጠኝ ብለዋል፡፡ ይህንን ሰነድ በሆነ አጋጣሚ በእጁ ያስገባ ሰው ካለ ማስታወቂያው በጋዜጣ በወጣ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ጽ/ቤት ይቅረብ፡፡ ካልሆነ ግን ምትክ የትምህርት ማስረጃ ለአመልካቹ የሚሰጥ መሆኑን ይገልጻል፡፡

**የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ጽ/ቤት**

## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ
## የግዢ መለያ ቁጥር:- ሽ/ወ/መ/004/2016

በሐረሪ ህዝብ ክልል መንግሥት የሸንኮር ወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤት አላቂ የጽሕፈት መሣሪያዎች ፕሪንተር የጽዳት እቃዎች፤ electronics furnitures ሞተር ሳይክሎች እንዲሁም የቢሮ ጥገና እቃዎች በተመደበው/በጸደቀው የ2016 በጀት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

1. ከላይ የተጠቀሰውን ግዥን ለመፈጸም በዘርፉ የተሰማራችሁ ብቃት ያላችሁ በጨረታ ሰነዱ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ እና በሰነዱ የተገለፁት አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ከመጫረቻ ሰነዶች ጋር በማያያዝ ማቅረብ የሚችሉ አቅራቢዎች/ተጫራቾች በጨረታው እንድትሳተፉ ተጋብዛችኋል፡፡
2. የጨረታው ሂደት በሐረሪ ህዝብ ክልል መንግሥት የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና የግዥ አፈፃፀም መመሪያ በተገለፀው በግልፅ ጨረታ ሥነ-ሥርዓት ይፈፀማል
3. የተሟላ የጨረታ ሰነዶችን ማንኛውም ብቃትና ፍላጎት ያለው ተጫራች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የማይመለስ ብር 400.00 /አራት መቶ ብር/ በመክፈል የተሟላ በአማርኛ የተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ በቢሮ ገንዘብ ያዥ ክፍል ቢሮ ቁጥር 20 ለ15 ተከታታይ የሥራ ቀናት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /Bid Bond/ ብር15,000.00 (አስራ አምስት ሺ ብር) በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የታሸገ ፖስታ ሆኖ በፖስታው ላይ የተጫራቹ ሙሉ ስም፣ አድራሻና ፊርማ ማህተም በማድረግ የተወዳደሩበትን የአገልግሎት አይነት በመግለጽ ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 15 ቀናት ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ድረስ ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን መግባት ይኖርበታል፡፡
5. ጨረታው አየር ላይ ተከታታይ 15 ቀናት ከዋለ በኋላ በ15ኛው ቀን በእለቱ ከጠዋቱ 3፡20 ሰዓት ይዘጋል፤ ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርቡ የመጫረቻ ሰነዶች ተቀባይነት የላቸውም፡፡
6. ጨረታው አየር ላይ ለተከታታይ 15 ቀናት ከዋለ በኋላ በ15 ኛው ቀን በእለቱ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በቢሮ ቁጥር 20 በግዥ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት ክፍል ጨረታው ይከፈታል፡፡
7. ቢሮው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ- በስልክ ቁጥር 0256660214**

**በሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግሥት የሸንኮር ወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሣሽ አቶ አለማየሁ ስለሺ እና በተከሣሾች 1. ሜላት ማስረሻ 2. አብረሃም ዘካሪያስ 3. ዘላለም አማረ 4. መልካሙ ሙላት መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች ክስ የቀረበባቸው መሆኑን አውቀው ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አ/አ/ከ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 4ኛ ፍታብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቦሌ ምድብ ችሎት**

## የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ቁጥር 02/2016

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለመ/ቤቱ አገልግሎት የሚውሉ ከዚህ በታች በሎት የተገለጹ እቃዎችን :

ሎት 1. ኤሌክትሮኒክስ

ሎት 2. አንቲ ቫይረስ

ሎት 3 ሞተር ሳይክል

ሎት 4 ፈርኒቸር

በዚሁ መሰረት፡-

1. በየዘርፉ የታደሰ ህጋዊ ንግድ ፍቃድ ያለው የዘመኑን ግብር የገበረ
2. የቫት /VAT/ ተመዝጋቢነት ሰርተፍኬት ያለው
3. የግብር ከፋይ/TIN/ መለያ ቁጥር ያለው
4. የዕቃና የአገልግሎት አቅራቢነት ሰርተፍኬት ማቅረብ የሚችሉ ድርጅቶች
5. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ ከተራ ቁጥር 1-4 የተጠቀሰውን ማስረጃዎች ኦርጅናልና ኮፒ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታውን ሠነድ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለእያንዳንዱ ሎት ሰነድ የማይመለስ ብር 100(አንድ መቶ ብር)ብቻ ሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢሮ ቁጥር 37 በመክፈል ሠነዱን መውሰድ ይቻላል።
7. ተጫራቾች መወዳደር ለሚፈልጉት ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ CPO/ BID BOND የ90 ቀን/ ለያንዳንዱ ሎት ብር 10,000 በጠቅላይ ፍርድ ቤት ስም በማሠራት ማቅረብ የሚችል
8. ተጫራቾች የፋይናንሻል ዶክመንት ኦርጂናል 1 ኮፒ 1 በተለያየ በሰም በታሸገ ኤንቬሎፕ ለጨረታ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ መክተት ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም ቴክኒካል ዶክመንት ኦርጂናል 1 እና ኮፒ 1 በተለያየ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
9. ጨረታው ጋዜጣ ላይ ከወጣ ከ15 ተከታታይ ቀናት በኋላ በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ 4፡30 ላይ ተጫራቾች /ህጋዊ ወኪሎቻቸው/ በተገኙበት ይከፈታል፡፡ ዕለቱ የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተገለጸው ሰዓት ይከፈታል፡፡
10. የጨረታ አሸናፊ ዕቃውን በራሱ ወጪ አጓጉዞ መጋዝን ማስገባት ይኖርበታል፡፡
11. የጨረታው አሸናፊ በጨረታ መመሪያ መሰረት የጨረታ አሸናፊነቱ በማስታወቂያ ይገለጻል

መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታው በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር፡- 0462125584 መጠቀም ይቻላል፡፡

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት**